ጅማ ዩኒቨርሲቲ
የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማንቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ
አማርኛ ትምህርት ክፍል

# በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው አስተዋፅኦ በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት

በ

አሰፋ በቀለ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል

ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጥቅምት 2012 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

# በምንባብ ውሰጥ የጽሑፍ አወቃቀርን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው አስተዋጽኦ-በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ  አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መረሃ ግብር

በአሰፋ በቀለ

የጥናቱ አማካሪ

ጥበቡ ሽቴ (ዶር)

# ጅማ ዩንቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች

## ስነ-ጽሑፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃግብር

በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው አስተዋጻኦ-በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት በአሰፋ በቀለ አጎናፍር የቀረበን ጥናታዊ ሥራ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

የድፓርትመንት ተጠሪ______________ ፊርማ __________ ቀን _______________

አማካሪ ________________________ ፊርማ ___________ ቀን _______________

የውጭ ፈታኝ_____________________ ፊርማ ___________ ቀን _______________

የውስጥ ፈታኝ____________________ ፊርማ ___________ ቀን _______________

# የአጥኚው ማረጋገጫ

በምንባብ ውስጥ የጽሑፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማገልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፤በሚል ርዕስ በጅማ ዩንቨርስቲ የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲ ኮሌጅ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናታዊ ስራ የራሴ መሆኑን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________________________

ፊርማ______________________________________

ቀን ______________________________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ አስጀምሮ ለአስጨረሰኝ የእውቀት ሁሉ ባለቤት ሁሉን ቻይ ለሆነው ቸር አምላክ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡በመቀጠል ይህንን ጥናታዊ ስራ ስሰራ ስራው የተቃና እንዲሆን ከርዕስ መረጣው ጀምሮ እሰከ ፍጽሜው ድረስ በማማከር ጠንካራ ድጋፍ ላደረገልኝ አማካሪ መምህሬ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ምሰጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡እንዲሁም የስታቲስቲክስ ቀመሮችን በመስራት፣ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተዛማጅ ጽሁፎችን እያፈላለገ ድግፍ ላደረገልኝ  ለአቶ እያሱ ታያቸው  እና ለጥናቱ አጋዥ ማቴሪያሎችን ወይም ቁሳ ቁሶችን በማቅረብ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአቶ አብርሃም መንገሻ እና ለአቶ ሰለሞን አበራ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ለተጠኝ ተማሪዎች የተዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሁፎችን በማስተማር፣መጠየቆችን እና ፈተናዎችን በመስጠት፣ፈተናዎችን በማረም እንዲሁም አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ የባሶ አጠ/2ኛ ደረጃ እና መሰነዶ ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በጥናቱ በመሳተፍና መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በዚህ ትምህርት ቤት በ2011 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ላሉ የ9ኛE እና ለ9ኛK ክፍል ተማሪዎች ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በምንባብ ውሰጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን በማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለው አስተዋጽኦን መፈተሽ ነው፡፡ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በመጠናዊ የምርምረ ዘዴን በመከተል ሙከራ አልባ ፍትነታዊ(Quasi experimental research)የጥናት ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ፣በብልሃት በማስተማርና በተለመደው የአንብቦ መረዳት የማስተማር አቀራረብ በመስተማር ሁለቱን ቡድኖች በቁጥጥርና በሙከራ በመመደብ ለአራት ሳምንታት በጥቅሉ ለስምንት ክፍለ ጊዜያት የአንብቦ መረዳት ትምህርት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎች በደብረብርሃን ከተማ በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት በ2011 ዓ.ም ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ካሉ በአስራ አራት(14) የመማሪያ ክፍሎች ተመድበው በመማር ላይ ከሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በዕድል ሰጪ (በዕጣ) ንሞና ከተመረጡ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች፣በ9ኛE ክፍል ያሉ (42) ተማሪዎችን በቁጥጥር ቡድንነት፣በ9ኛK ክፍል ያሉ (40) ተማሪዎችን በሙከራ ቡድን በጥቅሉ በ(82) ተማሪዎች ላይ ጥናቱ ተደርጓል፡፡ከተሳታፊዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመመዘን በጽሁፍ መጠይቅ እና በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና መረጃ ተሰብሰቧል፡፡መረጃዎችም በአማካይ ውጤት፣በመደበኛ ልይይት፣በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት በገለፃና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ጥናቱ እንደ አመለከተው በተለመደው (በተዘውታሪው) የማስተማሪያ ዘዴ አንብቦ መረዳትን ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች ይልቅ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን የተማሩት የሙከራ ቡድን የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው መሻሻል አሳይቷል፡፡ከቅድመ ትምህርቱ የፈተና ውጤት አንጻር የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በሁለቱም ቡድኖች መሻሻል ቢታይም የሙከራ ቡድን ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት የጉልህነት ልይይት በ4.55 የላቀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ስለዚህ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር እንደሚችል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት በመነሳት ወደፊት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ ምንባቦቹ ሁሉንም የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች እንደ የክፍል ደረጃው ያካተቱ መልመጃዎች ቢኖራቸው የሚል የመፍትሄ ሐሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

# የይዘት ማውጫ

የአጥኚው ማረጋገጫ ........ i
ምስጋና ........ ii
አጠቃሎ ........ iii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ vi
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር ........ 6
1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 9
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 9
1.5 የጥናቱ መላምት ........ 10
1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 10
1.7 የጥናቱ ወሰን ........ 11
1.8 የጥናቱ ውስንነት ........ 11
1.9. የሙያዊ ቃላትና ሀረጋት ፍች ........ 12
ምዕራፍ ሁለት ........ 13
ክለሳ ድርሳናት ........ 13
2.1 የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳቦች ........ 13
2.2. የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች ........ 15
2.3 አንብቦ መረዳት እና የጽሁፍ አወቃቀር ትስስር ........ 20
2.4. የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችና አንብቦ መረዳት ........ 21
2.5 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ........ 22
2.6. የአንብቦ መረዳት ሁለንተናዊ ፋይዳ፤ ........ 23
2.7 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........ 27
2.7.1 የሀገር ውስጥ ጽሁፎች ቅኝት ........ 27
2.7.2. የውጭ አገር ጽሁፎች ቅኝት ........ 30
ምዕራፍ ሶስት ........ 32
የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ........ 32

3.1 የጥናቱ ስልት ........................................................................................................ 32
3.2. የጥናቱ አካላይ ........................................................................................................ 33
3.3.የናሙና አመራረጥ ስልት ........................................................................................... 33
3.4 የመረጃ ምንጮች ........................................................................................................ 34
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ................................................................................. 34
3.5.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች (Pertest and Posttest)......................................... 34
3.5.2 የጽሁፍ መጠይቅ ........................................................................................................ 36
3.6. የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥና አዘገጃጀት ....................................................... 37
3.6.1 የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ ........................................................................... 37
3.6.2.የመልመጃዎች አዘገጃጀት ........................................................................................ 38
3.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ .............................................................................................. 39
ምዕራፍ አራት ............................................................................................................... 40
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ .......................................................................... 40
4.1.የጥናቱ ተሳታፊዎች ግለ ታሪክ መግለጫ ..................................................................... 40
4.1.1 ለጥናቱ ተሳታፊዎች የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች ......................................................... 41
4.1.2 የተሳታፊዎች ዳራ መገለጫ ........................................................................................ 41
4.1.3 ከቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ከሙከራናከቁጥጥርቡድኖች የተገኘ የፈተና ውጤት ትንተና ቡድኖች በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ ........................... 42
4.1.4 ከቁጥጥር ቡድንና ከሙከራ ቡድን በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ከተሳታፊዎች የተገኘ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና ........................................................................ 48
4.2. የውጤት ማብራሪያ ................................................................................................... 69
ምዕራፍ አምስት ............................................................................................................. 74
ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሐሳብ .................................................................. 74
5.1.ማጠቃለያ .................................................................................................................. 74
5.2. መደምደሚያ .............................................................................................................. 74
5.3. የመፍትሄ ሀሳብ ......................................................................................................... 75
ዋቢ መጻህፍት ................................................................................................................ 77
አባሪዎች ......................................................................................................................... i

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ ገጽ

ሠንጠረዥ 4.1 ለተሳታፊዎች የተሰጡ ጠቅላላ የመጠይቅ ብዛት፣የተመለሱ መጠይቆች ብዛትናያልተመለሱ መጠይቆች ብዛት.....41

ሠንጠረዥ 4.2 የተሳታፊዎች ዳራ (በፆታ፣በዕድሜ፣በትምህርት ደረጃ እና በልምድ) .......... 41

ሠንጠረዥ፡4.3 በቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት ትንተና የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ....42

ሠንጠረዥ፡4.4.የቅድመ ትምህርት የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች አማካይ ውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት....43

ሠንጠረዥ፡ 4.5. የሙከራ ቡድን የቅድመና ድህረ ፈተና አመካኝ ውጤት ንፅፅር በጥንድ ንሞና ስታቲስቲክስ.... 44

ሠንጠረዥ፡ 4.6 የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አማካይ ውጤቶች ንፅፅር በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት.... 44

ሠንጠረዥ፡ 4.7 የቁጥጥር ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ንፅፅር በጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስ....45

ሠንጠረዥ፡4.8 የቁጥጥር ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት....46

ሠንጠረዥ፡ 4.9 የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ፈተና ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ.... 46

ሠንጠረዥ፡ 4.10 የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ፈተና ውጤት ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት....47

ሠንጠረዥ፡ 4.11 የሙከራ ቡድኑ (Experimental Group) በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና....49

ሠንጠረዥ፡4.12 የቁጥጥር ቡድን (Control Group) የቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና ....53

ሠንጠረዥ፡ 4.13 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖ ቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ ....56

ሠንጠረዥ፡ 4.14 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ....56

ሠንጠረዥ፡4.15 የሙከራ ቡድን (Experimental Group) የድኅረ ትምህርት ፈተና
የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና………………………………………….57
ሠንጠረዥ፡4.16 የሙከራ ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት
በጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስ………………………………………………….62
ሠንጠረዥ፡4.17 ሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት
በጥንድ ንሙናቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ……………………………………...63
ሠንጠረዥ 4፡18 የቁጥጥር ቡድን (control Group) የድኅረ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ...... 63
ሠንጠረዥ 4.19 የቁጥጥር ቡድን የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት
በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ ...................................................... 66
ሠንጠረዥ፡ 4.20 የቁጥጥር ቡድን ቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በጥንድ
ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ ..................................................................... 67
ሠንጠረዥ፡ 4.21የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች በድህረ ትምህርት
ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ…………67
ሠንጠረዥ፡4.22 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ከጽሁፍ መጠይቅ
የተገኘ ውጤት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ……………………….68

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ረቂቅ በሆነ መንገድ ሰዎችን የሚያግባባ፣በዘፈቀደ የተፈጠረ የሰው ልጆች የሚጠቀሙበት የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ከዚህም የተነሳ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብና መጻፍ መካከል ማንበብ የሌሎችን ሀሳብ ለመረዳት ከማዳመጥ ቀጥሎ የሚመጣ የሰው ልጅ የሌሎችን ሐሳብ ለመጋራት የሚገለገልበት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ንባብ ማለት በጣም ሰፊ ትርጉም ያለው የማንበብና የመፃፍ አንዱ አካል ነው፡፡ማንበብ ሲባል ከማንበብ ባሻገር መፃፍን፣መናገርን እና ማዳመጥን አካቶ የሚይዝ ሲሆን፣የሚያነቡትን ጽሁፍ በጥልቀት ማየትን፣መለየትን፣ተገቢ የሆነ ትንታኔ መስጠትንና ክሂል ማዳበርን ያካትታል፡፡በአጠቃላይ ንባብ ለሚነበበው ጽሁፍ ትኩረት መስጠትን፣ ማስታወስን፣የቋንቋ ችሎታን፣የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ያለው በርካታ አእምሮአዊ ተግባራትን አቀናጅቶ የያዘ ክሂል ነው፡፡(Read Two ፕሮጀክት ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የተሻሻለው የአፍ መፈቻ ቋንቋ ማስተማሪያ ማንዋል፣2010)፡፡

ንበብ መቻል ማንኛውንም ትምህርት ለመማር መሠረት ሲሆን፣በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ማንበብ የቻለ ሰው ለወደፊት ትምህርትና የህይወት ስኬት አይነተኛ ሚና እንዳለው የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡በአሁኑ ጊዜ በኣለማች ላይ ከ250 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የታዳጊ ሀገራት ሕፃናት በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቆይታቸው ውስጥ መሰረታዊ ቃላትን የማንበብ ችሎታ ሳይኖራቸው ወደ ሁለተኛው እርከን እንደሚያልፉ የዩኒሰኮ ጥናት ያመለክታል፡፡በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከንና ሁለተኛ እርከን ቆይታቸው ማንበብን በአግባቡ ያልቻሉ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት እርከኖቻቸው የተወሳሰበ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡በተጨማሪም ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ለመረዳት ያላቸው የንባብ ክሂል በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ አንዳንዶችም ይህን ማድረግ ባለመቻላቸው ትምርቱንም የሚያቋርጡበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡(የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የንባብ ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ትምህርት ሚኒስተር፣(2009)፡፡

እ.ኤ.አ በ2010 በሀገራችን በስምንት ክልሎች በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ላይ የተካሄደ የንባብ ክሂል ግምገማ (Early Grade Reading Assessmente) ውጤት እንደሚያሳየው ጥናቱ በተደረገባቸው ክልሎች ከሚገኙ 2ኛ እና 3ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ተማሪዎች መካከል ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑ ህፃናት አንብቦ መረዳት የማይችሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡እንዲሁም በደረጃው መፃፍ የሚገባቸውን መጻፍ እንደማይችሉ ተመልክቷል፡፡

የማንበብ ችሎታ በጥቅሉ ሲታይ አንድ ሰው ሊኖሩት ከሚገቡ አስፈላጊ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ማንበብ በጽሁፍ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ለማግኘት ዋና መሳሪያ ነው፡፡አንብቦ መረዳት የሚችል ሰው ችሎታውን ለማዳበርና አእምሮውን በማዘዝ የአስተሳሰብ አድማሱን ለማስፋት ዕድል አለው፡፡በዚህ መነሻነት ማንበብ በመማር ሂደት ውስጥ ዋና ተግባር መሆኑን መገንዘብ እንደሚቻልና፣ይህ ሲሆንም የማንበብ ፍላጎት እነደሚነሳሳ አጥኚዎች ይናገራሉ፡፡

የማንበብ ችሎታን ማዳበር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያካሂዱት የንባብ ተግባራዊ ልምምድ ባሻገር በቀሪው ህይወታቸው የሚጠቀሙበት መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያሻል፡፡የተማሪዎች የንባብ ችሎታ ግብ መማሪያ ክፍል መሆን የለበትም፤ይልቁንም ከትምህርት ቤት ባሻገር ያለ ህይወታቸውን ግብ ያደረገ መሆን አለበት በድሉ፣ (2007)፡፡

መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪዎች በሚያቀርቡበት ጊዜ የተለያየ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ተጠቅመዋል፤እየተጠቀሙም ይገኛሉ፡፡ለነዚህ ስነ-ዘዴዎች መከሰት ምክንያቶቹም በየጊዜው ስለ ትምህርት ምንነትና ስለ ማስተማሪያ ዘዴዎች ያለው ፍልስፍናና ዕውቀት፣የሳይንስና የቴክኖሎጂ እድገትን ተከትሎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀያየረ መምጣትና ትምህርቱም የታለመለትን ግብ ማለትም የሚፈለገውን የባህርይ ለውጥ መምጣት አለመምጥቱን ከሚፈትሹ ጥናቶች በመነሳት ነው፡፡

ንባብ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ መሰረታዊ ክሂሎት ሲሆን፣ የሰው ልጅ ስብዕናውን የሚቀርጽበት፣የማንነቱና የምንነቱ መገለጫ የሆኑትን ባህላዊ፣ታሪካዊ ቅርጾችና ዕሴቶች እንዳይጠፉ ለቀጣዩ ትውልድ ጠብቆ የሚያቆይበትና የሚያስተላልፍበት አይነተኛ መሳሪያም ነው፡፡ማንበብ የማይችል ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ አካባቢውን የማያውቅና የመግለጽ ብቃቱ በማዳመጥና በማየት

ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ለማንኛውም የፈጠራም ሆነ የእውናዊ ጽሁፍ ዕውቀት እንግዳና ባይተዋር ይሆናል፡፡ስለ ህይወትና ስለ ተፈጥሮ ፤አካባባዊና ዓለም አቀፍ ሁነቶች ያለው ግንዛቤ ውስንና የተዛባ ይሆናል፡፡

የዳበረ የንባብ ልምድ በቋንቋ የመጠቀም ብቃታቸውን ከማሳደጉም በላይ ሂሳዊ አስተሳሰብና ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡የዳበረ የንባብ ልምድ የሌሎችን ሃሳብና ስሜት በቀላሉ ለመረዳትና ከማንኛውም አቅጣጫ ለሚሰነዘሩ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየቶች ምክንያታዊና በሳል ፤ቁጥብና ገላጭ በሆኑ ቃላት ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችል ብቃትና ክህሎት ያጎናጽፋል፡፡ንባብ በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረትን ሰብስቦ የማሰብና የማሰላሰል ጠቃሚ ልምድና ብቃትን ያጎናጽፋል፡፡ታላላቅ ሳይንቲስቶችና ኢንጂነሮች፤ስመጥር ደራሲያን፤ጸሓፊ ተውኔቶች፤ሰዓሊያን፤ገጣሚያንና ባለቅኔዎች፤ወዘተ የሚፈጠሩት በዳበረ የንባብ ልምድ ነው፡፡(የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የንባብ ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ትምህርት ሚኒስተር፤(2009)፡፡የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም ተማሪዎች በምንባብ ውሰጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን ቢማሩ አንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ማጎልበት ማስቻል አለማስቻሉን መፈተሽ ነው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂልን ማስተማር መምህራን ሲያለማምዱ ከሚገጥማቸው አንዱ የአንብቦ መረዳት ችግር የጽሑፍ አወቃቀርን ብልሃቶች ያለመጠቀም ችግር እንደሆነ ለማወቅ ወይም ለማረጋገጥ መፈተሽ አስፈለጊ ነው፡፡በመሆኑም በባሶ መሰናዶ እና አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ተዛምዶ ለመለየት ለተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን ማስተማር እና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ምን ያህል አስተዋጾኦ ያደርጋል፤የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ጥናቱ ተገቢ በመሆኑ የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ሆኗል፡፡

የጽሑፍ አወቃቀር (text structure) ጥናት የዲስኩር ንድፈሀሳብ (Rhetorical structure Theory) መሰረት አድርጎ የተጀመረ ሲሆን ንድፈ ሃሳቡ ሶስት መሰረታዊ ገጽታዎች አሉት፡፡Mann & Thompson (1988) እነሱም፡- በጽሑፍ ውስጥ ያለውን እርከናዊ ወይም

ተዋረዳዊ መዋቅር መለየት፣ በጽሑፍ ክፍሎች መካከል ያለ ዝምድናዎችን በተግባራዊ ስያሜዎች መግለጽና የሀሳብ ዝምድና መፍጠርያ እና መሻጋገርያ ስልቶችንና የሀሳቦች ተዛምዶአዊ ደረጃ መለየት ናቸው፡፡

እንደ Holsgrove (2011) ገለጻ ደግሞ የጽሑፍ መዋቅር ጥናት ቀደምት ከሆኑት የHenderson (1903) Thomlike (1917) እና  Bartlef (1932) የስነልቦና ጥናቶች መነሻ አድርጓል፡፡በተጨማሪም በስነልሳን ጥናቶች Fill More ፣(1968) ፣Hougrove (2011) እነደጠቀሱት ስለ ሀተታ መዋቅር  ከተደረጉት ፍተሻዎች  ፅንሰ ሀሳቦች ወስዷል፡፡ከዚህም ሌላ መዋቅራውያን ድህረ መዋቅራውያን ስለትርጉም ግንባታ ካፈለቋቸው ፅንሰ ሀሳቦች በርካታ መነሻዎችን አግኝተዋል፡፡በተለይ ደግሞ ቀደምት የማንበብ ክሂል ጥናቶችን መዋቅር (structure) ለጽሑፍ መረዳት ያለውን ሚና ለመፈተሽ ብቅ ካሉ አዳዲስ ጥናቶች ጋር በማስተሳሰር በእኩል የስኬማ ንድፈ ሀሳብ በንባብ ውስጥ (Schema Theory in Reading) ለዘርፉ ጥናት ማጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው አሳይቷል፡፡

በስነልሳን ዲስኩር ትንተና የጥናት መስኮች ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶችም የጽሑፍ መዋቅርን ለመተንተን የሚያስችሉ የተሻሉ ዘዴዎችን ማስገኘት ችሏል፡፡እነዚህ የትንተና ዘዴዎች አንድ የጽሑፍ አወቃቀር ለአንብቦ መረዳት ያለውን ሚና መፈተሸ ለፈለጉ የስነልቦና ባለሙያዎች እንደመሳርያ ሆኖ አገልግሏል፡፡በተለይም  Meyer (2011)  Poon, Zool, (2012) እንደጠቀሱት Meyer etal (1980) ከተለያዩ የሙያ ሁኔታዎች ለመረዳት ከፍተኛ እርከናዊ አወቃቀሮች ላይ በማተኮራቸው የተነሳ እንደ ምክንያትና ውጤት ማወዳደርና ማነጻጸር ፣ችግርና መፍትሄ ያሉት የጽሑፍ ውቅሮች ከገላጭ ውቅሮች የበለጠ ለመማርና ለማስታወስ አጋዥ እንደሆኑ አስተያየቶችን መስጠት ችለው ነበር፡፡ተናጥላዊ የሆነ ዐረፍተ ነገሮችን ከማጥናት ይልቅ ጽሑፉ እንዴት ተገነባ ወይም ሐሳቦቹ እንዴት ተዋቀሩ ከሚለው ጋር በእጅጉ ስለሚዛመድ ጽሁፋዊ ትርጉምን ለመረዳት መሰረት ሆኗል፡፡

ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ሲገቡ ሰፊ ይዘት ያላቸው የጽሁፍ ውቅር ምንባቦች በብዛት ይገጥሟቸዋል፡፡ምንባቦቹ ከይዘታቸው መለያየት በተጨማሪ በተለያየ መንገድ የተዋቀሩ የጽሁፍ ውቅር ብልሃቶች ስለሚገጥማቸው የሚያነቡት ጽሁፍ ሐሳብ ለመረዳት እነዚህን የጽሁፍ አወቃቀሮች መገንዘብ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግላቸው (Villanueva & Debat (2012) ገልጸዋል፡፡

በርካታ የጽሁፍ አወቃቀር በልሃቶች ቢኖሩም የተለመዱትና ዋና ዋናዎቹ የምክንያትና ውጤት፣የችግርና መፍትሄ፣የገለፃ፣የሂደት፣የማወዳደርና ማነፃፀር ብልሃቶች ናቸው፡፡ በምክንያትና ውጤት የሚቀርብ የጽሁፍ አደረጃጀት በምክንያትና ውጤቶች መካከል የሚኖርን ተጠይቃዊ ዝምድና ይተነተናል፡፡ማረው(2005) በምክንያትና ውጤት የሃሳብ አደረጃጀትን ሲገልጹ፣አራት ዓይነት የምክንያትና ውጤት የሃሳብ ተዛምዶ ይኖራሉ፤ እነሱም፡-ነጠላ ምክንያት ነጠላ ውጤት ሊወልድ ይችላል፣ነጠላ ምክንያት በርካታ ውጤቶችን ሊወልድ ይችላል፣በርካታ ምክንያቶች ነጠላ ውጤት ለወልዱ ይችላሉ፣በርካታ ምክንያቶች በርካታ ውጤቶችን ሊወልዱ ይችላሉ፡፡በዚህ መሰረት በምክንያትና ውጤት የሚደራጅ ሓሳብ በዝግ ወይም በተከታታይ ቅርፅ ሊዋቀር ይችላል በማለት ገልፀዋል፡፡ በምክንያትና ውጤት የሚደራጅ ሓሳብ ለሃሳብ ትስስር የሚያግዙ እንደ ምክንያቱ፣ ስለዚህ፣ከዚህ የበለጠ፣የመጀመሪያው ምክንያት፣ሁለተኛው ምክንያት፣ወዘተ አያያዥ እና መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ይጠቀማል፡፡

የማወዳደርና ማንጻጸር የጽሁፍ ውቅር ብልሃት የሚባለው ደግሞ አንድ ፀሃፊ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች፣ቦታዎች፣ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ያላቸውን ተመሳስሎ አልያም ልዩነት ወይም ተመሳስሎና ልዩነት በመጥቀስ ዋናውን ሓሳብ የሚብራራበት ዘዴ ነው፡፡ በእየዕለቱ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ፣ስንናገርም ሆነ ስንጽፍ በማወዳደርና ማነጻጽር ብልሃት እንጠቀማለን፡፡ማወዳደርና ማነጻጽር ስልትን ስንጠቀም ከዚህ ይልቅ፣ በሌላ በኩል፣ ከዚህ የበለጠ፣ ነገር ግን፣በተመሳሳይ፣ሲነፃፀር፣ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ወዘተ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ይጠቀማል፡፡

ገለጻ ሌላው የጽሁፍ አወቃቀር ሰልት ሲሆን፣ምስል ከሳች ቃላትና ዘይቤዎችን በመጠቀም የአንድን ሰው፣ሃሳብ፣ጉዳይ፣ወዘተ ማንነት/ምንነት/ ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚገለጽበት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ነው፡፡

ቀጣዩ የጽሁፍ አወቃቀር ስልት ችግርና መፍትሄ ሲሆን፣የዚህ አቀራረብ ደግሞ ችግሩን ነቅሶ በማውጣት፣ችግሩ እንዴት ሊፈታ እንደሚችል ሓሳብ የሚቀርብበት፣ችግሩን ዘርዝሮ የመፍትሄ ሓሳብ የሚያስቀምጥ ነው፡፡በሌላ በኩል ችግርና መፍትሄ የሐሳብ ትስስር በሚዋቀርበት ጊዜ ስለሆነ፣ይህንን ለማድረግ፣ምክንያቱም፣ከዚህም ሌላ፣የሆነ ሆኖ፣ምንም እንኳን፣ወዘተ ያሉ ቃላትና ሀረጋት ይጠቀማል፡፡

የሂደትና የአሰራር ስልት ሌላው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ነው፡፡የሂደትና አሰራር አፃፃፍ ስልት ከአስረጅ ጽሁፎች አንዱ ነው፡፡ይህ ስልት አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ፣እንዴት እንደሚሰራ የሚገለጽበት ነው፡፡ትንተናውም በጊዜና በቦታ ወይም በአፈጻጸም ቅደም ተከተል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡አጠቃላይ አላማው፣ለመግለጽ የተፈለገውን ጉዳይ የሚያልፍባቸውን ደረጃዎችና ሂደቶች በቅደም ተከተል ዘርዝሮ ማቅረብ ነው፡፡ይህን የጽሁፍ አደረጃጀት በምንጠቀምበት ጊዜ የሚከተሉትን አያያዥ ወይም መሻጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ይጠቀማል፡፡ እነሱም፡-ከዚህ በፊት፣ቀጥሎም፣እስከ፣ከዚህ በመቀጠል፣ከዚህ በኋላ፣መጀመሪያ፣በተከታታይ ፣በመጨረሻም፣ወዘተ ናቸው፡፡

በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን ማስተማር ሓሳብን በቀላሉ ለመረዳት፣ሓሳብን ለመተንተን፣ሐሳብን ለማደራጀት፣የጽሁፉን መልዕክት ለማስታዎስ (ላለመርሳት)፣ጽሁፍ በምንጽፍበት ጊዜ ሐሳብ ለማደራጀት፣የጽሁፍ አወቃቀርን ማወቅ ያግዛል፡፡የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን መረዳት አንብቦ መረዳትን እንደሚያጎለብት ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት አቅም የበለጠ ለማጎልበትና ውጤታማ ለማድረግ የሚቻለው በክፍል ውስጥ የሚሰሩ መልመጃዎችን በተለያዩ ተግባራት ሲቀናጁ ነው (Hadile፣(2003)፡፡ይህም ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ ተጠቅመው ስለ አነበቡት ጽሁፍ የማስተወስ ችሎታ እንዲኖራቸው፣ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን እንዲረዱና ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እንዲያይዙ ይረዳቸዋል Kevan & Moeruse፣(2009)፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረትም ተማሪዎችን በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ማጎልበት ያስችል እንደሆንና እንዳልሆነ በመመርመር እና የጽሁፍ አደረጃጀትና አወቃቀር ብልሃትን በመረዳት የጽሁፍ ችሎታቸውን ማሳደግ አለማሳደጉን በመፈተሽ ምላሽ ለመስጠት የሚደረግ ጥናት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

ተማሪዎች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ፣ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሳይኖራቸው፣የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡Dymock (2005) በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በርካታ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ደካማ ነው፡፡የዳበረ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከሌላቸው ደግሞ የሚያነቡትን ምንባብ ይዘት በሰፋትና በጥልቀት እንዳይረዱት ከማድረጉም በላይ በትምህርት ውጤታቸው ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡

የማንበብ ክሂል በትምህርት ቤት ውስጥ ለአካዳሚያዊ ስኬት ወሳኝ ከመሆን አልፎ በተማሪዎች የአስተሳሰብ ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያለው እና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ውጤታማ እንዲሆን የሚረዳ መሆኑ ታውቋል፡

ንባብ በክፍል ውስጥ ማስተማር ሲባል የቃላትን አነባበብ፣ማለትም ቃላትን በተገቢው ድምጸት ወይም አገላለፅ ማንበብን፣በትክክልና በተገቢው ፍጥነት ማንበብን፣የተዋጣለት የንግግርና የሃሳብ አገላለጽን፣ሓሳብን ከጽሁፍ እንዲረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ሊያጠቃልል እንደሚችል (Nuttall፣1982) ይገልጻሉ፡፡በዚህም ውስብስብ ባህሪው የተነሳ ይመስላል ንባብ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንዳይኖረው ያደረገው በማለት Tesfaye (2006፡6)፣Pertetti፣(1985) የተባለን ፀሐፊን በመጠቀስ የገለጹት፡፡ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹን ብያኔዎች መሰረት በማድረግ Harmer፣ (1991) ‹‹ንባብ በአይንና በአእምሮ የነቃ እንቅስቃሴ የሚከወን ተግባር ሲሆን፣አይን ከጽሁፍ መልዕክትን ይቀበላል፤አእምሮ ደግሞ የተቀበለውን መልዕክት ከጥቅም ላይ ያውለዋል በማለት ይገልጹታል፡፡››ከዚህ በያኔ እንደምንረዳው ንባብ ማለት የተጻፈን መመልከት ወይም ጽሁፍ በትክክልና በፍጥነት ማንበብ ሳይሆን ሳይሆን ያነበቡትን መረዳት ዋነኛው ተግባር እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ለዚህም ይመስላል Grellet (1981) ‹‹ከንባብ ጠቀሜታዎች መካከል መረጃን ማግኘት እና መዝናናት ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች ቢሆኑም፣የሚነበበውን ነገር መገንዘብ ግን የንባብ ትልቁ ጉዳይ ነው፡፡››በማለት ይገልጹታል፡፡

ከኪሂሉ አስፈላጊነት አኳያም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን እንዴት መማር አለባቸው? ስኬታማ የአንብቦ መረዳት ትምህርትን እንዴት ማቅረብ ይቻላል? የሚሉት ጥያቄዎች በየዘመኑ የሚነሱ ከፍተኛ ችግሮች ሆነው ይገኛሉ፡፡አንብቦ መረዳት አስቸጋሪ የሚሆነው የጽሁፍ ዓላማ እና ይዘት፣ የጽሁፍ ብልሓትና የቋንቋ አላባዎችን በጥምረት በአንድ ላይ በመተግበር የሚከወን ውስብስብ ክሂል ከመሆኑ የመነጨ ነው፡፡Chun፣(2000) Dorkehandra (2010) እንደጠቀሱት፡፡

የዚህ ጥናት አጥኚ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አማርኛ ቋንቋን ለሰላሳ ዓመታት ያህል አስተምሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ የአንብቦ መረዳት ችግር መሆኑን መገንዘብ ችሏል፡፡በርካታ

ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ የቻለው ተማሪዎች በየጊዜው ከሚሰሯቸው የክፍል ውስጥ መልመጃዎች፣ የቤት ስራዎች፣ሙከራዎች፣የሰሞን ስራዎች እና የፈተናዎች ውጤት ግምገማ ላይ በመመስረት ያለባቸውን ክፍተት በመመልከቱ ነው፡፡

ሌላው ተማሪዎች እንድን ምንባብ ሲያነቡ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ቀዳሚው ለሀሳቦች አደረጃጀት ትኩረት አለመስጠት፣ለማንበብ ተግብር ትኩረት አለመስጠት፣የማንበብ ተነሳሽነት ማጣት እንደሆነ Books & Dansereau (1983) ያስረዳሉ፡፡በተጨማሪም ጠለቅ ያለ ወይም አመራማሪ መልስ የሚሹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲገጥማቸው በትክክል አለመመለስ ወይም ወደጎን ገሸሽ አድርጎ ማለፍ ወይም ወደሌላ ተግባር መሸጋገር የመሳሰሉትን ሁኔታዎች በማጤን ነው::

በተጨማሪም አጥኚው የጽሁፍ አወቃቀር ብለልሃቶች ጥናት በኢትዮጵያ አውድ የተሰጠውን ትኩረት ለማወቅ በአማርኛ ቋንቋ በማንበብ ክሂል ላይ የተካሄዱ ጠቶችን ለመመልከት ሞክሯል፡፡ከነዚህ ጥናቶች የተወሰኑ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ በመዳሰስ ማሰተዋል፣ (1989) ዓ.ም.፣ተስፋዬ፣(2001) ዓ.ም.፣ የተወሰኑት ደግሞ የመማሪያ መጻህፍትን ተነባቢነት ወይም የማስተማሪያ መጻህፍትን ባህሪያት በመፈተሽ ጌታቸው፣(1986) ዓ.ም. ፣ታዬ፣(1999) ዓ.ም. ላይ ትኩረት በመስጠት ለማንበብ ችግሮች ማቃለያ የመፍትሄ አስተያየቶችን የቀረቡ ቢሆንም ፣በአንብቦ መረዳት ብልሓቶች አተገባበር ላይ ያተኮሩ አለመሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡

በእግሩ ዙሪያ ስነትምህርታዊ መፍትሄዎቸን በመፈለግ ላይ ያተኮሩትም ቢሆኑ እንግዳ ፣ (1992) ዓ.ም.፣ጌታቸው፣1991ዓ.ም.፣ግሩም፣(2003) ዓ.ም. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ሞዴሎችን ተግባራዊነት በመፈተሽ ላያ ያተኮሩ እንጂ የአንብቦ መረዳት ብልሓቶችን በተለያም የጽሁፍ አወቃቀር ብልሓተችን ተግበራዊነት የፈተሸ አልነበሩም፡፡ አጥኚው እስከሚያውቀው ድረስ በጽሁፍ አወቃቀር ላይ የተሰሩ የአገር ውስጥ ጥናቶች የጥሩነሽ ፣(2005) ዓ.ም.እና የመሪነሽ ፣(2009›) ዓ.ም. የጥሩነሽ ሆነ የመሪነሽ ስራዎች በአንድ ቡድን ላይ በሁለት የጽሁፍ ውቅሮች ብቻ የተሰሩ ስራዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጥናቶች ቢሆኑ በጽሁፍ አወቃቀር እውቀት ላይ በማተኮራቸው ውጭ ማንበብን በጽሁፍ አወቃቀር

ብልሃቶች በግልጽ ማስተማር ላይ ያተኮሩ አይደሉም፡፡በመሆኑም በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ የብልሃቶችን ውጤታማነት መፈተሸ በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ እየገጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት እንደ አንድ ስነ ትምህርታዊ አቀራረብ አማራጩ ሆኖ ያገለግል እንደሆነ መረጃ ይሰጣል፡፡ ስነዚህም አጥኚው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል በማስተማር አውድ በመተግበር ውጤታማነታቸውን መፈተሸ አስፈላጊ ሆኖ አግኝታል፡፡በአጠቃላይ አጥኝው በዚህ ዕርሰ ጉዳይ ላይ ጥናቱን ለመስራት የተነሳሳው ከላይ የተጠቀሱትን ንድፈ ሐሳባዊ፣ ምርምራዊናተሞክሯዊ ክፍተቶች መኖራቸውን በመገንዘቡ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በጽሁፍ ውሰጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን በብልሃት አልባ (በተዘውታሪው) አንበቦ መረዳትን ማስተማሪያ ዘዴ እና በጽሁፍ ውቅር ብልሃቶች አቀራረቦች ሁለቱ ቡድኖች ከተማሩ በኋላ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡

- የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤታቸው ላይ ልዩነት ይታይባቸዋል?ልዩነት ከታየ የተሸለ ውጤት ያሳየው የትኛው ቡድን ነው ?
- ተማሪዎች በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች እና በብልሃት አልባ (በተዘውታሪው) የማንበብ ትምህርት አቀራረቦች ከተማሩ በኋላ በአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ላይ ልዩነት ይታይባቸዋል? ልዩነት ከታየ የተሸለ አንብቦ የመረዳት ውጤት ያስመዘገበው የትኛው ቡድን ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወራና ወረዳ በባሶ መሰናዶ እና አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተፅዕኖ መፈተሸ ነው፡፡ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይዟል፡፡

- በጽሁፍ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የሚያመጣውን ልዩነት መፈተሽ፣
- በጽሁፍ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን መማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚኖረው ከሆነ፣አንብቦ በመረዳት ላይ መደንገግ አለመደንገጉን መፈተሽ፣

## 1.5 የጥናቱ መላምት

ይህ ጥናታዊ ስራ የሚከተለው የአጠናን ዘዴ መጠናዊ ዘዴ ስለሆነ መላምት ማስቀመጥ ግድ ይለዋል፡ መጠናዊ መላምት ደግሞ የሚለኩ ተለዋዋጮችና የሚተነተኑ መረጃዎችን ስለሚይዝ ጥናቱ የሚከተለውን መላምት በማስቀመጥ ውጤቱን ፈትሸዋል፡፡

- አንብቦ መረዳትን በጽሁፍ አወቃቀር ብለሃቶች የሚማሩ ተማረዎች በተዘውታሪው የማስተማሪያ ዘዴ ከሚማሩት የበለጠ  አማካይ ውጤት ያመጣሉ?

## 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

በዚህ ጥናት በምንባብ ውሰጥ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን መማር የተማሪዎችን አንብቡ የመረዳት ችሎታ አሻሽሎ በመገኘቱ፣ ስለዚህ ግኝቱ የሚከተሉት ስነ ትምህርታዊ፣ ምረምራዊና ንድፈ ሐሳበዊ ጠቀሜታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

ስለ ትምህርታዊ ፋይዳው ለተማሪዎች የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች በአንብቦ መረዳት ክዋኔ ሂደት መጠቀም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ የሚያስችል ሰልጠና እንዲያገኙ ያግዛል፤

- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች ለአንብቦ መረዳት መኀልበት ያላቸው ፋይዳ በመገንዘብ በማንበብ ክዋኔ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀሮችን እንዴት መተገበር እንዳለባቸው ፣ ለጠቃሚ መረጃዎች እንዴት ትኩረታቸውን እንደሚሰጡ ፣ ሐሳብን በቀላሉ መልሶ ለማፍለቅ በብልሃቶች እየታገዙ መረጃዎችን እንዴት ማደራጀት እንደሚችሉ ለማስተማርም የሚያስችል ግንዛቤ ያስገኛል፤
- በተጨማሪ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሁፍ አወቃቀር ብላሃቶችን በግልጽ ማስተማርን መሰረት ያደረገ አንብቦ የመረዳት ክሂል አቀራረብ በመከተል

የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያሻሽሉበትን አማራጮች ለማሳየት ይረዳቸዋል፤

- ምርምራዊ ፋይዳው ደግሞ ሌሎች ተመራማሪዎች በቀሩት ሌሎች የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ላይ ለሚያደርጓቸውን ጥናቶች መነሻ ሐሳብ ይሆናል፤
- ንድፈ ሐሳባዊ ጠቀሜታው አንብቦ መረዳትን ከማስተማር አንጻር በተለይም አፍልቆታዊ የመማር ንድፈ ሐሳብ (Generative Learning Theory) እና የአሳታፊ ማንበብ ትምህርት ሞዴል (Reading Engagemente-MOodel) አንብቦ መረዳት የተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች መስተጋብር ውጤትመሆኑን የገለጹበት ጽንስ ሐሳብ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂል ትምህርት አውድ ውሰጥ ስላለው ተተግባሪነት ፍንጭ ያሰገኛል፤

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወረና ወረዳ በባሶ መሰናዶ እና አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት በሁለት የ9ኛ የማስተማርያ ክፍሎች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርታችውን በመማር ላይ ባሉ ተማሪዎች የተወሰነ ሆኖ ፣አንደኛው ክፍል የመቆጣጠሪያ ቡድን (Control group) ሌላኛው ቡድን ደግሞ የሙከራው ቡድን (Expetmental group) በማድረግ በምንባብ ውሰጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ መለየት ላይ የተወሰነ ነው፡፡የጥናቱ ትኩረት በተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አመቃቀር ብልሃትን ማስተማር ላይ ብቻ ስለሆነ ሌሎች አንብቦ የመረዳት አለባውያን አይመለከትም፡፡የሚጠናውም ከጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች መካከል በምክንያትና ውጤት (Cause and effect)፣በማወዳደርና ማነፃጸር (Compare and Contrast) ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

## 1.8 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት በሚካሄድበት ሂደት በጥናቱ ላይ የተለያዩ ውስንነቶች አጋጥመዋል፡፡ ዋናውና ትልቁ ችግር የሙከራው ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ የጊዜና የቦታ እጥረት ማጋጠም ሲሆን ፣ምክንያቱም የማጠናከሪያ ትምህርት መሰጫ ክፍሎች በሌሎች መምህራን መያዝ፣

ተማሪዎች ሰዓት አክብረው አለመምጣት ፣ማሰለስ ፣ሌላው ትምርቱን የሚሰጥልኝ መምህር በሌሎች ተግባራት ስለሚጣበብ ትምህርቱ በታቀደለት ጊዜ አለመሰጠቱ ፣በሚሰጥበትም ጊዜ ክፍለ ጊዜውን ባግባቡ ያለመጠቀም ውስንነት አጋጥመው ነበር፡፡ይሁን እንጂ እነዚህን ችግሮች በመደበኛ የመማር ማስተማር ክፍለ ጊዜያት በክፍት ክፍለ ጊዜያት በመስጠት ችግሩን ለመፍታት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቁን በሚሞሉበት ጊዜ መጠይቁን በአግባቡ አለማንበብ እና በግዴለሽነት መለስ መስጠት ፤ፈተናውን በሚፈተኑበት ወቅት ምንባቡን ሙሉ ለሙሉ ሳያነቡ መልስ መስጠት ፣በጽሁፍ መልስ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች በሚመልሱበት ጊዜ ከምንባቡ ውጪ የሆነ የራሳቸውን መልስ መስጠት፣ ማብራሪያ እንዲሰጡ የተጠየቁበትን ጥያቄዎች ማበራሪያውን ሳይሰጡ መመለስ፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ውስንነቶች የተስተዋሉ ቢሆንም በድህረ ትምህርት ፈተና ወቅት ግን ስለ ጥናቱ ጠቀሜታ ተጨማሪ ግንዛቤ በመፍጠርና ክትትል በማድረግ ለማስቀረት ተችላል፡፡

## 1.9. የሙያዊ ቃላትና ሀረጋት ፍች

***አንብቦ መረዳት ችሎታ፡-***የአንድን ጽሁፍ ተራ ሀሳቦች ወይም መልዕክት ከመረዳትና ከመተርጎም ባለፈ ሰፋፊና ጥልቅ ሀሳቦችን ጭምር መርምሮ ማውጣት መቻል ሲሆን፣በዚህ ጥናት ተማሪዎች በአንበቦ መረዳት ፈተናዎች በሚያገኙት ውጤት የተለከ ነው፡፡

***የጽሁፍ አወቃቀር***፡-በጽሁፍ ውሰጥ የጽሁፉ አጠቃላይ መልዕክት በአንድነት የተዋቀረበት ስልት ወይም በጽሁፍ ውሰጥ ያሉ ይዘቶች የተደራጁበት ስልት ሲሆን፣ይህ ጥናት በመክንያትን ውጤት እና በማወዳደር አወቃቀሮች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

***ቅድመ ትምህርት ፈተና***፡-ታሳቢ የተድገው ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት ተማሪዎች ከዚህ በፊት ሰለ ይዘቱ ወይም ስለሚማሩት  ትምህርት ምን ያህል እንደሚያውቁ ነባሩን እውቀታቸውን ወይም ችሎታቸውን ለመለካት የሚሰጥ ፈተና ሲሆን፣በዚህ ጥናት ውሰጥ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመመዘን ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

***ድህረ ትምህርት ፈተና፡-***ተተኳሪው ትምህርት ለተማሪዎች ከተሰጠ  ወይም እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎች ከተማሩት ትምህርት ምን ያህል ግንዛቤ እንዳገኙ ለማወቅ የሚሰጥ የመመዘኛ ስልት ሲሆን፣ ይህም በዚህ ጥናታዊ ስራ ውሰጥ የተማሪዎችን ድህረ በፈተና ውጤት ለመመዘን ተግባራዊ ሆኗል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳቦች

አንብቦ መረዳት ሶስት መሰረታዊ ንድፈ ሃሳቦች እዳሉት አፀደ (Guninning) በመጥቀ1ስ ይገልጻሉ፡፡እነዚህም የአእምሮአዊ ምሰል ንድፈ ሃሳብ (Schema theory) ፣የአእምሮአዊ ሞዴል ንድፈ ሃሳብ (Mental model theory) እና የፕሮፓዚሽን ንድፈ ሃሳብ (Proposition theory) ናቸው፡፡እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ተቃኝተዋል፡፤

**ሀ.የአእምሯዊ ምስል ንድፈ ሃሳቦች፡-**

የአእምሯዊ ምስል ንድፈ ሃሳብ ፣ምስል የመጠቀም ንድፈ ሃሳብ ስለ ቅድመ ንባብ ተግባራት ውጤታማነት ጠንከር ያለ መረጃ ያቀርባል፡፡እነዚህ ተግባራት ለሚነበበው ምንባብ እንደ ማውጫ በመጠቀም ቁልፍ ፅንስ ሓሳቦችን አስቀድሞ ለመገንዘብ ይረዳል፡፡አእምሯዊ ምስል በቅድመ ንባብ ክንውን አንባቢዎች ጽሁፉን በንቃት እንዲያነቡ የሚያነሳሳ መሆኑ ላንብቦ መረዳት ተግባራት መልመጃዎች ያዘጋጃሉ፡፡ተግባራቱንም በተወሰነ ጊዜ እንዲያከናውኗቸው እና በራስ የመተማመናቸው ሁኔታ ስለሚጨምርላቸው በሌሎች ተግባራት የመሳተፍ ፍላጎት ያሳድራል (Casanave፣1988)፡፡ተማሪዎች በቂ የሆነ ልምድና ዳራ የሌላቸው ከሆነ መምህሩ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ቢያንስ የተወሰነ እውቀት እንዲጋሩ ሊያደርጋቸው ይገባል፡፡

የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለማነቃቃት መሞከር በመረዳት ወቅት ነገሮችን ቀለል እንዲል ያደርግላቸዋል (Camish,1992)::አንድ ሰው በምንባብ ውስጥ ስለ አንድ ነገር፣ስም፣ ቦታ፣ሁኔታ፣ድርጊት፣ወዘተ የቀደመና የተደራጀ እውቀት ሊኖረው ስለሚችል የአእምሯዊ ምስል ንድፈ ሃሳብም በአንባቢና በጽሁፍ መካከል ባለው ተራክቦ ላይ ያተኩራል (Gunning፣2006)፡፡በተጨማሪ አእምሯዊ ምስል ከአንባቢ አንባቢ ይለያያል፡፡ማለትም ሰፋ ባለ መልኩ ሊታይ አለበለዛም ሊጠብ ይችላል፡፡ለምሳሌ አንድ ሰው ስለ አጠቃላይ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ያለው አእምረዋዊ ምስልና ስለ አውሎ ነፋስ ብቻ ያለው ምስል በእጅጉ የተለያየ ነው፡፡እያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ምስልም በተለያየ መንገድና ደረጃ ከአንባቢ አእምሮ ውስጥ ተቀርጾ የተቀመጠበት መንገድ አለው፡፡ በመሆኑም አንባቢ አንድን ምንባብ

አንብቦ ለመረዳት የሚደረገውን ጥረት ቀድሞ የተቀረጸውን ነባር አእምሮሯዊ ምስል አዲስ ከሚያነበው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያገናዝባል፣ያወዳድራል፣ያነጻጽራል፡፡

በአጠቃላይ ከብያኔው መረዳት እንደሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ምንባቡን ሳያነቡ ርዕሱን ብቻ በማየት ከቅድመ እውቀታቸው በመነሳት ዝርዝር ሃሳቦችን የመተንበይ ፣ቅደም ተከተልን የሚጠይቁ ፣ወደ ምንባቡ ትኩረታቸውን ለማድረግ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ተገቢነት ያለው ነው፡፡

**ለ.የአእምሯዊ ሞዴል ንድፈሃሳብ፡-**

ይህ ንድፈ ሃሳብ አንድ አንባቢ አዲስ በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባለው መረጃ አማካይነት በአእምሮው የሚቀርጸውን ስዕል የሚመለከት ነው፡፡አእምሯዊ ስዕል የሚፈጠርበትን መንገድ (Gunning,1996) ሲገልጽ ፣አንድ ልቦለድ በማንበብ ላይ ያለ ተማሪ የልቦለዱ መሪ ገፀባህርይ አጠቃላይ ሁኔታ ፣ የአለባበስ ፣ የአነጋገር ባህሪ ፣ ወዘተ. በአእምሮው ውስጥ በስዕል መልክ ይቀርፃል፡፡ይህ ስዕልም ገፀባህሪው ፀባዩን በቀየረ ጊዜ አብሮ እተቀያየረ እስከ መጨረሳ የሚቀጥል ነው፡፡ይህ ሞዴል ተቀያያርና ወቅታዊ በመሆኑ አንባቢ አዳዲስ ነገሮችን ከሚያነባቸው የጽሁፍ ባህሪያትና ይዘት አንጻር እየተረዳ እንዲሄድ የሚያደርግ ነው፡፡እንደ Perkine (1991) ገለፃ ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሁፍ መሰረት አድርገው የሚስሉት አእምሯዊ ሞዴል የተለያየ ሆኖ መገኘቱ አንዳንድ ጊዜ በንድፈ ሃሳቡ ላይ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ይሁን እንጂ የመምህራን ጣልቃ ገብነት አስተዋጽኦ እንዳለው ይመክራሉ፡፡በአእምሯዊ ሞዴል ንድፈ ሃሳብ ተማሪዎች አንበበው የተረዱትን ነገር ትክክክኛ ስዕል/ምስል/መቅረጽ ካልቻሉ ክፍተት የመጣው በተማሪዎች የዕውቀት መራራቅ ይሆናል ተብሎ ተገምቷል፡፡ ለዚህም መፍትሄው መምህራን ጣልቅ በመግባት ይህንን ክፍተት መሙላት እንደሚችሉ ነው የተጠቆመው፡፡ለምሳሌ አንድ ተማሪ ሰላነበበው ጉዳይ ትክክለኛ አእምሯዊ ሞዴል/ምስል/ ከሌለው በጥያቄ በማመሳሰል፣በውይይት፣በስዕላዊ ማብራሪያ እና በሌሎችም መንገዶች ተማሪዎችን ወደተፈላጊው አእምሯዊ ሞዴል ማምጣት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከብያኔው እንደምንረዳው የአንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ከአነበቡት ምንባብ የተረዱትን እንዲተርኩ የሚያስችል ገላጭ ወይም ስዕላዊ

ድርሰቶችን እንዲፅፉ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ማዳበር እንደሚቻል የሰጡት ትንታኔ ያስረዳል፡፡

**ሐ. ስምምነታዊ ንድፈ ሃሳብ (የፕሮፖዜሽን ንድፈሐሳብ)**

የፕሮፖዜሽን ንድፈ ሃሳብ አንባቢ በአንድ ጽሁፍ ላይ የሰፈረ ዋና ሃሳብን ነቅሰው የሚያወጡበት ሁኔታን የሚቃኝ ነው፡፡ዋና ሓሳቡም በተዋረዳዊ አካሄድ መሰረት ቀዳሚ ቦታ ላይ ያለው መሆኑ ይረጋገጣል፡፡በአንብቦ መረዳት ሂደት ላይ በምንባቡ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና ሓሳብ ተማሪዎች ትክክል ለይተው ማውጣት አለማውጣታቸውን የሚጠይቁ መልመጃዎች ከዚህ ንድፈ ሃሳብ ጋር ተገናዝበው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው (Gunning፣1886) ፡፡

ለምሳሌ ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ጎጂ ባህል የሚያወራ ምንባብ ቢኖር ይህንን ምንባብ በትኩረት በማንበብ ጽሁፉ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋና ሃሳብ ምን እንደሆነ መረዳት አለመረዳታቸውን የሚያረጋግጡ ጥያቄዎችን በማካተት የተማሪዎችን የመረዳት ሁኔታ በመለየት ትምህርቱን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ማዛመድ ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከንድፈ ሃሳቡ ትንታኔ እንደምንረዳው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ፣እንዲሁም ከምንባቡ ውስጥ ፍሬ ሓሳብን ነቅሰው እንዲያወጡ የሚያስችሉ እና በምንባቡ ውስጥ ጽሁፉ የተዋቀረበትን ብልሃት እንዲለዩ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ማዳበር እንደሚያስችል ያስገነዝባል፡፡

## 2.2. የጽሑፍ ውቅር ብልሃቶች

የተጻፉ ድርሳናት በዓይነታቸው እና በቁጥራቸው በብዛት በሚገኙበት ዘመናዊው ዓለም ውስጥ ስለማንበብ ያለው ግንዛቤ ሆነ እይታ በጣሙን ተለዋዋጭ ሆኖ ይገኛል፡፡የማንበብ ክሂል በትምህርት ቤት ለአካድሚያዊ ስኬት ወሳኝ ከመሆን አልፎ በተማሪዎች መማር የአስተሳሰብ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያለው እና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ውጤታማ ለማድረግ የሚረዳ መማርያ መሆኑ ታውቋል፡፡Organization for Economic co-opretition and Development ፡OECD (2013)፡፡ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር የተጠቀሰው Programme for International Studies Assessment PISA (2009) ማንበብ የግል ዓላማዎችን ለማሳካት እውቀትንና ብቃትን ለማዳበር በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፊ

ለመሆን በሚያስችል መልኩ የጽሑፋዊ አወቃቀሮችን መረዳት፣መጠቀም፣ፅብረቃ ማቅረብ፣ በትጋት መሳተፍ መቻልን እንደሚያካትቱ የሰጠው ብያኔ ነው፡፡ይህም ማንበብ የእውቀት፣ የክህሎት፣ የብልህቶችና የስሜቶች ቅንጅት ሆኖ ተማሪዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በግላቸውም ሆነ ከማህበረሰቡና ከብጤዎቻቸው መስተጋብር በመፍጠር የሚገነቡት ወይም የሚያሳድጉት ችሎታ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

Gessesses (1999) በዋቢነት የጠቀሷቸው Anderson እንደገለጹት የማንበብ ትምህርት መለካት ያለበት ለአንብቦ መረዳት ፈተና በሚቀርበው ጥያቄ መስፈርት ሳይሆን፣ወደ ውጤቱ ለሚያደርሰው የማንበብ ሂደት አስፈላጊ በሆኑት ብልሃቶች ላይ በማተኮር ነው፡፡አንብቦ ለመረዳት ከሚያስፈልጉ ብልቶች አንዱ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች ይገኙበታል፡፡(Haas & Flower,(1998) Schwaks et al (2013) ተማሪዎች የሚያነቧቸው ምንባቦች ምን መልዕክት አስተለለፉ፣ከሚለው ይዘት አልፈው ጽሁፎች እንዴት ተዋቀሩ? ጽሁፎቹ ምን ተግባር አለቸው?የሚሉትንም ሆነ፣ ፀሀፍት በጽሁፋቸው ማስተላለፍ የፈለጓቸውን ዓላማዎች ለማጋራት ስሜት እንዲያጭርባቸው መፈተሸ የሚያስችላቸው፣ ከመማሪያ መፃህፍት ባለፈ ማንበብን እንዲከውኑ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው (Haas & Flower (1998)፡፡የጽሁፍ ብልሃቶች የመፃህፉን ቁልፍ ሀሳቦች እንደገና ለማፍለቅ፣ ለማስታውስና ለመረዳት እንደ ተቋም ሆነው ያገለግላሉ፡፡ጥቅል (ጥልቅ)መረዳትና ትርጉም ላለው መማር አጋዥ በሆነ መልኩ የጽሁፍ አወቃቀሮችን ተገንዝበው መለየትና መተንተን ብሎም መጠቀም የሚያስችሉ ናቸው፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓለማ ተማሪዎች በማንኛውም መንገድ የዳበረ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ለዚህም ነው አለምና ፅጌ (1997) የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ኣላማዎችን የመዳመጥ፣ የመናገር የማንበብና ፣መጻፍ ክሂሎችን ማጎልበትና የሥነ-ጽሁፍና የስነልሳን መሰረታዊ እውቀቶችን ለማዳበር ነው በማለት የገለጹት፡፡እነዚህም ክሂሎች በክፍል ውስጥ እንዴት መተግበር እንዳለባቸው መርሃ ትምህርት ተዘጋጅቶላቸው በቅንጅትና በተናጥል ይሰጣል፡፡

ንባብንም በክፍል ውስጥ ማስተማር ሲባል የቃላትን አነባበብ ማለትም ቃላትን በትክክልና በተገቢው ድምፀት ማንበብን፣የተዋጣለት የንግግርና የሐሳብ አገላለጽን፣ሀሳብን ከጽሑፍ እንዲረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ሊያጠቃል እንደሚችል Nuttall (1982 ) ይገልጻል፡፡ Harmer (1990) ንባብ በዐይንና በአእምሮ የነቃ እንቅስቃሴ የሚከወን ተግባር ሲሆን ዐይን

ከጹሑፍ መልዕክትን ይቀበላል፤አእምሮም የተቀበለውን መልዕክት ከጥቅም ላይ ያውላል በማለት ገልጸውታል፡፡ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው ንባብ ማለት የተጻፈን ነገር መመልከት ብቻ ሳይሆን ያነበቡትን መረዳት ዋና ተግባር ነው፡፡ለዚህም ነው Grellt (1981) ከንባብ ጠቀሜታዎች መካከል መረጃን ማግኘት እና መዝናናት ዋና ዋና ዓላማዎች ቢሆኑም የሚነበበውን ነገር መገንዘብ ግን የንባብ ትልቁ ጉዳይ ነው በማለት ይገልጸዋል፡፡

ንባብ እንደ ተማሪዎች ክፍል ደረጃና በይዘትና በአቀራረብ ተመጥኖ ሲሰጥ ይታያል፡፡በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት በሚል ንባቡ ይቀርባል፡፡አንብቦ መረዳትን በክፍል ውስጥ ለማስተማር መጀመርያ መምህሩ ቀድሞ ምንባቡን አንብቦ እና እንዴት ማስተማር እና መገንዘብ እንዳለበት (Nutfall (1982) ፣Wallance (1992) ይገልጻሉ፡፡ነገር ግን በአገራችን በተጨባጭ እነዚህ ተግባሮች በተገቢው መንግድ ተከናውነው በስራ ላይ መዋላቸው አጠራጣሪ ነው፡፡ምክንያቱም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአንብቦ መረዳት የንባብ ትምህርቶች አሰጣጥ ብዙውን ጊዜ ችግር ያለበትና ተማሪዎችንም ለጥሩ አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያበቃ እንዳልሆነ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች አሳይተዋል፡፡ማስተዋል (1989)፣ ጌትነት (1998) መዓዛ (1991) ሰዎች መማርን የሚተገብሩት አካባባዊ፣ግለሰባዊ ሁኔታዎችን ባካተተ፣ በአእምሮኣዊ፣ በስሜታዊና በሥነ-ሂወታዊ ክስተቶች መስተጋብራዊ መዋቅር ተጽእኖ ውስጥ ሆነው ነው፡፡(Pajates፣2006) ሆኖም አእምሮኣዊ፣ስሜታዊና ስነ-ህይወታዊ ክስተቶች የሚያመጡት አንፃራዊ ተፅእኖ በተግባራቱና በሁኔቶች ላይ በመሆኑ ምክንያቱ እኩል ጥንካሬ የለውም፡፡አንብቦ መረዳት መማርም መስተጋብራዊና ውስብስብ ሂደት በመሆኑ በስነልሳናዊና በአእምሮአዊ ሁኔታዎች፣ በባህላዊ ሁኔታዎች፣በስሜታዊና በተነሳሽነት ሁኔታዎች ተፅእኖ ይደርስበታል (Baker & Wigfield,1999)፡፡የማንበብ ሂደት በርከት ያሉ የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በንቃት መከወንን ጭምር የሚያካትት ነው (Baker & Boonkt, (2004)፡፡

ከሁሉም ንድፈሃሳቦች የባህሪያዊያን (Behviorism) የመማር ንድፈ ሃሳብ ከአፍልቆታውያን (Generative learning) ንድፈሃሳብ ጋር የጎላ ልዩነት አለው በማለት የSkinner(1999) ማብራሪያ ጠቅሰው Grabowfki (1996) እንዳስረዱትም ሆነ Wiflrock (1991) በመሰረታዊ ልዩነትም የተማሪው ሚና ይታሰባል፤ይህ እሳቤስ ለመማር ምን እንድምታ አለው? በሚለው

ፅንሰ ሀሳብ ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡በአፍልቆታውያን የመማር ንድፈሃሳብ መረጃውን ለመማርም ሆነ ላለመማር ወሳኝ የሆኑት ተማሪዎች ዋና ጉዳይ ሆነው ይታሰባሉ፡፡ከፍላጎት ጀምሮ እስከ ማስታወስ ድረስ ያሉትን ሁሉንም በመማር ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ አእምሮአዊ ሂደቶችን መረዳት የሚያስፈልገው የተማሪዎችን መረጃን የመቀበል ወይም የማዛመድ ሁኔታዎችን የሚደግፉ ተገቢ ተግባራትን ለመምረጥና ለማደራጀት ስለሚያግዝ ነው፡፡ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በንቃትና በትጋት ሃሳቦችን ማዛመድ ይጠበቅባቸዋ፡፡ በባህሪያውያን የመማር ንድፈሃሳብ መስረት ግን ፍዝ የመረጃ ተቀባይ ከመሆን ባሻገር ለመማራቸው የሚጫወተው ሚና የለውም፡፡ስለዚህ የባህሪያውያን የማስተማር ንድፈሃሳብ በአዎንታ ወይም በአሉታ መልሶ ምገባ የሚጠናከር አነቃቂ ተግባርን በመፍጠር ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ከፍተኛ እርከን ያላቸው የሃሳብ ተዛምዶዎች ወይም ቅበላዎች ጠቃሚ ተደርገው አይታዩም፡፡የንድፈ ሃሳቡ አላባዎች ሁኔታዎችን መልመድ፣ምላሽ መስጠት ፣መጋራት፣ማጠንከርና ቀድሞ የታቀደን ጥብቅ አሰራርን የሚከተል ነው፡፡

የተዛምዷውያን (Connectionism) የመማር ንድፈ ሃሳብም ተዛምዶዎችን በማጠናከር ላይ በማተኮሩ ከባህሪያውያን ጋር ተመሳሳይነት አለው (WIttirok,1992,Grahowski,1996) በማለት ጠቅሰዋል፡፡ይሁን እንጂ በተዛምዷውያን የግለሰቦች ትውስታ ትስስር ወሳኝ እንደሆነ ሰለሚያምን ከአፍልቆታውያን ንድፈሃሳብ ጋር ይመሳሰላል፡፡በተዛምዷውያን የግለሰቦች ትውስታ ትስስር የሚገነባው በሀሳቦች መካከል በሚፈጠሩ ተዛምዶዎች ሳይሆን ውጫዊ ተነሳሽነት ባለው ተደጋጋሚ ልምምድ በማጠናከር ማዛመድ ነው፡፡ በአፍልቆታውያን የመማር ንድፈ ሃሳብ ግን መረዳት የሚፈጠረው ውስጣዊ በሆነ ሂደት ስለሆነ ድግግሞሽ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል፡፡በአጭሩ የተዛምዶአውያን መማር ንድፈ ሃሳብ የትውስታ ተዛምዶ ጥናት ሲሆን፣መማርን እንደ ሃሳቦች ዝምድና ወይም ትስስር የሚበይን፣ማሰብም ከአእምሮአዊ ሂደቶች የሚመነጭ፣የማሰብ ደረጃም የጽንስ ሃሳብ ፈጠራ የሚገለጽበት፣የትውስታ ከፊል ንቁ ትስስር መማርን የሚከተል ነው፡፡የንድፈሃሳቡ አላባዎች የአሰላለፍ ትስስሮች የትስስሮችና የሃሳብ ፍሰት ክብደት ናቸው፡፡

የግንባታውያን (Constructivism) የመማር ንድፈ ሃሳብ፣መማርን የሚደግፍ ንድፈ ሃሳብ (Jonassen፣1990፣Garbowski፣1996)ጠቅሰው፡፡ንድፈ ሃሳቡ መማር በአእምሮአዊ፣በልማዳዊ ወይም በማህበራዊ እውነታ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚያመላክቱ የተለያዩ እይታዎች ቢኖሩትም፣ተማሪዎች ጥልቅ መረዳትን ለሚያዳብሩበት ስልት ትኩረት የሚሰጥ ነው

(Abiy፣2005)፡፡ተማሪዎች ጥሩ አፍላቂዎች(Processors)እንዲሆኑ ሰለሚተሰብ ከአፍልቆታዊ መማር ንድፈ ሃሳብ ጋር ያዛምደዋል፡፡ይሁን እንጂ ተጨባጭ እውነታ ስለመኖሩ የሚያሳየው አቋም ፅንፍ የወጣ ያደርገዋል፡፡እንደ (Pearson፣(1993) Sadoski and Pairio (2007) ገለጻም ከጽሁፍ ውቅር ይልቅ አንባቢዎች ወሳኝነት የሚከራከር ንድፈሃሳብ የመማር ንድፈሃሳብ ነው፡፡በአጭሩ የግንባታውያን የመማር ንድፈሃሳብ ትርጉም የመገንባት ጥናት ሲሆን መማር በግለሰብ እንደሚገነባ መረዳት የሚበየንበት፣ማሰብም ከልምዶች የመፈረጅ ግንባታ የሚመነጭበት ነው፡፡የንድፈሃሳቡ ፍሬ ነገሮች የእውነታ መነሻና ተማሪን እንደገንቢ አካል መውሰድ ነው፡፡

አፍልቆታዊ የመማር ንድፈሃሳብ የማንበብ ትኩረት ለአንብቦ መረዳት ያለውን ወሳኝ ሚና አካቶ በመገኘቱ ከሌሎች ንድፈሃሳቦች እንደሚለየው ከላይ ተጠቅሷል፡፡እንደ(Reynolds and Shirey፣1988)ገለጻ አንባቢዎች ጠቃሚ ካልሆኑ ሓሳቦች ይልቅ ጠቃሚ የሆኑትን በተሻለ የሚረዱበትና የሚያስተውሉበት እንዱ ምክንያት ጠቃሚ ለሆኑት ሓሳቦች ተጨማሪ ትኩረት ስለሚስጡ ነው፡፡እንደ ማስታወሻ መያዝ፣ማስመር፣ቢጋር ማውጣትና የፅንስ ሃሳቦችን ዝምድና በስዕላዊ የሓሳብ ማዋቀሪያዎች ማስፈር ያሉት መረጃዎችን ሊታወሱ በሚችሉ መዋቅራዊ ስልቶች እንጻር ተግባራዊ የሚያደርጉት ጠቃሚ የጽሁፍ አላባዎች ከመለየትና ትኩረት ከመስጠት ሂደቶች ትግበራ በኋላ ነው፡፡

በማንበብ ክወና ትኩረትን በመጨመር ጠቃሚ የጽሁፍ መረጃዎችን መለየት ከመማር ጋር ስላለው ዝምድና የ(Anderson፣(1981) መርጦ የማተኮር ንድፈሃሳብ (Selective Attention Theory) እንደሚከተለው ያስረዳል፡፡መጀመሪያ አንባቢዎች በተወሰነ ደረጃ የጽሁፍን አላባዎች ያብሰልስሉ፤ባላቸው የጠቃሚነት ሁኔታም ደረጃ ይስጧቸዋል፤ከዚያም ለጽሁፍ አላባዎች የጠቃሚነት ደረጃ ተመጣጣኝ ተጨማሪ ትኩረት ያደርጉባቸዋል፡፡በሰጡት ተጨማሪ ትኩረት የተነሳም ከሌሎች አላባዎች በበለጠ የጽሁፉን ሓሳብ ለመረዳት ይችላሉ፡፡በዚህ ሂደት የጽሁፍ አላባዎች ጠቃሚነት የሚወሰነው በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ከምክንያቶቹም የተወሰኑ ፀሐፍት ጽሁፍ ውስጥ ካሰፈሯቸው ጥቋማዎች፤ሐሳቦቹ ከተገኙበት የጽሁፍ አወቃቀር የጽሁፉን ሐሳቦችና ጽሁፉን ለመረዳት ይዘውት ከመጡት ሁኔት አኳያ ሊሆን ይችላል (Anderson (1982)፤Van Disik and Kintsch (1983)፡፡የጽሁፍ አላባዎች ያላቸው ጠቃሚነት የማንበብ ትኩረትን ጨምሮ በሌሎች የማንበብ ሂደቶች ላይም ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ታውቋል፡፡

## 2.3 አንብቦ መረዳት እና የጽሁፍ አወቃቀር ትስስር

በጽሑፍ አወቃቀርና በአንብቦ መረዳት ትስስር ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡Chang (2002) Grabe (2002) Holssrodo (2011) ካደረጓቸው የጥናት ፍተሻዎች በመነሳት በጽሑፍ አወቃቀር ላይ የተደረጉ ጥናቶች አንባቢና ጽሑፍን የሚመለከቱ በሚሉ ሁለት ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡አንባቢ በሚለው ስር የሚካተቱት ስለ ጽሑፍ አወቃቀር አንባቢዎች ያገኙት ትምህርትና ግንዛቤ ወይም የነበራቸው ቀደምት እውቀት በአዲስ ማስታወስና በአንብቦ መረዳት ችሎታው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የፈተሹ ጥናቶች ናቸው፡፡እነዚህን ጥናቶች በማስተማር አቀራረባቸው በአራት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡አንድ ሰው ቀጥተኛ ማስተማርን (direct instruction) ተከትለው የተሰሩ ጥናቶች Ambruster etal (1987) Carrell (1985) Dclge & Pearson (2002) Grabe (2002) እንደጠቀሱት የጥናቶቹ ተሳታፊዎች ስለተወሰኑ የጽሑፍ አወቃቀሮች በግልጽና በቀጥታ የተማሩባቸው ናቸው፡፡ጥናቶች በመሸጋገርያ ቃላት፣በሀይለ ቃል፣በጠቋሚዎች በልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮች ሚዲያዎች ወዘተ ማስተማር ላይ አጽንኦት የሰጡ ናቸው፡፡

ሁለተኛው አቀራረብ የጽሑፍ አወቃቀር ግንዛቤ ፈጠራ (awereness of text structure) ሲሆን እንደ ሀሳብ ማዋቀርያ ስዕሎች፣የሐሳብ ድሮች፣የንድፍ ሓሳብ ምሬቶች ፣አብገር ዛፎች፣ቅድም ተከተላዊ ማጠቃልያዎች ያሉትን የጽሑፍ አወቃቀር በመጠቀም ቀጥተኛ ባልሆነ ሁኔታ የጥናቶቹ ተሳታፊዎች የጽሑፍ አወቃቀር ግንዛቤ ማግኘታቸው፣ በመረዳታቸው ወይም በማስታወሳቸው ላይ ያለውን ተፅዕኖ የፈተሹ ጥናቶች Bouchard (2002),Grable (2002) እንደተጠቀሱት Berowity (1986), Slater etal (1985) የሚገኙበት ጥናት ነው፡፡

ሶስተኛው በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ውስጥ የጽሑፍ መዋቅሮችን ማቅረብ ሲሆን እንደማጠቃለል፣የሀሳብ ስደራ፣መተንበይ፣የጽሑፍ የጎንዮሽ ጥያቄዎች ወዘተ ያሉትን ብልሃቶች ትኩረታቸውን ለአወቃቅሮቹ ባደረገው የተተገበሩባቸው ጥናቶች Block & pressley (2002) Calrell፣Etal (1989) Pressley (2002) እንደጠቀሱት ናቸው፡፡በሶስቱ አቀራረብ የተገኙት ጥናቶች ሙሉ ፍትነታዊ ወይም ፍትነት መሰል የምርምር ስልት ተከትለው የተካሄዱ ቢሆንም በውጤታቸው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ እንደ ምንባቡ መጠን የስልጠና ጊዜ ርዝመት፣የናሙና መጠን፣የተግባር አቀራረብ፣የማንበቢያ ጊዜ

አመዳደብ ያሉትን ጣልቃ ገብ ተለዋዋጮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም Chang፣ (2002)፡፡

አራተኛው ያለምንም ስልጠና የጥናቱ ተሳታፊዎች ቀድሞ ለነበራቸው ልዩነት ወይም መዋቅር ግንዛቤ መኖርና አለመኖር በመመደብ በንፅፅራዊ የጥናት ስልት ያቀረቡትን ይመለከታል፡፡በጥሩ አንባቢዎች እና በደካማ አንባቢዎች የጽሑፍ መዋቅሮች ግንዛቤ ልዩነት ላይ ንፅፅር ካደረጉ ጥናቶች ውስጥ Chang (2002) ዋቢ ያደረጓቸው የTroyer (1993) Talow (1990) McGee (1982) እና Davis (1981) ጥናቶች እንዲሁም የEnglert & Hiebert (1984) እና Geva & Ryan (1951) ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡የጽሑፍ ውቅር ግንዛቤ ያላቸው አንባቢዎች ግንዛቤ ከሌሎች አንባቢዎች በአንብቦ መረዳትም ይሁን በማስታወስ ችሎታቸው ልዩነት እንዳላቸው ከፈተሹ ጥናቶች Hokgrove (2011) ዋቢ ያደረጉት Scholotz (1982) እንዲሁም Chang (2002) የጠቀሷቸው Durham (1990) እና Stargell (1992) ይገኙባቸዋል፡፡ጥናቶቹ በአንባቢያን ባህርያትና በጽሁፍ ውቅር መለየት መካከል ወይም በአንባቢ የጽሑፍ ውቅርና ግንዛቤና በአንብቦ መረዳት መካከል ዝምድና መኖሩን በንፅፅራዊ ጥናት ስልት ፈትሸው ከማሳየት ውጭ ያላቸውን የምክንያትና ውጤት ትስስር ያሳዩ አይደለም፡፡

## 2.4. የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችና አንብቦ መረዳት

የጽሑፍ ብልሃቶች አጠቃቀምና በአንብቦ መረዳት መካከል አዎንታዊ የሆነ ጠንካራ ተዛምዶ እንዳለ የZare (2013) ጥናት አሳይቷል፡፡ በማንበብ አውድ ውስጥ የጽሑፍ አወቃቀር ብልሃት እውቀታቸውን እንዴት እንደሚተገብሩት ካልተማሩ የውቅር ብልሃት እውቀት መኖር ብቻ ለተማሪዎች የማንበብ ውጤት ስኬት ያለው ሚና ዝቅተኛ መሆኑን ደግሞ የShang (2010) ጥናት ውጤት ጠቁሟል፡፡Mehrdad & Ahgar (2012) ባደረጉት ጥናት ደግሞ እሳቦታዊና ልዕለ እሳቦታዊ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ዝቅተኛም ሆነ ከፍተኛ የቋንቋ ብቃት ባላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ጉልህ ተፅዕኖ እንደሌላቸው፣መካከለኛ ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ግን እንደሚያሻሽሉ አሳይቷል፡፡

አንብቦ መረዳትን ከማዳበር አንጻር በብልሃቶቹ መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳዩ ጥናቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ Tobing (2013) በዋቢነት በጠቀሱት የPadron & Waxman (1988) ጥናት የተወሰኑ የጽሑፍ አወቃቀር ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ ሲያሳዩ፣ ሌሎቹ ደግሞ አሉታዊ ተዛምዶ ማሳየታቸው ታውቋል፡፡Davis (2010)

የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ብልሃት ትምህርቶች አሰጣጥ ላይ የተሰሩ ጥናቶችን የተፅዕኖ ደረጃ በማወዳደር በፈተሸበት ጥናት የብልሃት ትምህርቶች የሚኖራቸው ተፅዕኖ ከብልሃት ብልሃት እንደሚለያዩ አሳይቷዋል ፡፡

## 2.5 የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች

የአንብቦ መረዳት ብልሃት አንድ ምንባብ በምን መልኩ አንብቦ መረዳት እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ስለሆነ የተለያዩ ብልሃቶችም እንዳሉ (Gunnining.2006) ይገልፃሉ፡፡እነዚህ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አራት ሲሆኑ፣እነሱም፡-ቅድመ ዝግጅት፣ቅንጅታዊ፣ማብራራትና ቁጥጥር ናቸው፡፡

**ሀ.ቅድመ ዝግጅት**

ቅድመ ዝግጅት ብልሃት አንድ አንባቢ ሊያነበው በተዘጋጀው ጽሁፍ ዙሪያ የነበረው የቀደመ እውቀት ለንባብ እንድነሳሳ ሊያደርገው የሚችል ተግባር ነው፡፡በዚህ ብልሃት ለምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ እንግዳ ያልሆኑ ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት አንብቦ ለመረዳት በቀላሉ ማነሳሳት ይችላል፡፡

ከቅደመ ዝግጅታዊ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ውስጥ መተንበይ፣በዋናነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡በምንባቡ ሊካተቱ የሚችሉ ይዘቶች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ተማሪዎች እንዲተነብዩ ለማስቻልም ቀድመው ሊታዩ የሚችሉ ነገሮች ይዘጋጃሉ፤ለዚህም አጋዥ የሚሆኑ ነገሮች ሥዕሎች፣የመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ሥዕሎች፣ርዕሶች፣ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቅድመ ዝግጅት ብልሃት ዋና ዓላማ ከዋናው የንባብ ሂደት በፊት የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት እንዲነቃቃ ለማድረግ የሚያዘጋጁ የተለያዩ ጥያቄዎች ስለሚያነቡት ጽሁፍ ትኩረት እንዲሰጡ እና የንባብ ተግባር ላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው የተሸለ እንዲሆን ይረዳቸዋል፡፡

**ለ.ቅንጅታዊ፡-**

ቅንጅታዊ የአንብቦ መረዳት ብልሃት በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ሓሳቦችና ዝርዝር ነጥቦችን በመምረጥና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት የመመርመር ሂደት ሲሆን፣ይህ ብልሃት የምንባቡን ዋና መልዕክትና ሀይለ ቃልን መለየት፣መረጃዎችን መመደብ፣የትኛው መረጃ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ መገንዘብ፣ቅደም ተከተል ማስያዝና መከለስ ፣ወዘተ

ያጠቃልላል (Wiener፣1997)፡፡ከገለጻው እንደምንረዳው የአንብቦ መረዳት መልመጃ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ መሆን ያለባቸው የምንባቡን ሀይለ ቃል እንዲያወጡ የሚያስችሉ ጥያቄዎች፣የምንባቡን ዋና መልዕክት እንዲገልጹ የሚያስችሉ ጥያቄዎች፣ መረጃዎችን የመመደብ፣ወዘተ የመሳሰሉ የጥያቄ አይነቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና መልዕክቶች ለይተው እንዲያወጡ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

**ሐ.ማብራራት (መተርጎም)፡-**

እንደ (Gunnining, 2006) ገለፃ አንባቢ ያነበበውን ጽሁፍ መሰረት አድርጎ የቀደመ እውቀቱን በመጠቀም ርዕሰ ጉዳዩን የበለጠ ለማብራራት የሚጥርበት ብልሃት ነው፡፡በዚህ ብልሃት የአንባቢው የቀደመ እውቀት አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2.6. የአንብቦ መረዳት ሁለንተናዊ ፋይዳ፤

ዓለም እየዘመነ ባለበት በአሁኑ ወቅት ማንበብ መቻል ቅንጦት ሳይሆን ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ አስገዳጅነት አለው፡፡Gove & welferberq (2011) ያልተማሩና የመረዳት ተግባራትን መከወን የማይችሉ ግለሰቦች በተለይ የዲጅታል ዘመን በሆነው በዚህ ክፍለ ዘመን ተወዳዳሪ ለመሆን ከፍተኛ ችግር ሲገጥማቸው ይስተዋላል፡፡ተማሪዎች በትምህርት ቤት ከሚማሯቸው ክሂሎች ምንባብ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የሚናገሩ ጻሕፍት(Conley, (1992)Guthrie, Schafer, & Wang, &Afflebach (1995) መኖራቸው የክሂሉ አስፈላገነት ያሳያል፡፡ከክሂሉ አስፈላጊነት አኳያም ተማሪዎች አንብቦ መረደትን እንዴት መረዳት እንዳለባቸው ስኬታማ የአንብቦ መረዳት ትምህርትንስ እንዴት ማቅረብ ይቻላል የሚሉ ጥያቄዎች የየዘመኑ ከፍተኛ ችግር ሆነው ይገኛሉ፡፡ይህም አንብቦ መረዳት የጽሑፍ(text) የዓለማ፣የይዘት፣የብልሃትና የቋንቋ እውቀት አላባዎችን በጥምረት በመተግበር የመከወን ውስብስብ ክሂል ከመሆኑ የመነጨ ነው፡፡Chun (2000) እንደጠቀሱት ተማሪዎች በተለይ ሁለተኛ ደረጃ ሲገቡ ጀምሮ ክፍላቸው በጨመረ ቁጥር አዳደስ አወቃቀር ያላቸው ውስብስብ የጽሑፍ ዓይነቶች ይገጥማቸዋል፡፡እንደ Wyse & Jones (2001) ገለጻ ማንበብን ለማንበብ ዓለማ ብቻ ሳይሆን ለመማር ዓለማ ማንበብን መማር የሚሸጋገሩበት ደረጃ ነው፡፡ Ambruster,Anlerson,and Ostertng (1987)፣(1989)፡፡

በትምህርት ቤታችንም የሚስተዋለው ችግርም ጽሑፍን ማንበቡ ሳይሆን ያነበቡትን ጽሑፍ ሐሳብ መረዳት አለመቻል ነው፡፡በትምህርት ቤታችን የተለያዩ ዳራ ያላቸው ከተለያዩ ገባሪ ትምህርት ቤት እንደመምጣታቸው መጠን የማንበብ ችሎታቸውም እንደዚሁ ይለያያል፡፡ የተወሰኑ ንባብን በቅድመ መደበኛ የጀመሩ፣ግሚሱ በቤተክርስቲያን የጀመሩ፣ ሌሎች ደግሞ በመዋዕለ ህፃናት እያለፉ የመጡ በመሆናቸው፤ሁለተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ መጀመርያ ማንበብ የለመዱበት ብልሃት ተፅዕኖ ሲያሳድርባቸው ይታያል፡፡ቤተክህነት ማንበብን የጀመሩት ለእነሱ ማንበብ ማለት ጽሑፉን እንደ ዳዊት ማበልበል ነው፡፡በትክክልም ያለግድፈት ያነባሉ፣ግን ያነበቡትን ጽሑፍና የጽሑፉን አይነት ይቅርና ስለምን እንደሚያወራ እንኳ አያቁትም፡፡ቅድመ መደበኛና መዋዕለ ህፃናት የጀመሩ ደግሞ የአቀላጥፎ ማንበብ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች ጥሩ አንባቢና ያነበቡትን መረዳት እንዲችሉ ለማስቻል አሁን ባሉበት የክፍል ደረጃ የጽሑፍ አወቃቀር (Text structure) ብልሃቶችን በማስተማር የተሻለ ውጤት ማምጣት መቻሉን ለመፈተሽ ነው፡፡

በመሆኑም በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች በሁለት ምክንያቶች የተነሳ ስለ መረጃ ሰጭ ጽሑፍ ውቅሮች አንብቦ መረዳት ማስተማር ያስፈልጋል፡፡Wong & Au(1985) አንደኛው ምክንያት መረጃ ሰጪ ጽሑፎችን ሲያነቡ በርካታ መረጃዎችን ተገንዝበው እንዲቆዩ ከመፈለግ አኳያ የውቅርን (Expostiory textes) ቃላትና የሀረጋትን ፅንሰ ሐሳቦች የሚረዱባቸውን ስልቶች ለማቅረብ ነው፡፡ሁለተኛው ምክንያት የመረጃ ሰጭ (Expostiory texts) ውቅር ጽሑፎች መዋቀርም ሆነ ይዘት ለክፍል ደረጃው እንግዳ ስለሚሆኑ ነው ፡፡

እንደ Taylor (1986), Wingral (1984) እና Brown (1983) ጥናቶች እንዳመለከቱት ግን በየደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች መረጃ ሰጭ ውቅር (Expostiory texts) ጽሑፎች አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው፡፡ ከችግሮቹ መገለጫዎችም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ማጠቃለያዎችን ዋና ሀሳቦችን ፣ጠቃሚ መረጃዎችን ፣ከጽሑፎቹ ለይተው በማውጣት ዝምድናቸውን ለማብራራት ሲቸገሩ መታየታቸው ነው፡፡በተጨማሪም ፅንሰ ሃሳብን ከመገንባት ይልቅ ፅንሰሃሳብ በመለየት ላይ ሲያተኩሩ ይስተዋላል (Ulilliams፣(1984)፡፡ ተማሪዎች በመጀመርያ እርከን የማንበብ ትምህርታቸው ለተራኪ ጽሑፍ ውቅሮች ሰፊ ተጋልጦሽ ሲፈጠርላቸው የመረጃ ስጭ ውቅር (Expostiory texts) ግንዛቤ ለማዳበር ግን አጋጣሚው የላቸውም (Piccoto፣(1987)፡፡ በተጨማሪም እነዚህን በይዘታቸው ጠጠር ያሉ

ጽሁፎችን አንብበው መረዳት ሲያቅታቸው በንባባቸው ተስፋ መቁረጥና ተነሳሽነት የማጣት ባህርይ ይንጸባረቅባቸዋል፡፡Edem,n.d Guthrie & Davis (2003)፡፡በመሆኑም በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት የተዘጋጁ ጽሑፎች አንብቦ መረዳትን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

እነዚህ የጽሑፍ አወቃቀር ብልሃቶች እውቀት የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም (Geua & Ryan፣ (1985) Grabe, (1991) ጉዳዩ በቂ ትኩረት ያለማግኘት ችግር ታይቶበታል፡፡ተማሪዎች ጽሑፍ መዋቅር እንዳለው እንዲገነዘቡ፣በማንበብ ሂደታቸው መዋቅሩን ከሚመለከቱ ጠቋሚዎች ጋር እንዲተዋወቁ፣ ለጥቆማዎቹ አእምሮያዊ ምላሽ እየሰጡ ሀሳቦችን እያስተሳሰሩ የመረዳት ልምድ እንዲያዳብሩ፣በአግባቡ ያልተዋቀሩ ጽሑፎችም ሲገጥሟቸው ጭምር ሐሳባቸውን በራሳቸው ዳግም ማደራጀትና ማዋቀር ቢጠበቅባቸውም ሲተገብሩ አይስተዋሉም፤የትምህርት አሰጣጡም ለዚህ አይጋብዛቸውም፡፡Williams (2007) በተለይም መረጃ ሰጭ ጽሑፎች (Expostiory texts) እንደ አወዳዳሪና አነፃፃሪ ፣ምክንያትና ውጤት፣ችግርና መፍትሄ ፣ቅደም ተከተል ፣ወዘተ ያሉትን የጽሑፍ ሀሳብ ተዛምዶዎች መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡Meyer Ray & Middlemies (2012) VanDisk & Kintch,(1983) ለተራኪ ጽሑፎችም የተለያዩ የግጥምጥምነት ዝምድና ስልቶች ማወቅ አለባቸው፡፡ማረው (2005) ጌታቸው (1987)፡፡Padua (2008) የጽሁፍ መዋቅር ትምህርት በአንድ ጽሁፍ ይዘት ስር ወሳኝ የሆኑ መዋቅሮችን በማካተት ተማሪዎች ቁልፍ የሆኑ እሳቤዎች ላይ ትኩረት እንያደርጉ ቀጥሎ የሚመጣውን እንዲተነብዩ ያግዛል፡፡

(Haydari and Mustapha,(2009) እንዳመለከቱት የጽሁፍ አወቃቀርን በጽሁፍ አማካኝነት ጸሐፊው መረጃ ለመስጠት፣ለመግለጽ፣ ለማብራራት እና ለማግባባት የሚጠቀምበት ነው፡፡ ትምህርታዊ ይዘት ያላቸውን ጽሁፎች የሚቀርቡበት አንዱ የጽሁፍ አወቃቀርን በመጠቀም ነው፡፡ተማሪዎች ስለ ተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች ማወቃቸውን ከጽሁፍ ውስጥ መለየት ያለባቸውን ሐሳቦች ለመለየት፣ የችግርና መፍትሄ ተዛምዶን ለመገንዘብ፣ጽሁፉ የተዋቀረበትን አደረጃጀት በመለየት፣ ወዘተ ሓሳብን እንዲለዩ ያግዛቸዋል፡፡የምክንያትና ውጤት ተዛምንዶን ለመገንዘብና የጽሁፍን ሙሉ መልዕክት ለማስታወስ ይጠቅማቸዋል፡፡ ልክ እንደ ማንኛውም የማንበብ ብልሃቶች የጽሁፍ አወቃቀር እውቀት መኖር ለተማሪዎች በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ትምህርቱ በግልጽና በዘዴ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

Meyer፣Brandt and Bluth (1980) እንዳስረዱት የጽሁፍ አወቃቀርን መለየት በማንበብ ክሂል ላይ ተመስርተው ለሚካሄዱ ጥናቶች ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡አንዱ የጽሁፍ አወቃቀር ገጽታዎች በምንባቦች ውስጥ ያሉትን ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ከመገምገም አኳያ ትርጉም አዘል ገጽታ ይኖረዋል፡፡ሁለተኛ የጽሁፍን አወቃቀር መለየት አንባቢው ከጽሁፍ ምን ያህል የመረጃ መጠንና አይነት ማስተዋስ እንደሚችሉ ለማወቅ ያስችላል፡፡ሶስተኛ በጽሁፉና በአንባቢው ጽሁፍን አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል የሚፈጠርን ልዩነት ለማወቅ ያስችላል፡፡ስለዚህ የጽሁፍ መዋቅርን ማስተማር አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡

Grabe (2002) ባካሄዱት ጥናት ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት ሶስት ሐሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡የመጀመሪያው ተማሪዎች በቀጥታ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር የሚያገኙት እውቀት በራሱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ሁለተኛ የተማሪዎችን የጽሁፍ አወቃቀር ግንዛቤን ለማሳደግ አቀራረቡ በግራፍ ፣በሠንጠረዥ ፣በዐረፍተነገር ፣በካርታዎች፣በዛፍ ምስል እና ማጠቃለያ በመስጠት መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ እንደሚያሳየው የተማሪዎች ጽሁፍን የመረዳት ችሎታ የተሻለ የሚሆነው አንድ መረጃ እንዴት በጽሁፍ ውስጥ እንደ ተደራጀ መለየት ሲቻሉ ነው፡፡

Harmer (1991) እንደሚገልጹት የተለያዩ ጽሁፎች ለተለያየ ዓላማዎች ሲነበቡ አንባቢዎች የተለያዩ ስለቶችን መጠቀም የግድ ነው፡፡እነዚህም የንባብ ስላቶች የግርፍታ (ምልከታ) ንባብ፣የአሰሳ ንባብ፣ሰፊ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ በመባል በአራት ይመደባሉ፡፡የግርፍታ ንባብ የተጻፈን ጽሁፍ ሃሳብ ለማግኘት ወይም መልዕክቱን ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ስልት ነው፡፡ይህ ስልት ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ የአንቀጹን መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ለመረዳት የምንጠቀምበት ነው፡፡ሁለተኛው ስልት የአሰሳ ንባብ ሲሆን፣ በፍጥነት የማንበብ ስልት ሆኖ ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ አንድ የተወሰነን መረጃ ፈልጎ ለማውጣትና ለመገንዘብ የምንጠቀምበት ስልት ነው፡፡ሶስተኛው ሰፊ ንባብ የሚባለው ሲሆን በቦታና በጊዜ ሳይወሰን ሰዎች በአብዛኛው ለመዝናናት የሚያነቡት የንባብ ስልት ነው፡፡የሚነበበው ጽሁፍ ሰፊ ስለሆነ የጽሁፉን መልዕክት ለመገንዘብ የአንባቢውን ልምድና ብቃት ይጠይቃል፡፡ አራተኛው ደግሞ ጥልቅ የንባብ ስልት የሚባለው ሲሆን፣ይህም ጽሁፍን በጥልቀት ለመረዳት ሲባል የጽሁፉ መጠን ይነስም ይብዛ በቦታና በጊዜ ተወስኖ፣ከፍጥነት ይልቅ በርጋታ፣በትኩረትና በጥንቃቄ የሚከወን የንባብ ስልት ነው፡፡በጥልቅ ንባብ ጊዜ በጽሁፍ

ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ መረጃዎች ላይ ከማተኮር አንስቶ በግልጽ ያልሰፈሩ ሓሳቦችን ምንነት እስከ መተንተን የሚደርስ የንባብ ስልት ነው፡፡

ለዚህ ጥናታዊ ስራ ማጠንጠኛ የሆነኝ የ (Haydari and Mustapha፣2009) ስራ የሆነው የጽሁፍ አወቃቀርን በጽሁፍ አማካይነት ፀሐፊው መረጃ ለመስጠት፣ ለመግለጽ፣ለማብራራትና ለማግባባት የሚጠቀምበት ነው ስለሚል፣ እንዲሁም ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች አንዱ የጽሁፍ አወቃቀርን መጠቀም ነው ስለሚል ነው፡፡ ተማሪዎች ስለተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች ማወቃቸው ጽሁፍ ውስጥ ሐሳቦችን ለመለየት፣የችግርና መፍትሄ ተዛምዶ ለመገንዘብ፣ጽሁፉ የቀረበበትን አደረጃጀት በመለየት ፣የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን በመገንዘብ የጽሁፍን ሙሉ መልዕክት ለማስታወስ ይጠቅማቸዋል፡፡ በሚሉት ሐሳቦች ዙሪያ ስለሚያጠነጥን ለዚህ ስራ እንደመነሻ ሆኖኛል፡፡

## 2.7 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.7.1 የሀገር ውስጥ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በሀገራችን የተሰሩ የተዛማጅ ጽሁፎችን በመቃኘት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተወሰኑ ሥራዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

ሓይማኖት (2005)፡፡‹‹በፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች የቃላት ዕውቀት ችሎታና የአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ›› በሚል ርዕስ የተቃኘ ጥናት አካሂዶ የቃላት ዕውቀት መኖር ለአንብቦ መረዳት አስተዋጽኦ እንዳለው አረጋግጧል፡፡የሓይማኖት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በአንብቦ መረዳት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ይመሳሰላል፡፡የሓይማኖት ጥናት ተለዋዋጩን ያደረገው የቃላት ዕውቀት ለአንብቦ መረዳት ያለውን አስተዋጽኦ ሲሆን፣ይህኛው ትኩረቱን ያደረገው ደግሞ በጽሁፍ አወቃቀር ላይ በመሆኑ ይለያያል፡፡

መሪነሽ (2004)፡፡‹‹የማንበብ ተነሳሽነት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ›› በሚል ርዕስ በጎንደር ከተማ የእድገት ፈለግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጥናት አድርጋ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመዳበር ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሽነትን በመፍጠር አጥጋቢ ውጤት ማግኘቷን ገልጻለች፡፡የመሪነሽ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማጎልበት ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ስለሆነ ይመሳሰላል፡፡ ልዩነቱ የመሪነሽ ትኩረት ወይም ዓላማ ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሽነትን በመፍጠር

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማጎልበቱን መፈተሸ ሲሆን፣ይህ ጥናት ደግሞ ትኩረት ያደረገው የጽሁፍን አወቃቀር ብልሃትን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ሚና ላይ ስለሆነ ይለያያል፡፡

ማስተዋል (1989)፡፡በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናቱ ዓላማም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን መፈተሽ ነው፡፡ጥናቱ በመረጃ መሰብሰቡያነት የተጠቀመው ፈተና ፣ምልከታንና የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡በጥናቱ የተገኘው ውጤት የተማሪዎች የአነብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን አመልክቷል፡፡የማስተዋል ስራ ከዚህ ስራ ጋር የሚያመሳስለው የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ ስለሆነ ይመሳሰላል፡፡በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም ቢሆን ከምልከታ በስተቀር በሌሎቹ ይመሳሰላል፡፡

ሰለሞን (2003)፡፡‹‹ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ›› በሚል ርዕስ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡የጥናቱ ዓላማ በሁለቱ ክፍሎች በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ጽሁፍ ከአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብና ከጥሩ ምንባብ ባህሪ አኳያ መፈተሽና መተንተን ነው፡፡ ለጥናቱ የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡የጥናቱ ውጤት ያሳየው መምህራን በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን እንደማይጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡ይሁን እንጂ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ሳቢ፣ተገቢነትና ግልጽነት ያላቸው ሥራዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡የሰለሞን ስራ አንብቦ መረዳት ላይ ትኩረት ማድረጉ ከዚህ ስራ ጋር ሲያመሳስለው፤የጥናቱ ስልትና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው የተለያየ በመሆኑ ከዚህ ሥራ ጋር ያለያየዋል፡፡

በየነ (1989) ፡፡‹‹የፍጥነት ንባብ እና የአንብቦ መረዳት ዝምድና በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ እንደተሞከረው›› በሚል ርዕስ የፍጥነት ንባብ እና የአንብቦ መረዳት ክሂል ዝምድና መለየትን የጥናታቸው ዓላማ በማድረግ ባደረጉት ፍተሻ፣የፍጥነት ንባብ እና አንብቦ መረዳት የማይነጣጠሉና ጠንካራ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡የበየነ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ትኩረቱን በአንብቦ መረዳት ላይ በማድረጉ ሲማሳሰል፣በየነ ተለዋዋጭ ያደረገው የፍትነት ንባብን በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

ነብዩ (2005) ፡፡ ‹‹በግጥም አማካኝነት የ9ኛ ክፍልተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳትና የጽሁፍ ችሎታን ማዳበር›› በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት ዓላማ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳትና የጽሁፍ ችሎታን ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና ማረጋገጥ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያውም ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡የትናቱ ውጤትም በፈጠራ ስራዎች አማካኝነት ማበብን ማስተማር የማንበብ ክሂላቸውን እንደሚያዳብር ገልጸዋል፡፡ይህም ጥናት ትኩረቱን ያደረገ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መፈተሽ ላይ በመሆኑ ከነብዩ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ይሁን እንጂ የእኔው ጥናት ተማሪዎች የቀረበውን ጽሁፍ ብቻ አንብበው እንዲረዱ ሳይሆን በጽሁፍ አወቃቀር ብልሐቶች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረግ ላይ ስለሚያተኩር ይለያያል፡፡

ከበደ(1989)፡፡በ11ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተመረጡ ሁለት የጉራጌ ዞን የመሰናዶ ት/ቤቶች ለመጀመሪያ ድግሪ ማሙያነት ባቀረቡት ጥናታቸው እየተሰራበት ያለው የንባብ ክሂል አተገባበር በመቃኘት ያሉትን ችግሮች ለመለየትና የመፍትሄ ሐሳቦችን ለማስቀመጥ ችለዋል፡፡የከበደ ጥናት የሚያጠነጥነው በማንበብ ክሂል ዙሪያ ባለው ችግር ላይ ስለሆነ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ልዩነቱ ይህ ጥናት የሚያተኩረው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማዳበር የጽሁፍ አወቃቀርን በማስተማር የሚመጣውን ለውጥ መፈተሽ ሲሆን፣ የከበደ ግን የንባብ ትምህርት አተገባበር ላይ በመሆኑ ይለያያል፡፡

እንዲሪስ (2009)፡፡ ‹‹በቴክስት ውቅር ብልሐቶች በአማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ›› በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ጥናት አድርገዋል፡፡የጥናቱ ዓላማ በቴክስት ውቅር ብልሐቶች ማንበብን መማር በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት፣ግለ ብቃት፣እምነት፣ትኩረትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተጽዕኖ መፈተሽ ነው፡፡የመረጃ መሰብሰቢውም ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡የጥናቱ ውጤትም ያመለከተው በጽሁፍ ውቅር ብልሐቶች አጠቃቀምና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል አዎንታዊ ጠንካራ ተዛምዶ እንዳለ ጠቁሟል፡፡የጽሁፍ መዋቅርን ማስተማርና አንብቦ መረዳት ጠንካራ ተዛምዶ እንዳላቸው አመልክቷል፡፡ የእንዲሪስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ከሞላ ጎደል ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.7.2. የውጭ አገር ጽሁፎች ቅኝት

በጽሁፍ አወቃቀር ላይ ከተሰሩ ቀደምት ስራዎች ውስጥም የAlexander and Jetton (1996)፣Golding and Fower(1992) ስራዎችን ዋቢ አድርገው እንዳሰፈሩት የጽሁፍ አወቃቀሮች ግንዛቤ ዋና ሃሳቦችን ለመለየትና ለማስታወስ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡እንደ Berkowwitz (1986)፣Carrell (1985) እና Troyer (1994) ጥናቶችም የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን (ማስታወስን) እንደሚያሻሽሉ አመልክተዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የጽሁፍ አወቃቀሮችና መረጃዎች ባሏቸው ፅሰንስ ሃሳባዊ አወቃቀሮች መካከል ተመሳሳይነት ካለ መረዳት እንደሚኖር፣ተመሳሳይነት ከሌለ መረዳት እንደሚደናቀፍ ጥናቶቹ አመለክተዋል፡፡

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱና አስፈላጊው ክሂል የማንበብ ክሂል ነው፡፡ማንበብ የማሰብ፣የመገመት፣የመፈረጅ፣ችግርን የመፍታት ችሎታን የሚያጎናጽፍ ሂደት ነው፡፡Greay የተባለ ምሁር በአለም አቀፍ የምርምር ጆርናል (2012) በሰነዘረው አስተያየት የማንበብ ሂደት መገንዘብን፣መረዳትን፣ማሰላሰልና ማዛመድን እንደሚይዝ አስረድተዋል፡፡የማንበብ ክሂል አስፈላጊነት እና ጠቃሚነት ለሁሉም ማህበረሰብ ቢሆንም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ዘርፈ ብዙ ችግር እንዳለባቸው ያመላከቱ ጥናቶች አሉ፡፡ (Ambuster,Anderssen &Ostertage1987)፡፡የጥናቶቹ ውጤት እንዳመለከተው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች በሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ አስፈላጊና አላስፈላጊ ሃሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት አይረዱም ፤አንብበውም የማጠቃለያ ሃሳብ በቃልም ሆነ በጽሁፍ መስጠት አይችሉም፡፡ በአንብቦ መረዳትና በጽሁፍ አወቃቀር መካከል ጥብቅ ትስስር እንዳለ ጥናቶች የጠቁማሉ፡፡Hass (2006) አራትና አምስት አንቀጽ ያለው ጽሁፍ ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ማስተማሪያነት ቢቀርብ የመጀመሪያው አንቀጽ ስለ ችግሩ ምንነት ይጠቅሳል፣ሁለተኛው፣ሶስተኛው እና አራተኛው የችግሩን መፍትሄ ይጠቁማል፡፡ይህ አይነት አደረጃጀት ለአንባቢው ስለሚነበበው ጽሁፍ ጥቆማን ስለሚሰጥ የሚይነቡትን ጽሁፍ የማደራጀትና የማቀናጀት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ያስችላቸዋል፡፡

Gentry (2006),Piyonukool (2002) ንባብ በትምህርትም ይሁን፣በህይወት ዘመን ስኬታማ ለመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡የማንበብ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የጽሁፍን መልዕክት ለመገንዘብ ይቸገራሉ፤ቃላትና ፅንስ ሓሳቦችን የመረዳት ችግር፣ጠቃሚ የሆኑ

የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ያለመጠቀም፣በአጠቃላይ የሚያነቡትን ጽሁፍ ሓሳብ ሙሉ ለሙሉ ያለመረዳት ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ ያለ ጽሁፍን አንብበው እንዲረዱ በአነበቡት ጽሁፍ ሀሳብ ላይ ተመስርተው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠበቃል፡፡በጥልቀት የማንበብ ችሎታ ደግሞ የጽሁፍ ማዕከላዊ ሃሳብ እንዲያወጡና በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ወሳኝ ነው፡፡

የቀደምትና የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በየትኛውም የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀርብላቸውን በተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀር የተደራጁ ጽሁፎችን አንብበው ለመረዳት ይጥራሉ፡፡ይሁንና ባላቸው ዝቅተኛ የማንበብ ችሎታ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ማስታዋስ አይችሉም፡፡በዚህ ምክንያት ካነበቡት ብዙ ሃሳብ ውስጥ የተወሰነ መረጃ ብቻ ይወስዳሉ፡፡ይህንን ችግር ለመፍታት አንዱ መንገድ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሓቶችን ለተማሪዎች ማስተማርና ማስጨበጥ መሆኑን የጠገኙው ጥናት ያመለክታል፡፡

Yochun (1991),Dole & etal (1991) እንደጠቆሙት አንብቦ መረዳት ማለት በአንባቢው የቀደመ እውቀትና በጽሁፍ ውስጥ በቀረበው መልዕክት መካከል የሚፈጠር መስተጋብር ውጤት ነው፡፡ስለዚህ ማንበብ በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ሓሣቦችን አንባቢው ያለውን የቀደመ እውቀት የማስተሳሰር ብቃትን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡የዳርዊ እውቀትንና የጽሁፍ አወቃቀርን በማጣመር ጽሁፍን ለመረዳት የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ማዳበር ይኖርበታል፡፡በአጠቃላይ በጥናቶች ውጤት እንደተጠቆመው የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀርን ማስገንዘብና መጠቀም አስፈላጊነቱ የጎላ እንደሆነ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከጽሁፍ አወቃቀር ጋር አወንታዊ ግንኙነት እንዳለው የተገኘው መረጃ ያመለክታል

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ስልት

ይህን ጥናታዊ ስራ ከግብ ለማድረስ የተመረጠው ዋና የምርምር ስልት (ጥናት ንድፍ) ሙከራ አልባ ፍትነታዊ (Quasi Expermental Research) ነው፡፡የዚህ ዘዴ ተጠኚዎች በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን የማስተማር ዘዴን በመተግበር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማጎልበት ያለውን ሚና ቃኝቶ (ፈትሾ) ውጤቱን ለመግለጽና መፍት ለመስጠት ተመራጭ በመሆኑ ነው፡፡ጥናቱ የሚደረገው በሁለት ቡድኖች ላይ ስሆን፣ሁለቱ ቡድኖች የሚለያዩበተን ባህሪ ማለትም ነፃ ተለዋዋጩ በተጠኝ ቡድኑ ባህሪ ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ በመለካት የተጠኝው ቡድን ከተለመደው ወይም ከአይነተኛው ባህሪ ምን ያህል እንዳፈነገጠ የመቆጣጠሪያ(የቁጥጥር) ቡድኑን ባህሪ እንደማወዳደሪያ መስፈርት በመውሰድ መደምደሚያ ላይ መድረስ ስለሚያስችል ለዚህ ጥናታዊ ስራ ተመራጭ የምርምር ስልት ሆኖ በመገኘቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ታላሚ በማድረግ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማጎልበት የጽሁፍ አወቃቀርን (Text structure) ውጤታማነቱን ለመፈተሽ ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅና በፈተና የሚገኝን የመረጃ ውጤት በስታቲክሳዊ ስሌት መሰረት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ጥናቱ ሲካሄድ በ9ኛ ክፍል በ2011 ዓ.ም ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል የሁለት ክፍል ተማሪዎች በመውሰድ፣አንደኛውን ክፍል የመቆጣጠሪያ ቡድን (Control group) ሁለተኛውን ቡድን ደግሞ ሙከራ ቡድን (Expermental group) በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ይህ ያስፈለገው በቡድኖቹ መካከል በፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበን መረጃ በመተንተን በተጠኝዎቹ መካከል ያለውን የውጤት ተቀራራቢነትና ልይይት በንፅፅር ለማሳየት ነው፡፡ጥናቱ የሚካሄደው በባሶ መሰናዶ እና አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2011 ዓ.ም በ9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በሚከታተሉ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

## 3.2. የጥናቱ አካላይ

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ሆነው የተመረጡት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወራና ወረዳ ከሚገኙ ሁለት 2ኛ ደረጃና አንድ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃና መሰነዶ ት/ቤት መካከል አንዱ በሆነው በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤት በ2011 ዓ.ም በ14 (አስራ አራት ) የዘጠንኛ ክፍል ደረጃ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥም ተመዝግበው በመማር ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ በሁለት የመማሪ ክፍሎች የሚማሩትን እኩል ዕድል ሰጭ በሆነው ተራ የዕጣ ንሞና በመምረጥ ነው ጥናቱ የተካሄደው፡፡

ት/ቤቱ የተመረጠው በአመች ወይም በግኝት ንሞና ዘዴ ነው፡፡ምክንያቱም አጥኚው በት/ቤቱ ለአራት ዓመት የሰራና አሁንም እየሰራ ያለ በመሆኑ ከመምህራንም ሆነ ከተማሪዎች መረጃን በቀላሉ ለመሰብሰብና የተለያዩ ድጋፎች ለማግኘት አመች በመሆኑ ነው፡፡

## 3.3.የናሙና አመራረጥ ስልት

የጥናቱ ዋና ዓላማ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን፣ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገው በባሶና ወራና ወረዳ በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ባሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ለጥናቱ የተመረጠው ንሞና እኩል ዕድል ሰጪ ንሞና የሆነው ቀላል የዕጣ ንሞና ነው፡፡ይኸም የሆነው ተመራማሪው ሁሉንም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ለማካተት የጊዜ፣የሰው ኃይልና የእኮኖሚ ችግር ስለሚያጋጥምው በትምህርት ቤቱ ለመማር ከተመዘገቡት 774፣ከአስራ አራት መማርያ ክፍሎች ውስጥ የሁለት ክፍል ተማሪዎችን ብቻ በመውሰድ ጥናቱን ለማድረግ ዕድል ሰጪ ንሞና ተመርጧል፡፡

ሁለቱ የመማሪያ ክፍሎች የተወሰዱት እንዱን የሙከራ ቡድን ሌላውን የቁጥጥር ቡድን በማድረግ ሲሆን፣የተለዩትም እኩል ዕድል ሰጭ ንሞና በሆነው በተራ ዕጣ ንሞና ነው፡፡በጥናቱ ለመሳተፍ ፍቃደኝነታቸው ተጠይቆ ፍቃደኛ ከሆኑ በኋላ የቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጎ አማካይ ውጤታቸውና መደበኛ ልይይታቸው ሲሰላ የሁለቱም ክፍሎች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የ9ኛE ክፍል የቁጥጥር ቡድን ሲሆን፣በብልሃት አልባ ወይም በተለመደው (በተዘውታሪው)

የአንብቦ መረዳት የማስተማሪያ ዘዴ እንደማር ሲደረግ፣በሙከራ ቡድንነት የተመረጠው የ9ኛK ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በተመረጠው በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት የማስተማሪያ ዘዴ እንዲማሩ በማድረግ ጥናቱ ተካሄዷል፡፡

## 3.4 የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት በተሳታፊነት የተመረጡት በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወራና ወረዳ ከሚገኙ የመንግስት ት/ቤቶች በአንዱ በባሶ መሰናዶ እና አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ2011 ዓ.ም በ9ኛ K ክፍል እና በ9ኛE ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች በአንድ መምህር የሚማሩ ናቸው፡፡ የ9ኛK ክፍል ተማሪዎች ሙከራው የሚካሄድባቸው ሲሆኑ፣በ9ኛE ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ደግሞ የመቆጣጠሪያ (Control group) በማድረግ ነው፡፡ተማሪዎቹ በዕድሜና በጾታ ስብጥራቸው ተቀራራቢ ስለሆኑ ውስጣዊ ትክክለኝነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረውን የትምህርት ክትትል ልዩነት ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ የተሳተፉት ተማሪዎች ሳያቋርጡ እስከ መጨረሻው በመሳተፋቸው በጥናቱ ውስጣዊ ትክክለኝነት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችለውን አቋራጮች መቆጣጠር አስችሏል፡፡

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዋና አላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት አግባብነት አላቸው ተብለው የተወሰዱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.5.1. የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች (Pertest and Posttest)

ፈተና በቀላል መንገድ የሰዎችን ችሎታና የስራ አፈጻጸም በአንድ በተወሰነ ነገር ላይ መመዘን የሚችል መረጃ መሰብሰቢያ ነው በማለት Brawon (2012፡3) ይገልጸዋል፡፡ለዚህ ጥናት ፈተና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ተመርጧል፡፡ይህም የሚለካልን የጥናቱን ታላሚዎች የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን በምንባብ ውስጥ በመጠቀማቸው በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ መሻሻል መምጣት ወይም አለመምጣት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመለካት ሰለሚያስችል የጥናቱ ተሳታፊዎች ሁለት ጊዜ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ተፈትነው አንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ መረጃ ተሰብስቧል፡፡የመጀመሪያው የቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና ነው፡፡የዚህ ፈተና ውጤትም በጥናቱ መነሻ ሁለቱም ቡድኖች ትምህርቱን ከመማራቸው በፊት ተመጣጣኝ ችሎታ(እውቀት) ያላቸው

መሆኑን ለማረጋገጥ ስራ ላይ ውሏል፡፡ይህ ለሁለቱም ቡድኖች የጥናቱ የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው የቀደመ እውቀታቸውን መለኪያ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም የቅድመ ትምህርት ፈተና ከተጠናቀቀ በኋላ ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጋር ለውጥ መኖር አለመኖሩንና የሚኖር ከሆነም የለውጡን የጉልህነት ደረጃ ለመመርመር ይረዳል፡፡ ሌላው ፈተና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ነው፡፡ዓላማውም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ሁለት አቀራረቦች ማለትም የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው (በተዘውታሪው) የማስተማር ዘዴ አንብቦ መረዳትን እንዲማሩ ሲደረግ ፣ተጠኚው (የሙከራ ቡድኑ) ደግሞ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንዲማሩ በማድረግ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መለያየት (መበላለጥ) ጉልህ መሆን አለመሆኑን አነፃፅሮ መረጃ ማስገኘት ነው፡፡

እነዚህ ሁለት ፈተናዎች የጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ ሆነው ሲዘጋጁ፣ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምንባቦች ኖሯቸው በሰራቸው ደግሞ ሃያ ሃያ (20) ጥያቄዎችን አካተው ይዘዋል፡፡ ጥያቄዎቹ ሁለት ክፍል ያላቸው ሲሆን፣በሁለቱ ክፍሎች የተለያየ የአንብቦ መረዳት ችሎታን መለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ተሰተዋል፡፡የመጀመሪያው ክፍል ከምንባቡ የወጡ ቃላትና ሀረጋትን አውዳዊ ፍች የሚጠይቁ የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የቃላትና ሀረጋት እውቀት ምን ያህል እንደሆነና የሚያነቡትን ጽሁፍ መልዕክት ለመረዳት ምን ያህል እንደሚያግዛቸው ለመለካት አስችሏል፡፡

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት የመረዳትና በምንባቡ ውስጥ ያለውን የጽሁፍ ትስስር መለየት እና በጽሁፍ የቀረቡ የሀሳብ አደረጃጀትን የሚያሳዩ በጅምር የቀሩ ሀሳቦችን በመቋጨትና የሀሳብ ትስስሩን በስዕል እያደራጁ እንዲመልሱ የሚያስችሉ፣የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ ፣በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

ሁለቱ ፈተናዎች የክፍል ደረጃውን ፣ የተማሪዎችን ዕድሜ እና ችሎታ በአገናዘበ መልኩ በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት አግባብ የተዘጋጁ መሆናቸው በትምህርት ቤታችን በሚያስተምሩ ሁለተኛ ድግሪ ባላቸው መምህራን እንዲገመገም ተደርጎ ነው የተሰጠው፡፡ የተመረጡት ምንባቦች በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተመሰረቱ፣ከጽሁፍ ማስፋፊያ ብልሃቶች ውስጥ በምክንያትና ውጤት እና በማወዳደርና ማነጻጸር ብልሃት የተዋቀሩ፣የክፍል ደረጃውን ያገናዘቡ በርካታ ቅንጫቢዎችን የያዙ አስር ምንባቦች፣አራቱን ለቅድመና ድህረ

ትምህርት ፈተና፣ስድስቱን ደግሞ ለማስተማሪያነት በመምረጥ እና ከላይ በተጠቀሱት መምህራን በማስፈተሽ ተተግብሯል፡፡

በአጠቃላይ ፈተናዎች ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት የመለየት አቅማቸውን፣የቃላት አውዳዊ ፍች እንዴት እንደሚገነዘቡ፣ በምንባቡ ውስጥ ቃላትና ሀረጋት የያዙትን ፍችና ሃሳብ የመረዳት ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ ምንባቦቹ የሚያስተላልፉቸውን ማዕከላዊ ሃሳቦችን ማውጣትና የማጠቃለያ ሃሳብ መስጠት መቻላቸውን የሚመዝኑ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ ምንባቦቹ በምክንያትና ውጤት እና በማወዳደርና ማነጻጸር የተዋቀሩ ናቸው፡፡

እርመቱን ያካሄዱት በባሶ አጠ/ 2ኛ ደረጃ መሰናዶ ት/ቤት የሚያስተምሩ ሶስት የአማርኛ መምህራን ሲሆን፣ የሶስቱን መምህራን እርማት ውጤት አመካይ በመውሰድ የውጤት ትንተናው ተሰርቷል፡፡እርማቱ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የጎረቤት ት/ቤት መምህራን እንዲፈተሽ ተደረጓል፡፡የመጣው ውጤት ከ 40% ታርሞ የእያንዳንዱ ተጠኚ ቡድን ነጥብ ተመዝግቦ ተተንትኗል፡፡

እነዚህ ነጥነታዊ ስራው የተመረጡ ምንባቦች እና ትምህርት የተሰጡት ከመደበኛው የመማር ማስተማር ፕሮግራም ውጭ በቲቶሪያል ክፍል ሲሆን፤መደበኛውን ትምህርት ከሰዓት በኋላ የሚማር ከሆነ በጠዋቱ የቲቶሪያል ክፍለ ጊዜ መደበኛ ትምህርቱን የሚማሩት ጠዋት ከሆነ ከሰዓት በኋላ እንዲማሩ በማድረግ ትምህርቱ ተሰቷል፡፡ በትምህርት ቤታችን ደነብ ፈረዎች የሚለወጡት በየአስራምስት ቀኑ ሰለ ሆነ ተኚዎቹ በሁለቱ ፈረቃ የመማር እድል አግኝተዋል፡፡ይህ ደግሞ በውስጣዊ ትክክለኝነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድረውን የትምህርት ክትትል ልዩነት ለመቀነስ ይረዳል፡፡

### 3.5.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የዚህ ጥናት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡በዚህ ጥናታዊ ስራ ላይ ተግባራዊ የተደረገው የጽሁፍ መጠይቅ ዝግ መጠይቅ ነው፡፡ዓላማውም የጽሁፍ መዋቅር መማር፣መለማመድና የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በንባብ ክዋኔ ጊዜ በመጠቀም አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መሻሻሉን፣ተማሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ፣አመለካከት እና ክሂሉን የመረዳት አቅም አመላካች ጥያቄዎችን መጠየቅ ነው፡፡የጽሁፍ መጠይቁ በዋናነት የሚጠቀመው ሬቲንግ ስኬል (Rating scale)ነው፡፡መጠይቆቹ ዝግ ስለሆኑ

ለእያንዳንዳቸው አራት አማራጮች እንዲሆኑት ተደርገዋል፡፡ጥያቄዎቹ ጊዜ ቆጣቢ፣ ግልፅና ተነባቢ እንዲሆኑ ጥረት ተደረጓል፡፡ይህም ሲከናወን የአማካሪን ድጋፍና አስተያየት መጠቀም ተችሏል፡፡መጠይቁም ለተጠኚዎች ሲቀርብ በተገቢው መንገድ ምላሽ እንዲሰጡ በተቻለ መጠን አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡የጥያቄዎቹ ብዛት10 (አስር) ሰሆኑ፣ እያንዳንዳቸው አራት አራት አማራጮች አሏቸው፡፡እነሱም፡-

4.በጣም እስማማለሁ

3.እስማማለሁ

2.አልስማማም

1.ጭራሽ አልስማማም ናቸው፡፡

## 3.6. የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥና አዘገጃጀት

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ ምንባቦች (ጽሁፎች) የቅድመ ትምህርት ፈተና ከተሰጠ በኋላ የተጠኝዎችን የክፍል ደረጃቸውን በሚመጥን መልኩ የምንባቦቹ አመራረጥና የመልመጃዎች አዘገጃጀት ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

### 3.6.1 የማስተማሪያ ምንባቦች አመራረጥ

ለብልሃት ቡድንም ሆነ ለቁጥጥር ቡድን የተመረጡት ምንባቦች በምክንያትና ውጤት እና ማወዳደርና ማነፃፀር የተደራጁ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን የያዙ ምንባቦች ናቸው፡፡ ለምክንያትና ውጤት አወቃቀር በተለያዩ ሁኔታዎችና ፅንስ ሀሳቦች መካከል ያሉ ምክንያታዊ ዝምድናቸውን የሚያሳዩ ወይም አንድ ነገር በአንድ ቦታ ላይ የመገኘቱን ምክንያትና ውጤት የሚገልጹ ምንባቦች ተዘጋጅተው ተሰተዋል፡፡ለማወዳደርና ለማነፃጸር አወቃቀርም ሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ድርጊቶችና ሁነቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ታቃርኖ የሚገልጹ ምንባቦች ተለየተው እና ተመርጠው ቀርበዋል፡፡እነዚህን የጽሁፍ አወቃቀሮች የሚያለማምዱ ምንባቦች የተማሪዎችን ችሎታ ከግምት ውሰጥ ባስገባ መልኩ ከልዩ ልዩ የጽሁፍ ምንጮች ተመርጠው ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ አባሪ‹‹መ››ን ይመልከቱ፡፡

ምንባቦቹ ለተማሪዎች ሲቀርቡ፣የብልሃት ቡድኑ በምክንያትና ውጤት እና በማወዳደርና ማነፃፀር የተደራጁ፣ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን የያዙ ምንባቦች ሲቀርብላቸው፣ የቁጥጥር ቡድን ደግሞ በተለመደው (በተዘውታሪው) የአንብቦ መረዳት የማስተማሪ ዘዴ የሚተገበሩ ምንባቦች እንዲቀርብላቸው ተደርገው ተመርጠዋል፡፡

### 3.6.2. የመልመጃዎች አዘገጃጀት

ለልመምድ የቀረቡት የምክንያትና ውጤት እና የማወዳደርና ማነጻጸር የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች ናቸው፡፡በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት አንብቦ መረዳትን ለሚማረው የሙከራ ቡድን ማስተማሪያ የተዘጋጁ መልመጃዎች በየክፍለ ትምህርቱ የጽሁፍ አወቃቀሮችን ምንነትና ባህሪያት ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ይጀመራል፡፡ከዚያም እያንዳንዱን አወቃቀር እየነጣጠሉ በማቅረብ በእነሱ ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ተግባራት ቀርበዋል፡፡የጽሁፍ አወቃቀር ይዘቶች እንደ ማወዳደርና ማነጻጸር፣ምክንያትና ውጤት ያሉትን የጽሁፍ አወቃቀሮች እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡በመቀጠል የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን ለማስተማር የሚችሉ አጫጭር ምንባቦች ቀርበዋል፡፡አወቃቀሩን እንዲለዩ የሚያስችሉ የጽሁፉን ምንነት የሚጠቁሙ ፍንጭ ሰጪ አያያዥ እና የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋት ፣ዓላማቸውን የሚያሳዩ ተግባራት ተካተው ቀርበዋል፡፡በሌላ በኩልም የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ጠቋሚ ጥያቄዎች በማካተት መልሳቸውን ከምንባቡ እያወጡ እንዲመልሱ የሚያደርጉ ተግባራት ተሰተዋል፡፡እንዲሁም እያንዳንዱን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት አመልካች ቃላትና ሀረጋት፣የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋት እየተለዩ እንዲቀርብላቸው ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ምንባቡ ቀርቦላቸው ምንባቡን እያነበቡ ከላይ የተጠቀሙትን ተግባራት ግምት ውስጥ እያስገቡ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

ለቁጥጥር ቡድን አንብቦ መረዳትን በብልሃት ለተማረው ቡድን የቀረቡት ምንባቦች ምንም ሳይቀየሩ ያለ ጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን እንዲማሩ የሚያደርጉ በአመዛኙ በተለመደው (በተዘውታሪው) የአንብቦ መረዳት ችሎታ እውቀት ማዳበር ላይ የሚያተኩሩ መልመጃዎች ተዘጋጅተው ተሰተዋል፡፡ይህ ቡድን በተለመደው የአንብቦ መረዳት የማስተማሪያ ዘዴ እንዲማሩ ማለትም በመጀመሪያ ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀታችውን የሚቀሰቅስ የቅድመ ንባብ ጥያቄ ቀርቧል፡፡በመቀጠል እያንዳንዱን ምንባብ የማንበብ ሂደት ተግባራት ይከወናል፡፡በመጨረሻም ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የሚሰሯቸው የድህረ ንባብ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተሰተዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን መለያ የሆኑ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ጠቋሚ የሆኑ ቃላትና ሀረጋትን እንዲመልሱ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡እንዲሁም ምንባቡን

መሰረት ያደረጉ ጽሁፉ የተዋቀረበትን ብልሃት የሚጠቁሙ መልመጃዎች ተካተው ተሰተዋል፡፡

## 3.7. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ከናሙና ምርጫና ከመረጃ መሰብሰብ ቀጥሎ የመረጃ ትንተና ለጥናቱ ውጤት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡መረጃ ትንተናው የተጠቀመው በቅድመና በድህረ ትምህርት በፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡትን የጥናቱ መረጃዎችን በጥራት በመያዝ ትክክለኝነቱን ለማረጋገጥና መረጃው ትርጉም ሰጭ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ጥናቱ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች እና በጽሁፍ መጠይቆች የተገኙ ውጤቶችን ለማነፃፀርና ለመተንተን የአማካይ ውጤት ቀመራዊ አሃዝና ቲ-ቴስትን ተጠቅሟል፡፡መረጃዎቹም በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታቲስትክ ተተንትነዋል፡፡

በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአማካይ ውጤት እና በባዕድ/ነፃ/ንሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ትንተናው በመጀመሪያ በቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኙ የፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤቶች ከጥብቅ (ቁጥጥር) ቡድኑና ከሙከራ ቡድኑ አንፃር በንፅፅር በአማካይ ውጤት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡በመቀጠል የሁለቱም ቡድኖች ከድህረ ትምህርት ፈተናው የተገኙ የፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤቶች በንፅፅር በአማካይ ውጤትና በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልተው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንትናና የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ብልሃትን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ስለነበር የጥናቱ ትኩረት የብልሃቶችን አጠቃቀም በመፈተሽና ውጤታማነታቸውን በማረጋገጥ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ማጎልበት ነው፡፡ስለዚህ ለጥናቱ አጋዥነት አላቸው ተብለው የተሰበሰቡ መረጃዎች በዚህ ክፍል ተተንትነዋል፡፡የጥናቱ መረጃዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችና በጽሁፍ መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች በሁለት ቡድን የተከፈሉ በመሆናቸው ትንተናውም የተደረገው በሁለት ምድብ ነው፡፡በመጀመሪያ የሁለቱን ቡድን የችሎታ ተመሳሳይነት ወይም አቻነት ለማወቅ የተሰጠው የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡እንዲሁም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጉልህነት ልይይት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ፍተሸ ተደርጓል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤቶች ልክ እንደ መጀመሪያው ሁሉ ለየቡድኖቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በመጨረሻም የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት በአንድነት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ቀርቧ፡፡

## 4.1.የጥናቱ ተሳታፊዎች ግለ ታሪክ መግለጫ

ይህ ንዑስ ክፍል የተሳታፊዎችን ባህርይ በዕድሜ፣በፆታ፣በትምህርት ደረጃ እና በልምድ በመመደብ የተሰጣቸውን የጽሁፍ መጠይቅ ሞልተው የመለሱ መግለጫ

### 4.1.1 ለጥናቱ ተሳታፊዎች የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች

*ሠንጠረዥ4.1 ለተሳታፊዎች የተሰጡ መጠይቆች ብዛት፣የተመለሱ መጠይቆች ብዛትና ያልተመለሱ መጥቆች ብዛት፣*

| ቁጥር | የጽሁፍ መጠይቆች | ብዛት | በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተመለሰ | 82 | 100% |
| 2 | ያልተመለሰ | 0 | 0 |
| 3 | ጠቅላላ | 82 | 100% |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

ከላይ ያለው ሠንጠረዥ 4.1 እንደሚያሳየው 82 የጽሁፍ መጠይቆች ለተሳታፊ ተማሪዎች ተሰተው 82ቱም መጠይቆች በተሳታፊዎች በአግባቡ ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡

### 4.1.2 የተሳታፊዎች ዳራ መገለጫ

*ሠንጠረዥ 4.2 የተሳታፊዎች ዳራ (በፆታ፣በዕድሜ፣በትምህርት ደረጃ እና በልምድ)*

| ቁ ር | ምድብ | | የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 1 | ፆታ | ወንድ | 34 | 41.46 | 34 | 41.46% |
| | | ሴት | 48 | 58.53 | 48 | 58.53% |
| | | ጠቅላላ | 82 | 100% | 82 | 99.99% |
| 2 | የትምህርት ደረጃ | 9ኛ ክፍል | 82 | 100% | 82 | 100% |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሠንጠረዥ፡4.2 መመልከት እንደሚቻለው የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የ(9ኛ)ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ 34 (41.46%) ወንዶች፣48(58.53%) ሴቶች በአጠቀላይ 82(100%) ተማሪዎች በዚህ ጥናታዊ ስራ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## 4.1.3 ከቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ከሙከራና ከቁጥጥርቡድኖች የተገኘ የፈተና ውጤት ትንተና

*ሠንጠረዥ፡4.3 በቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት ትንተና የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ*

| የፈተና አይነት | ተጠኝ ቡድኖች | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | የቁጥጥርቡ ድን | 12 | 34 | 42 | 20.5000 | 6.70691 | 1.035 |
| | የሙከራ ቡድን | 10 | 36 | 40 | 21.4286 | 7.61577 | 1.204 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሠንጠረዥ 4.3 እንደቀረበው የቅድመ ትምህርት ሙከራና ቡድን ቅድመ ትምህርት ቁጥጥር ቡድን ስታትስቲካዊ መግለጫ እነደሚያሳየው የቅድመ ትምህርት የቁጥጥር ቡድን ውጤት (20.5000) ከቅድመ ትምህርት የሙከራ ቡድን አማካይ ውጤት(21.4286) ተቀራራቢ ይመስላሉ፡፡ከዚህም ሌላ የመደበኛ ልይይት ውጤቶቹ ብዙም የተራራቁ ባለመሆናቸው የሁለቱም ቡድኖች በመደበኛው መማር የአንበቦ መረዳት ውጤታቸው ከየአማካዮቻቸው ያላቸው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላከታል፡፡

ይህም በሁለቱም የጥናት ቡድኖች የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ከየአማካያቸው ተመሳሳይ ርቀት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ሁለቱ የቅድመ ትምህርት ፈተና የቡድን አማካይ ውጤቶቻቸው ሲታዩ የሙከራ ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ በ(0.92) ብልጫ እንዳለው በሠንጠረዥ፡4.3 የሰፈረው መረጃ ያመላክታል፡፡ሆኖም የአማካይ ውጤቶቻቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት በእርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል፡፡በመሆኑም በቅድመ ትምህርት ፈተና የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ

ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በሠንጠረዥ 4.4 እኩል ልዩነት መኖር አለመኖሩን በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.4.የቅድመ ትምህርት የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች አማካይ ውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| | | የልይይት ደረጃ ሙከራ ለቫሪያስ እኩልነት | | ቲ-ቴስት ለእኩልነት አማካይ ውጤት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ | ጉልህነት | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት | የአማካይ ልዩነት | መደበኛ ስህተት ልዩነት | 95%የስህተት ይሆንታ ልዩነት | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | እኩል ቫሪያንስ ሲታሰብ | .53 | .466 | .677 | 80 | 0.500 | 1.071 | 1.583 | 4.221 | 2.078 |
| | እኩል ቫሪያንስ ሳይታሰ | | | .675 | 77.613 | 0.502 | 1.071 | 1.588 | 4.233 | 2.09 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሠንጠረዥ፡4.4 እንደቀረበው የልይይት ደረጃ ሙከራ ለቫሪያስ እኩልነት (Sig. 0.466) ከጉልህነት ደረጃ መቁረጫ (Level of significance) 0.05 የበለጠ በመሆኑ እኩል ልይይት ሲታሰብ የሚታየውን መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ስለሆነም እኩል ቫሪያንስ ሲታሰብ የሚያሳየው መረጃ፣ጉልህነት (በባለሁለት ጫፍ) (Sig.2 tailed 0.500) ከጉልህነት ደረጃ ከመቁረጫ ነጥብ (Level of significance) (0.05) የበለጠ በመሆኑ ውጤቱ በሁለቱ የተጠኚ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡በዚህም መሰረት በቅድመ ትምህርት የተጠኚዎች ቡድን ችሎታ በሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል የአማካይ ልዩነቱ 1.071 ቢሆንም ብዙም የጎላ አለመሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.5 የሙከራ ቡድን የቅድመና ድህረ ፈተና አመካኝ ውጤት ንፅፅር
በጥንድ ንሞና ስታቲስቲክስ

| የተጠኝ ቡድን | | አማካይ ውጤት | የናሙና ብዛት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | የሙከራ ቡድን ድህረ ፈተና | 27.80 | 40 | 7.101 | 1.123 |
| | የሙከራ ቡድን ቅድመ ፈተና | 21.50 | 40 | 7.616 | 1.204 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሠንጠረዥ፡4.5. እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት በቅድመ ፈተና 21.50፤መደበኛ ልይይት 7.616 ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ደግሞ 27.80 አማካይ ውጤትና 7.101 መደበኛ ልይይት አሳይቷል፡፡ይህም በአማካይ ነጥብ የ6.3 (21.50 _27.50) አማካይ ነጥብ ልዩነትና የ0.51 መደበኛ ልይይት ተመዝግቧል፡፡ይህ ደግሞ የሚያሳየው ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ይልቅ በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የላቀ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ይህ የመጣው በብልሃት ከተማሩ በኋላ ስለሆነ በጽሁፍ ብልሃት መማር አንብቦ መረዳትን ማጎልበት ይቻላል ማለት ነው፡፡ለቡድኑ በሁለት አማካይ ውጤቶች የታየው ልዩነት ጉልህነት እንዳለው ወይም እንደሌለው ለማረጋገጥ መረጃው በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት በሠንጠረዥ 4.6 እንደሚታየው ተሰልቶ ውጤቱ በነጻነት የጉልህነት ደረጃ ቲ(40)=0.000 ከመቅረጫ ነጥብ 0.05 ስለሚያንስ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ የጎላ ልዩነት እንዳለ አመልክቷል፡፡በሠንጠረዥ 4.6 እንደተመለከተው፡፡

ሠንጠረዥ፡-4.6 የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አማካይ ውጤቶችንፅፅር በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት

| ተጠኝዎች | | ጥንድ ልይይት (Paired Differences) | | | | | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የስህተት የይሆንታ ልዩነት | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| Pair 1 | የሙከራ ቡድን ድህረ ፈተና<br>የሙከራ ቡድን ቅድመ ፈተና | 6.300 | 8.540 | 1.350 | 3.569 | 9.031 | 4.666 | 39 | .000 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በመቀጠል የቀጥጥር ቡደኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤቶች መካከል ልዩነት ስለመኖርና አለመኖሩን የቡድኑ የሁለት ጊዜ ፈተና አማካይ ውጤቶች፣መደበኛ ልይይት፣የጉልህነት ደረጃ በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስና በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት የተገኙ ውጤቶች ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.7 የቁጥጥር ቡድን የቅድመና ድህረ ፈተና አማካይ ውጤት ንፅፅር በጥንድንሙና ስታቲስቲክስ

| ተጠኝዎች | | አማካይ ውጤት | የንሙና ብዛት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | የቁጥጥር ቡድን ድህረ ፈተና | 20.90 | 42 | 6.609 | 1.023 |
| | የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ፈተና | 20.43 | 42 | 6.707. | 1.035 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች በፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤ በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

ከላይ በሰንጠረዥ፡-4.7 እንደሰፈረው የቁጥጥር ቡደኑ የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት በንፅፅር ሲታይ ቅድመ ትምህርት ፈተና አመካይ ውጤት 20.43 መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 6.707 ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 20.90፣መደበኛ ልይይቱ 6.609 መሆኑ ተመልክቷል፡፡የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት አመካይ ውጤት ጋር ሲነፃፀር በ0.47 በልጦ ታይቷል፡፡ከቅድመ ትምህርት ይልቅ በድህረ ትምህርት ከፍ ያለ የአመካይና የመደበኛ ልይይት ውጤት መገኘቱ የቡድኑ ተሳታፊዎች በድህረ ትምህርት የአንብቦ

መረዳት ውጤታቸው መቀራረቡን ያሳያል፡፡በበድኑ አማካይ ውጤቶች መካከል የታየን ልዩነት የበለጠ ለማረጋገጥ በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት መፈተሽ አስፈላጊ ስለሚሆን በሚቀጥለው ሰንጠረዥ፡4.8 ተተንትኗል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.8 የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት

| ተጠኝዎች | | የጥንድ ልይይት (Paired Differences) | | | | | የቲ-ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አመካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የስህተት የይሆንታ ልዩነት | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| Pair 1 | የቁጥጥር ቡድንድህረ ፈተና<br>የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ፈተና | 476 | 9.954 | 1.536 | 2.626 | 3.578 | .310 | 41 | .758.000 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሰንጠረዥ 4.8 እንደተመለከተው የቁጥጥር ቡድኑ በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል የታየው ልዩነት ጉልህነት እንዳለውና እንደሌለው ለማረጋገጥ መረጃው በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በነጻነት ደረጃ (42) የቲ ዋጋ 0.310 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 በልጦ ሰለተገኘ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ተምህርት የአንብቦ መረዳት ውጤቶች መካከል በስታቲስቲካዊ መረጃ የጎላ ልዩነት እንደሌለ አመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ4.9 የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ፈተና ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ

| ተጠኝዎች | የፈተና ዓይነት | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ ቡድን | ድህረፈ.ተና | 40 | 27.80 | 7.101 | 1.123 |
| ቁጥጥር ቡድን | | 42 | 20.90 | 6.609 | 1.101 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

በሰንጠረዥ፡4.9. እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት በተደገፈ፣ ቁጥጥር ቡድኑ በብልሃት አልባ (በተለመደው) የአንብቦ መረዳት ትምህርት ከተማሩ በኋላ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን ለማረጋገጥ የማረጋገጫ ፈተና ተሰቷል፡፡ቡድኖቹ በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 27.80፣መደበኛ ልይይት 7.101 ሲሆን፣የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 20.90፣መደበኛ ልይይት 6.707 ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

በቡድኖቹ መካከል ከአንብቦ መረዳት የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በኋላ ልዩነት እንዳለ ከላይ በሰንጠረዥ የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ይሁን እንጂ ይህን ሐሳብ በዚህ ብቻ ማጠቃለል የመረጃው ታማኒነት ስለሚያሳንሰው የበለጠ ለማጉላት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.10 የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖች ድህረ ፈተና ውጤት ንፅፅር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples Test)

| ተጠኚ ዎች | የፈተና ዓይነት | በእኩል ልይይት የጉልህነት ፍተሻ | | የእኩል አማካይ ውጤት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ | ጉልህነት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ | አማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95% የስህተት ይሆንታ ልዩነት | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ሙከራ | ድህረ ፈተና | .246 | .-621 | 4.55 | 80 | .000 | 4.489 | 6.895 | 9.913 | 3.878 |
| ቁጥጥር | | | | 4.54 | 78.90 | .000 | 4.489 | 6.895 | 9.918 | 3.872 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከፈተና የተገኘ (2011) ዓ.ም በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች*

ከላይ ባለው ሰንጠረዥ 4.10 እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ በአንብቦ መረዳት ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ አንጻር ያመጣው ውጤት ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ይኸውም በ0.000 ባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ በ80 የነጻነት ደረጃ (Df) የቲ ዋጋ 4.55 ነው፡፡የቲ-ዋጋ ከቲ የሰንጠረዥ ዋጋ (1.980) በልጦ ተገኝቷል፡፡የጉልህነት ደረጃውም 0.000 ከመቁረጫ ነጥብ

0.05 ያንሳል፡፡በዚህ ስታቲስክሳዊ መረጃ መሰርት በናሙናነት የተመረጡት ተማሪዎች የሙከራ ትምህርት ከተማሩ በኋላ በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት ተስተውሏል፡፡ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳዳበረ ነው፡፡በሁለቱ ቡድኖች በድህረ ትምህርት ፈተና ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤታች የበለጠ ውጤት ተመዝግቧል፡፡መበላለጡ ግን በጣም የተለያየ ነው፡፡አንብቦ መረዳትን በብልሃት የተማረው ቡድን የበለጠ ውጤት ሲያስመዘግብ፣በብልሃት አልባ የተማሩት ግን ያለው ለዩነት ያን ያህል የጎላ አይደለም፡፡ይህ የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ በብልሃት መማሩ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዲያዳብር አድርጎታል፡፡

## 4.1.4 ከቁጥጥር ቡድንና ከሙከራ ቡድን በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ከተሳታፊዎች የተገኘ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ጥያቄ በምንባብ ውሰጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማጎልበት ማስቻል አለማስቻሉን በአንደኛ ደረጃ፣የጽሁፍ ችሎታን ማዳበር ያስችል እንደሆነ መፈተሽ በሁለተኛ ደረጃ ይዞ የተነሳ ጥናት ነው፡፡ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ደግሞ መረጃ ማሰባሰብ የጥናቱ ዋና አካል ነው፡፡መረጃ ለመሰብሰብ ስራ ላይ ከዋሉ መሳሪያዎች አንዱ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

የጽሁፍ መጠይቅ መስጠት ያስፈለገው አንድ ምንባብ (ጽሁፍ) በሚዘጋጅበት ጊዜ በጽሁፍ ውስጥ ያሉ ሐሳቦች ትስስር የተዋቀሩበትን ወይም የተጻፉበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ቀደም ሲል ማወቅ አለማወቃቸውን ለመፈተሽና የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን መማር አንድን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ያለውን አስተዋጽኦ ለመመርመር ሲባል የተሰጠ ነው፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተና መስጠት ያስፈለገው የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለ አንብቦ መረዳት እና በምንባብ ውስጥ ያሉ ሐሳቦች በምን አይነት የጽሀፍ አወቃቀር ብልሃት ተሰናስነው እንደ ቀረቡ ምን ይህል እነደሚያውቁ የቀደመ እውቀታቸውን ለመፈተሽና ለማረጋገጥ ነው፡፡

ሠንጠረዥ፡-4.11 የሙከራ ቡድኑ (Experimental Group) በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እሰማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ጭራሽ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % |
| 1 | ማንኛውንም ጽሁፍ ያለምንም ችግርማንበብ እና የሚያሰተላልፈውን መልዕክት በአግባቡ መረዳት እችላለለሁ፡፡ | 12 | 30 | 16 | 40 | 7 | 17.5 | 5 | 12.5 |
| 2 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለን ዋና እና ዝርዝር ሐሳቦችን ለይቶ ለማውጣት አልቸገርም፡፡ | 15 | 37.5 | 18 | 45 | 5 | 12.5 | 2 | 5 |
| 3 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት የተለያዩ የንባብ ብልሃቶችን እጠቀማለሁ፡፡ | 4 | 10 | 7 | 17.5 | 19 | 47.5 | 10 | 25 |
| 4 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት ምንም አይነት የንባብ ብልሃት አልጠቀምም፡፡ | 10 | 25 | 19 | 47.5 | 6 | 15 | 5 | 12.5 |
| 5 | አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በማነብበት ጊዜ ጽሁፉ በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንደተዋቀረ መለየት እችላለሁ፡፡ | 5 | 12.5 | 7 | 17.5 | 20 | 50 | 8 | 20 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን ትርጉም /ፍች/ በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍብልሃት ማወቅ እችላለሁ፡፡ | 8 | 20 | 13 | 32.5 | 14 | 35 | 5 | 12.5 |
| 7 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እገዛ እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ | 11 | 27.5 | 18 | 45 | 8 | 20 | 3 | 7.5 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ከአነበብኩት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያለምንም ችግር መመለስ እችላለሁ፡፡ | 10 | 25 | 18 | 45 | 7 | 17.5 | 5 | 12.5 |
| 9 | ያነበብኩትን ጽሁፍ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ያለምንም ችግር አሳጥሬ መናገርና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 4 | 10 | 4 | 10 | 20 | 50 | 12 | 30 |
| 10 | አንበቦ መረዳትን ለማፋጠን ከሚያግዙ የጽሁፍ ብልሃቶች አንዱ የጽሁፍ መዋቅር ብልሃትን ማወቅ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ | 6 | 15 | 10 | 25 | 15 | 47.5 | 9 | 22.5 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሰንጠረዥ 4.11 እንደተመለከተው መጠይቁን ከሞሉት 40 ተማሪዎች ለቁጥር አንድ የሰጡት ምላሽ 12(30%) እና 16(40%) የሚሆኑት መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ይህ የሚያሳየው ደግሞ 70% የሚሆኑት አቀላጥፌው ማንበብና ያነበቡትንም መረዳት እንደሚችሉ ያሳያል፡፡30% የሚሆኑት ደግሞ እንደማይስማሙ ጠቁመዋል፡፡ይህ ምላሽ ካሉበት የክፍል ደረጃ አንጻር ትክክል ሊሆን ይችላል ይሆናል፤በክፍል ውስጥ የሚታየው ሐቅ ግን ይህ አይደለም፡፡ ከዚህ ምላሽ አንጻር ማለት የሚቻለው ምናልባትም ተማሪዎች ስለ አቀላጥፎ ማንበብና አንብቦ መረዳት የግንዛቤ ክፍተት ሳይኖር አይቀርም ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ሁለት የሰጡት ምላሽ ደግሞ 15(37.5%)፣18(45%) በድምሩ 82.5% በሚያነቡት ጽሁፍ ውሰጥ ያለን ዋና እና ዝርዝር ሐሳብ ለይተው ማውጣት እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡5(12.5%) እና 2(5%)የሚሆኑ ተሳታፊዎች እንደማይስማሙ አሳይተዋል፡፡ ይህ የተማሪዎች ምላሽ የሚያመለክተው እየተማሩበት ያለው የአንብቦ መረዳት የጽሁፍን ዋናና ዝርዝር ሐሳብ ለይተው እንዲያወጡ በያንዳንዱ የአንብቦ መረዳት መልመጃ ስር በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ ሰለሚተገበሩት ሳይሆን አይቀርም ወደሚል መደምደሚያ ይወስደናል፡፡

ለጥያቄ ሶስት የሰጡት መልስ 6(15% እና 7(25%) እንደሚስማሙ ሲሆን፣19 (47.5%) እና 10(25%) ደግሞ የሰጡት ምላሽ እንደማይስማሙ አሳይተዋል፡፡ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አንድን ምንባብ (ጽሁፍ) ሲያነቡ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን እንደማይጠቀሙ ያሳየ ነው፡፡

ለቁጥር አራት የሰጡት ምላሽ ለቁጥር ሶስት ከሰጡት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡10 (25%) እና 19(47.5%) በጥቅሉ 29(72.5%) የሚሆኑት በሚያነቡበት ጊዜ ምንም የንባብ ብልሃት አንደማየጠቀሙ ሲያሳይ፣6(15%) እና 5(12.5%) በድምሩ (27.5%) የሚሆኑት እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡በአጠቃላይ ከዚህ ምላሽ የምንገነዘበው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የንባብ ብልሃት እንደማይጠቀሙ የሚያመለክት ነው፡፡

ለቁጥር አምስት የሰጡት መልስ ደግሞ 20(50%) እና 8(20%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጽሁፍ ውስጥ ጽሁፉ በምን አይነት የጽሁፍ ውቅር ብልሃት እንደተዋቀረ እንደማያውቁ ሲመልሱ፣5(12.5%) እና 7(17.5%) መለየት እንደሚችሉ አሳይዋል፡፡ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው 70% የሚሆኑት አንድ ምንባብ በምን አይነት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እነደተዋቀረ እንደማያውቁ አመልክቷል፡፡ይህ ምላሽ ተሳታፊዎቹ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ተምረው እንደማያውቁ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ተሳታፊዎች ለተራ ቁጥር ስድስት የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው 8(20%) እና 13(32.5%) የሚሆኑት በመጠይቁ ሐሳብ መስማማታቸውን ሲገልጹ፣14(42.5%)እና 5(12.5%) የሚሆኑት ደግሞ እንደማይስማሙ ጠቁመዋል፡፡ለጥያቄ ስድስት የተሰጠው መልስ ከሁለቱም አቅጣጫ የተቀራረበ ምላሽ ቀርቧል፤ይሁን እንጂ 57.5% የሚሆኑት አለመስማማታቸውን አሳይተዋል፡፡ምንም እንኳን በመደበኛው የአንብቦ መረዳት ትግበራ ወቅት ፍንጭ ሰጭ ቃላትና ሀረጋትን ሳይጠቀሙ እንዳልቀሩ ቢያመለክትም ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ግን ግንዛቤ እንደሌላቸው የሚያመለክት ይመስላል፡፡

ለቁጥር ሰባት የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው 11(27.5%) እና 18(45.5%) የሚሆኑት እንደሚሰማሙ ሲያመለክት 29(82%) እና 3 (7.5%)የሚሆኑት እንደማይስማሙ አመልክተዋል፡፡በዚህ መጠይቅ ስር አብዛኛው ተማሪ መስማማቱ አዎንታዊ ይመስላል፣ ምክንያቱም በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ በያንዳንዱ የአንብቦ መረዳት ምንባብ ስር እነዚህ

መልመጃዎች የማይቀሩ ተግባራት በመሆናቸው ከዚህ በመነሳት የተሰጠ ምላሽ ስለሆነ ተገንዝበውት የሰጡት ምላሽ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ለጥያቄ ሰምንት የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው 10(25%) እና18(45) የሚሆኑት መስማማታቸውን ሲያሳዩ፣ 7(17.5%) እና 5(12.5%) እንደማይስማሙ ያመለክታል፤ያም ሆኖ 70% የሚሆኑ መላሾች ተስማምተዋል፡፡ይህ የሚያሳየው ደግሞ በመደበኛው የመማር ሂደት በብዛት የሚተገበር ሰለሆነ መላሾቹ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ግንዛቤው እንዳላቸው መገንዘብ ያቻላል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ የተሰጠው መልስ እንደሚያመለክተው 4(10%) እንደሚስማሙ፣20(50%) እና 12(30%) የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት የመጨረሳን ግብ ወይም ማጠቃለያን መተግበር እንደማይችሉ አብዛኛዎቹ መላሾች ሰላረጋገጡ በአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ላይ ችግር እንዳለ ያመለከተ ነው፡፡

ለጥያቄ አስር የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው 6(15%) እና 10 (25%) የሚሆኑት አዎንታዊ መላሽ ሲሰጡ15(47.5%) እና 9(22.5%) የሚሆኑት ደግሞአሉታዊ ምላሽ ሰተዋል፡፡በዚህ ምላሽ መሰረት ከላይ በጥያቄ ቁጥር 3፣4፣5፣6 እና 9 ከተሰጡ ምለሾች ጋር ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ይህ የሚያመለክተው ደግሞ ተማሪዎች እስከ አሁን ባለው ሁኔታ አንድ ጽሁፍ በምን አይነት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንደተዋቀር እንደማያውቁትና እንዳልተማሩ አመልካች ነው፡፡ይህ ደግሞ የጥናቱን ጥያቄ መነሻ ችግር ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ ትምህርት ፈተና በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ  የተጠኚው ቡድን መላሾች ሲጠቃለሉ በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡የመጀመሪያው ለጥያቄ ቁጥር 1፣2፣7፣8 የተሰጡትን መልሶች ስንመለከት ተሳታፊዎች እስከ አሁን እየተማሩ ያሉበትን የማስተማሪያ ዘዴ መሰረት አድርገው መሆኑን ያመለከተ ነው ማለት ይቻላል፡፡ምክንያቶቹ ከላይ በያንዳንዱ ጥያቄዎች ስር ተብራርቷል፡፡ሁለተኛው ጥያቄ ቁጥር 3፣4፣5፣6፣9፣10 በቀጥታ ከጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው የተማሪዎች መልስም እስከ አሁን ባለው ሁኔታ በምንባብ ውስጥ ሰላለ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች እንደማያውቁ አሳይቷል ፡፡

ሠንጠረዥ፡4.12 የቁጥጥር ቡድን (Control Group) የቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ጭራሽ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % |
| 1 | ማንኛውንም ጽሁፍ ያለምንም ችግር ማንበብ እና የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአግባቡ መረዳት እችላለለሁ፡፡ | 13 | 30.1 | 19 | 45.2 | 7 | 16.7 | 4 | 9.5 |
| 2 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለን ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ለይቸ ለማውጣት አልቸገርም፡፡ | 14 | 33.3 | 18 | 42.9 | 7 | 16.7 | 3 | 7.1 |
| 3 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት የተለያዩ የንባብ ብልሃቶችን እጠቀማለሁ፡፡ | 5 | 11.90 | 7 | 16.7 | 18 | 42.9 | 13 | 30.5 |
| 4 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት ምንም አይነት የንባብ ብልሃት አልጠቀምም፡፡ | 11 | 26.2 | 15 | 35.7 | 12 | 28.6 | 4 | 9.5 |
| 5 | አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በማነብበት ጊዜ ጽሁፉ በየትኛው የጽሁፍ ውቅር ብልሃት እንደተዋቀረ መለየት እችላለሁ፡፡ | 3 | 7.1 | 8 | 19.04 | 23 | 54.8 | 8 | 19.04 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን ትርጉም /ፍች/ በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍ ብልሃት ማወቅ እችላለሁ፡፡ | 7 | 16.7 | 10 | 23.8 | 18 | 42.9 | 7 | 16.7 |
| 7 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡንመልዕክት ለመረዳት እገዛእንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ | 13 | 31 | 19 | 45.23 | 7 | 16.7 | 3 | 27.14 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ከአነበብኩት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያለምንም ችግር መመለስ እችላለሁ፡፡ | 13 | 31 | 14 | 33.3 | 10 | 23.8 | 5 | 11.9 |
| 9 | ያነበብኩትን ጽሁፍ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ያለምንም ችግር አሳጥሬ መናገርና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 4 | 9.5 | 6 | 14.3 | 18 | 42.9 | 14 | 33.3 |
| 10 | አንበቦመረዳትን ለማፋጠን ከሚያግዙየጽሁፍ ብልሃቶች አንዱ የጽሁፍ መዋቅር ብልሃትን ማወቅ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ | 7 | 16.7 | 10 | 23.8 | 21 | 50 | 4 | 9.5 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጸሀፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንጠረዥ፡4.12 መመልከት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ የሰጡት ምላሽ ለቁጥር አንድ 13(31%) እና 19(45.2%) የሚሆኑ መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ፣7(16.7%) እና 4(9.5%) የሚሆኑት ደግሞ እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡በዚህ ምላሽ መሰረት አብዛኛው ተሳታፊ 76.2% አቀላጥፎ ማንበብና ያነበቡትንም መረዳት መቻላቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ ምላሽ ከተጠኚው ቡድን መላሽ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው፡፡በዚህ መሰረት በተየጠኚው ቡድንና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ምንም የችሎታ ልይይት እንደሌለ አሳይቷል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ሁለት ተሳታፊዎች የተሰጠውን መልስ ሲገመግም የአብዛኛው 75% ምላሽ እንደሚሰማሙ ሲጠቁሙ፣25% የሚሆኑት እንደማይስማሙ አሳውቀዋል፡፡ይህ የተሳታፊዎች ምላሽ ከሙከራ ቡድን ምላሽ ጋር ተመሳይ ነው፡፡ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ከድህረ ትምህርቱ ፈተና በፊት ምንም ያህል የችሎታ ልይይት አለመኖሩን አመላካች ነው፡፡

በጥያቄ ቁጥር ሶስት 18(42.9%) እና 15(35.7%)፣በጥያቄ ቁጥር አራት 15(35.7%) እና 11(26.2%)፣ በጥያቄ ቁጥር አምስት 23(54፣8%)እና 11(26.2%)፣በጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ 18 (42.9%) 14(33.3%) እንዲሁም ለጥያቄ ቁጥር አስር 27(64.5%) እና 8(19%) በሰጡት መልስ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ከምንባብ ጋር ተያይዞ እንድን ምንባብ (ጽሁፍ) በሚያነቡበትጊዜ ከጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች ጋር ትውውቅ እንደሌላቸው አረጋግጠዋል፡፡

በሌላ በኩል ለጥያቄ ሰባት 13(31%) እና 25(59.5%)፣ለጥያቄ ቁጥር ስምንት 13(31%) እና 14 (33.3%) የሚሆኑ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ አዎንታዊ ሲሆን፣3(7.1%) እና 1(2.4%)፣10 (23.8%) እና 5(11.9%) እንደ ቁጥሮቹ ቅደምተከተል እንደማስማሙ ገልጸዋል፡፡የእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች መልሶች ሲጠቃለል የአብዛኛው ተሳታፊ ምላሽ አዎንታዊ ነው፡፡ይህ የሚጠቁመው ደግሞ ተማሪዎች እነዚህን ተግባራት በመደበኛው የመማር ሂደት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን ሲሰሩ ስለሚለማመዱቸው ይመስላል፡፡

ለጥያቄ ስድስት ተሳታፊዎች የሰጡት መልስ አምሳ አምሳ ነው፡፡50% እንደሚስማሙ 50% እንደመይስማሙ ገልጸዋል፡፡ይህ ምላሽ ከተጠኚው ቡድን መላሽ ጋርም የተወሰነ ልዩነት አለው ፡፡ልዩነቱ ግን የተጋነነ ስላልሆነ ‹‹በሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትንና ሀረጋትን ፍች በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍ ብልሃት መረዳት እችላለሁ››የሚል ስለሆን የተገነዘቡበት መንገድ ከምንባቡ ከወጡ ጥያቄዎች ከመመለስ አኳያ ሰለሚመስል ምላሻቸው ትክክል ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ የቁጥጥር በቡድን ምለሽን ሲጠቃለል ለጥያቄ ቁጥር 1፣2፣7፣8 ተመሳሳይ ሲሆን፣ምላሻቸውም አዎንታዊ ነው፡፡የተሳታፊዎች ምላሽ አዎንታዊ የሆነው ለተጠኚው ቡድን ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ይህም በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ ተማሪዎች በመደበኛው የመማር ሂደት በአንብቦ መረዳት ትግበራ ጊዜ ስለሚማሩት ነው ብሎ ማጠቃለል ዕንደሚቻል ያመለክታል፡፡

ለጥያቄ 3፣4፣5፣6፣9 እና10 የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው በምንባብ ውስጥ ስላለ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እውቀቱ እንደሌላቸው የሚያመለከት ነው፡፡ይህ ደግሞ ከተጠኚው ብድን ምላሽ ጋር ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ተመሳሳይ ነው፡፡ይህ የሚያሳየው ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም የችሎታ ልይይት አለመኖሩን ነው፡፡

የቁጥጥር እና ተጠኚው ቡድን ተሳታፊዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና ወቅት ለቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ 90% ተመሳሳይ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ይህ ደግሞ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የቀደመ እውቀት ወይም ችሎታ ተመጣጣኝ መሆኑን ነው፡፡ይህን ሐሳብ ለማጠናከር በገላጭ እሰታቲስተክ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ተብራርቷል፡፡

ሰንጠረዥ፡4.13 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ

| የፈተና ዓይነት | ተጠኚ ቡድን | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 42 | 2.64 | .284 | .044 |
| | የሙከራ ቡድን | 40 | 2.60 | .300 | .047 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንጠረዥ፡4.13 እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው አማካይ ውጤት (2.60) እና መደበኛ ልይይት (0.300) ከቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 2.64 እና መደበኛ ልይይት 0.284 መካከል ምንም የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡የሁለቱ ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ውጤት ከየአማካያቸው ያለው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ የአማካይ ውጤታቸውን ብቻ በማየት በመካከላቸው ያለውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በእርግጠኝነት መናገር ስለሚያስቸግር ልዩነታቸውን ለማረጋገጥ በስታቲስካዊ ስሌት ማስላት አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ መሰረት በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ መረጃውን በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት በመቀጥለው ሠንጠረዥ 4.14 ተሰልቷል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.14 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ

| ተጠኚ ቡድን | የፈተና ዓይነት | በእኩል ልይይት የጉልህነት ፍተሻ | | የእኩል አማካይ ውጤት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ | ጉልህነት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ | አማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልይይት | 95% የስህተት ይሆንታ ልዩነት | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ሙከራ | ቅድመ ፈተና | .372 | .544 | 631 | 80 | .530 | .041 | .064 | .088 | .169 |
| ቁጥጥር | | | | 630 | 79.096 | .530 | .041 | .065 | .088 | .169 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንጠረዥ፡4.14 እንደተመከተው የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርት በአንብቦ መረዳት ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ አኳያ ያመጠው ነጥብ ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል ፡፡በ(.530) የጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ በ(80) የነፃነት ደረጃ (Df) የቲ-ዋጋ 0-631 ነው፡፡የጎልህነት ደረጃውም( 0.544) ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 ይበልጣል፡፡በዚህ ስታቲስከሳዊ መረጃ መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.15. የሙከራ ቡድን (Experimental Group) የድኅረ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እሰማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ጭራሽ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | % | ድግግሞ | % | ድግግሞ | % | ድግግሞ | % |
| 1 | ማንኛውንም የማነበውን ጽሁፍ ያለምንም ችግር ማንበብ እና የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአግባቡ መረዳት እችላለሁ፡፡ | 18 | 45 | 17 | 42.5 | 4 | 10 | 1 | 2.5 |
| 2 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለን ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ለይቸ ለማውጣት አልቸገርም፡፡ | 18 | 45 | 20 | 50 | 2 | 5 | - | - |
| 3 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት የተለያዩ የንባብ ብልሃቶችን እጠቀማለሁ፡፡ | 10 | 25 | 20 | 50 | 6 | 15 | 4 | 10 |
| 4 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት ምንም አይነትየንባብ ብልሃት አልጠቀምም፡፡ | 6 | 15 | 7 | 17.5 | 17 | 42.5 | 10 | 25 |
| 5 | አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በማነብበት ጊዜ ጽሁፉ በየትኛው የጽሁፍ ውቅር ብልሃት እንደተዋቀረ መለየት እችላለሁ፡፡ | 15 | 37.5 | 17 | 42.5 | 5 | 12.5 | 3 | 7.5 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን ትርጉም (ፍች) በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍ ብልሃት ማወቅ እችላለሁ፡፡ | 15 | 37.5 | 17 | 42.5 | 7 | 17.5 | 1 | 2.5 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋትን ማወቅ የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እገዛ እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ | 20 | 50 | 20 | 50 | - | - | - | - |
| 8 | ከአነበብኩት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያለምንም ችግር መመለስ እችላለሁ፡፡ | 23 | 57.5 | 12 | 30 | 4 | 10 | 1 | 2.5 |
| 9 | ያነበብኩትን ጽሁፍ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ያለምንም ችግር አሳጥሬ መናገርና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 13 | 32.5 | 17 | 42.5 | 8 | 20 | 2 | 5 |
| 10 | አንበቦ መረዳትን ለማፋጠን ከሚያግዙ የጽሁፍ ብልሃቶች አንዱ የጽሁፍ መዋቅር ብልሃትን ማወቅ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ | 25 | 57.5 | 11 | 27.5 | 1 | 2.5 | 3 | 7.5 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንረዥ፡4.15 መመልከት እንደሚቻለው በጥያቄ አንድ ለቀረበው ጥያቄ የስምምነት ምላሽ የሰጡት 35(87.5%)፣ለጥያቄ ቁጥር ሁለት 38(95%)፣ለጥያቄ ቁጥር ሰባት 32(80%)፣ለጥያቄ ቁጥር ሰምንት 35(87.5%) የሚሆኑ ተሳታፊዎች መስማማታቸውን ሲረጋግጡ እንደማይስማሙ የገለጹ ተሳታፊዎች ዝቅተኛ ሰለሆኑ አብዛኛው መላሽ ተስማምቷል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ይህ ምላሽ በቅድመ ትምህርት ከተሰጠው ጋር ተቀራራቡነት እንዳለው ያሳያል፤ይሁን እንጂ ልዩነት የለም ማለት አይደለም፣በቅድመ ትምህርት ፈተናወቅት ለጥያቄ አንድ የስምምነት ምላሽ የሰጡት 28(70%) ሲሆን፣ከድህረ ፈተና በኋላ የሰጡት 32(80%) የሚሆኑናቸው፡፡ለጥይቄ ሁለትም በቅድመ ትምህርት ፈተና የሰጡት33(82.5%) ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ደግሞ 38(95%) ነው፡፡ለጥያቄ ሰባት በቅድመ ትምህርት ፈተና የሰጡት 29(72.5%)ሰሆኑ፣በድህረ ፈተና የሰጡት ደግሞ 40(100%) ናቸው፡፡በቅድመ ትምህርት የተሰጠው ምላሽ 28(70%)፣በድህረ ፈተና ደግሞ 35(87.5%) የሚሆኑ መስማማታቸውን ሰለገለጹ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ይልቅ በድህረ ትምህርት ፈተና የሰጡት ቁጥር የላቀ ስለሆነ ለውጥ ታይቷል፡፡ይህ ደግሞ የሚያሳየው ተሳታፊዎቹ ከብልሃት ትምህርት በኋላ መሻሻል እንዳሳዩ ነው፡፡

በሌላ በኩል ለጥያቄ ቁጥር 3፣4፣5፣6፣9፣10 የተሰጡ ምላሾች በቅድመ ትምህርት ከተሰጡ ምላሾ ጋር ሲነጻጸር ሙሉ በሙሉ ለውጥ ታይቷል፡፡እንዳንዱን እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡ ለጥያቄ ሶስት ስምምነታቸውን የገለጹት 30(75%) ሲሆኑ፣ያልተስማሙት ደግሞ 10(25%) ናቸው፡፡ለዚህ ጥያቄ በቅድመ ትምህርት ፈተና ጊዜ የተሰጠው የስምምነት መልስ 11(27.5%) ሲሆን፣አልስማማም ደግሞ 29(72.5) ነበር፡፡ይህን በንፅፅር ስናየው ከድህር ትምህርት ፈተና በኋላ የተሰጠው ምላሽ ሙሉ ለሙሉ ተቀይሯል ማለት ይባላል፡፡ ለጥያቄ አራት የእሰማማለሁ መልሳቸውን የሠጡት29(72.5) ሲሆኑ፣11(27.5)የሚሆኑ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ለዚህ ጥያቄ በቅድመ ትምህርት ፈተና ጊዜ 29(72.5%) የእስማማለሁ መልስ ሲሆን፣አልስማማም ደግሞ 11(27.5%)ነበር፡፡ በድህረ ትምህርት እስማማለሁ ያሉት13(32.5% ሰሆኑ፣27(67.5%) ናቸው፡፡ይህ የሚያሳየው ሙሉ በሙሉ መለወጡን ነው፡፡ለጥያቄ አምስት ስምምነታቸውን የሰጡት 32(80%)ሲሆኑ፣ያለተስማሙ 8(%)ናቸው፡፡ለዚህ ጥያቄ በቅድመ ትምህርት ፈተና ጊዜ የእስማማለሁ መልስ 12(30%)፣አልስማማም ያሉ ደግሞ 28(70%)ነበሩ፡፡ለጥያቄ ስድስት እንደሚስማሙ የገለጹ30(75%)ሲሆኑ፣10(25%) የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ለዚህ ጣያቄ በቅድመ ትምህርት ጊዜ የተሰጠው የእስማማለሁ 21(52.5%)ሲሆን አልስማማም ያሉት 19(47.5%)ነበሩ፡፡ለጥያቄ ዘጠኝ በድህረ ትምህርት ፈተና የስምምነት መልስ የሰጡት30(75%)ሲሆኑ፣ያልተስማሙትደግሞ10(25%)ናቸው፡፡ለዚህ ጥያቄ በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰተው ምላሽ ፣እስማማለሁ 8(20%)፣አልስማማም 32(80%)ነበር፡፡ ለጥያቄ አስር የተሰጠው እሰማማለሁ ምላሽ 36(90%) ሲሆን፣ያልስማማም ምላሽ የሰጡት 4(10%) ብቻ ናቸው፡፡ለዚህ ጥያቄ በቅድመ ትምህርት ፈተና ወቅት የተሰጠው ምላሽ እስማማለሁ16 (40%) ሲሆን፣አልስማማም 24(60%) ነበር፡፡

ከቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘውን የሙከራ ቡድን የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ለማጠቃለል የሁለት ጊዜውን ምላሽ በንፅፅር ሲተነተን በሠንጠረዥ4፡11 እና 4፡14 እንደተመለከተው ለጥያቄ አንድና ሁለት የተሰጡት መልሶች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ወቅት ተመሳሳይ ሲሆኑ ልዩነቱ የቁጥር መጨመር ነው፡፡በቅድመ ፈተና ተሰጠው የቁጥር አንድ 28(70%) በድህረ ፈተና ወደ35(87.5%)ከፍ ብሏል፡፡የቁጥር ሁለትም ከ33(82.5%) ወደ 38 (90%) አድጓል፡፡ይህ የሚያሳየው ከትምህርቱ በኋላ መሻሻል መኖሩንነው፡፡ይህም ለጥናቱ መነሻ ጥያቄ መልስ ሊሆን ይችላል፡፡

ለጥያቄ ሶስት በቅድመ ትምህርት ፈተና ከተሳታፊዎች የተገኘው መልስ እንደአመለከተው 11 (27.5%) መስማማታቸውን ሲያመለክት፣29 (72.5%) እንደማይስማሙ ተቁመው ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በተቃራኒው የሆነ ነው፡፡ እሱም 30 (75%) እንደሚስማሙ እና 10(25%) እነደማይስማሙ ተመልክቷል፡፡ከጥያቄ ቁጥር ሶስት መረዳት የሚቻለው ከድህረ ትምህርት በኋላ የተማሪዎች ምላሽ በአብዛኛው የሚያመለክተው በምንባብ ወይም በጽሁፍ ውስጥ የጽሁፍን ብልሃት መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከፍ እደሚያደርግ ነው፡፡በተዛማጅ ጽሁፍ ውስጥ በ2.1.3. እንደተጠቆመው በጽሁፍ ውስጥ የንባብ ብልሃት መጠቀም አንብቦ ለመረዳት እገዛ እንዳለው ያስገነዝባል (Gunnining, 2006)፡፡

ለጥያቄ አራት የተሰጠውን ምላሽ ስንገመግመው በቅድመና በድህረ ትምህርት ወቅት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መላኩ ተመሳሳይ ሰለሆነ እዚህ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ መሰጠት አስፈላጊ አይደለም፡፡የዚህን ጥያቄ ምላሽ ትንታኔ በሠንጠረዥ 4፡11 ስር መመልከት ይቻላል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር አምስት በቅድመ ትምህርት ፈተና ወቅት የተሰጠው የተሳታፊዎች መልስ 12 (30%) እንደሚስማሙ፣28(70%) የሚሆኑት ደግሞ እንደማይስማሙ ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው ምላሽ እንደጠቆመው ደግሞ 32(80%)እንደሚስማሙ ሲያመለክት፣8(20%) ብቻ ናቸው ያልተስማሙት፡፡በዚህ ጥያቄ መልስ መሰረት በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቀቀር ብልሃትን ከተማሩ በኋላ የሰጡት ምላሽ ሰለሆነ በብልሃቱ መማር በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ለውጥ መምጣቱን አሳይቷል፡፡ይህ ደግሞ የጥናቱን ዋና ጥያቄ መልሷል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ስድስት የተሰጠው መልስ እንደሚያመለክተው በቅድመ ትምህርት ፈተና 17(42.5%) የሚሆኑት መስማማታቸውን ሲገልጹ፣23 (57.5)% የሚሆኑት እንደማይስማሙ ጠቁመው ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰጠው ምላሽ ውጤት የሚያመለክተው 32(80%) የሚሆኑት ሲስማሙ 8(20%) ብቻ ናቸው ያልተስማሙት፡፡ይህ የተሳታፊዎች ምላሽ የሚያሣየው በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ከተማሩ በኋላ የሰጡት መልስ በመሆኑ በብልሃት መማራቸው የሚያነቡት ምንባብ በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንደተጻፈ ተገንዝበዋል ወደሚል ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡

ለጥያቄ ሰባት በቅድመ ትምህርት ፈተና የተሰጠው መልስ እንደሚያመለክተው 29(72.5%) እንደመሰማሙ ተሰማምተው ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና ወቅትም ይህንንው ምላሻቸውን የበለጠ ያጠናከረ ሰለሆነ የተለወጠ ነገር ስለሌለ በጽሁፍ ውስጥ የሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋትን ፍች መረዳት የምንባቡን መልክት ለመረዳት እንደሚረዳቸው የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ስምንት ተሳታፊዎች በድህረ ትምህርት ፈተና የሰጡት መልስ በቅድመ ትምህርት ከሰጡት መልስ ጋር ምንም ልይይት የለውም፡፡ይህ የሚያመላክተው በዚህ ጥያቄ የቀረበው ሀሳብ ከተለመደው የአንብቦ መረዳት ክንውን ጋራ የተዛመደ ስለሆነ በቀደመ እውቀታቸው ያዳበሩት እንደሆነ አሳይቷል፡፡

ለጥያቄ ዘጠኝ የተሰጠው የተሳታፊዎች መልስ እንደሚያሳየው በቅድመ ትምህርት ፈተና 8(20%) ብቻ እንደሚስማሙ ሲያመለክት፣ 32(80%) እንደማይስማሙ የተቆሙ ሲሆን፣ከድህረ ትምህርት ፈተናው በኋላ የሰጡት መልስ የሚያሳየው በተቃራኒው 30(75%)የሚሆኑት ሲስማሙ10(25%)የሚሆኑት ደግሞ እንደማይሥማሙ አመልክተዋል፡፡ የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚያመለክተው ከድህረ ትምህርት ፈተና በፊት ተማሪዎች ምንብብን አሳጥሮ ስለ መናገርና መጻፍ አብዛኛዎቹ ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው፡፡ከትምህርቱ በኋላ የሰጡት መልስ ደግሞ እንደሚያመለክተው ምንባብን አሳጥረው መናገርና መጻፍ እንደሚችሉ ነው፡፡ከዚህ በመነሳት ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ሁለተኛ ጥያቄ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሓትን መማር የመጻፍ ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ የሚለውን የሚመልስ ይመስላል፡፡

ለጥያቄ አስር በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ጊዜ የሰጡት መልስ በቅድመ ትምህርት ከሰጡት ከሰጡት መልስ በእጅጉ ይለያል፡፡በቅድመ ትምህርት ፈተን የስምምነት ምላሽ የሰጡት 16(40%) ሲሆኑ አለመስማማተቸውን የገለጽት ደግሞ 24(60%) ነበሩ፡፡በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በኋላ የሠጡት መልስ 36(80%) ሲስማሙ፣4(10%) ብቻ ኛቸው፡፡ይህ የሚያመላክተው ተማሪዎች ከድህረ ትምህርት አንቦቦ መረዳት ፈተና በኋላ በብልሃት መማራቸው አንብቦ መረዳትን ከሚያፋጥኑ ብልሃቶች አንዱ የጽህፍ አወቃቀር መሆኑን መረዳታቸውን ያመለክታል፡፡ይህን ከጽሁፍ መጠይቅ

የተገኘ መረጃ የበመለጠ ለማረጋገጥ ቀጥሎ በሠንጠረዥ  በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.16 የሙከራ ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤትበጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስ

| | | አማካይ ውጤት | የነሙና ብዛት N | መደበኛ ልይይት Std. Deviation | መደበኛ የስህተት አማካይ Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | የሙከራ ቡድን ድህረ ፈተና | 3.21 | 40 | .275 | .044 |
| | የሙከራ ቡድን ቅድመ ፈተና | 2.60 | 40 | .300 | .047 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጸሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

በሠንጠረዥ፡4.16 እንደተመለከተው የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና 2.60፣መደበኛ ልይይት0.300 ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ፈተና ደግሞ 3.21 አማካይ ውጤትና 0.275 መደበኛ ክፍ ብሏል፡፡ይህም በአማካይ ነጥብ 0.61 (2.60-3.21) አማካይ ነጥብ ልዩነትና የ0.25 መደበኛ ልዩነት ተመዝግቧል፡፡ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ይልቅ በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ መሻሻል አሳይቷል፡፡መሻሻሉ የመጣው በብልሃት ከተማሩ በኋላ ስለሆነ በምንብብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን መማር አንብቦ መረዳትን ማጎልበት መቻልን ያሳያል፡፡

የቡድኑን አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልይይት ብቻ በማየት ድምዳሜ ላይ መድረስ በርግጠኝነት ውጤቱ ይህ ነው ብሎ ለመናገር ይረዳ ዘንድ የመረጃውን ውጤት ለማጉላት ጉልህ ልዩነት እንደመጣና እንዳልመጣ ለማረጋገጥ በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በነፃነት ጉልህነት በለ ሁለት ጫፍ በነፃነት ደረጃ (40) 0-000 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 ያነሰ ስለሆነ የመከራ ቡድኑ በቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ውጤቶች መካከል የጎላ ልዩነት እንዳለ አመልክቷል፡፡ትንታኔውን በሰንጠረዥ 4.17 ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ፡4.17 ሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ

| የተጠኝ ቡድኖች | | የትንድ ልይይት(Paired Differences) | | | | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ከፍታ ልዩነት | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተ | | | |
| Pair 1 | ድህረ ሙከራ ቡድን<br>ቅድመ የሙከራ ቡድን | .610 | .325 | .051 | .506 | .714 | 11.87 | 39 | .000 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጸሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጸሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ሠንጠረዥ 4፡18 የቁጥጥር ቡድን (control Group) የድኅረ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እሰማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ጭራሽ አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % | ድግግሞሽ | % |
| 1 | ማንኛውንም ጽሁፍ ያለምንም ችግር ማንበብ እና የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአግባቡ መረዳት እችላለሁ፡፡ | 14 | 35 | 20 | 47.6 | 6 | 14.3 | 2 | 4.8 |
| 2 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለን ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ለይቸ ለማውጣት አልቸገርም፡፡ | 16 | 38.0 | 19 | 45.2 | 5 | 11.9 | 2 | 4.76 |
| 3 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት የተለያዩ የንባብ ብልሃቶችን እጠቀማለሁ፡፡ | 6 | 14.3 | 10 | 23.8 | 24 | 57.1 | 2 | 4.76 |
| 4 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት ምንም አይነት የንባብ ብልሃት ተጠቅሜ አላውቅም፡፡ | 13 | 31 | 17 | 40.5 | 8 | 19.0 | 6 | 14.3 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በማነብበት ጊዜ ጽሁፉ በየትኛው የጽሁፍ ውቅር ብልሃት እንደተዋቀረ መለየት እችላለሁ፡፡ | 5 | 11.98 | 8 | 19.0 | 22 | 52.38 | 7 | 16.7 |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን ትርጉም /ፍች/ በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍ ብልሃት ማወቅ እችላለሁ፡፡ | 9 | 21.4 | 15 | 40.5 | 11 | 26.19 | 7 | 16.7 |
| 7 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እገዛ እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ | 114 | 33.3 | 20 | 47.6 | 6 | 14.3 | 2 | 4.76 |
| 8 | ከአነበብኩት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያለምንም ችግር መመለስ እችላለሁ፡፡ | 14 | 33.3 | 14 | 33.3 | 10 | 23.8 | 4 | 9.52 |
| 9 | ያነበብኩትን ጽሁፍ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ያለምንም ችግር አሳጥሬ መናገርና መጻፍ እችላለሁ፡፡ | 9 | 21.1 | 6 | 14.3 | 19 | 45.2 | 8 | 19.04 |
| 10 | አንብቦ መረዳትን ለማፋጠን ከሚያግዙ የጽሁፍ ብልሃቶች አንዱ የጽሁፍ መዋቅር ብልሃትን ማወቅ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ | 18 | 19.0 | 12 | 28.6 | 16 | 38.0 | 6 | 14.28 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት /ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ለጥያቄ አንድ በቅድመ ትምህርት 32(71.9) በድህረ ትምህርት ደግሞ 34(87.6) የሚሆኑ ተሳታፊዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ፣10 (26.2) እና 8(19.1) የሚሆኑት ደግሞ አልተስማሙም፡፡ከዚህ ጥያቄ አንፃር በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውቅት የሰጡት መልስ በተወሰነ ደረጃ ከቅድመ ትምህርት ፈተና በለጧል፡፡ብልጫው ግን ያን ያህል የተጋነነ አይደለም፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ሁለት በድህረ ትምህርት ፈተና ጊዜ የተሰጠው ምላሽ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ምላሽ የቱንም ያህል አይለያይም፡፡በቅድመ ትምህርት 32(86.2) ፣በድህረ ትምህርት 37(88.2) የሚሆኑት ሲስማሙ፣10 (23.8) እና 5(11.9) የሚሆኑት አለመስማማታቸውን

ገልጸዋል፡፡ከቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ይልቅ በድህረ ትምህርት ፈተና መስማማታቸውን የገለጹት ልቀው መገኘታቸውን ያሳያል፡፡

ለጥይቄ ሶስት በቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና እንደሚስማሙ የገለጹ 12(31.5) ሰሆኑ በድህረ ትምህርት 16(42.80)፣እንደማይስማሙ የገለጹት ደግሞ በቅድመ ትምህርት 31(88.6)፣ በድህረ ትምህርት 28(61.86) ናቸው፡፡የተወሰነ መሻሻል ታይቷል፡፡ይህም የመጣው ከአንብቦ መረዳት ትምህርት በኋላ ሥለሆነ መሻሻሉ አዎንታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ይነስም ይብዛ ከትምህርቱ የተወሰነ እውቀት እንዳዳበሩ ስለሚጠቁም ነው፡፡

ለጥያቄ ቁጥር አራት በቅድመ ትምህርት እንብቦ መረዳት ፈተና እስማማለሁ ያሉት 26(61.9)፣አልስማማም ያሉት ደግሞ 16(38.1) ሲሆኑ፣በድህረ ትምህርት ፈተና እስማማለሁ ያሉት 30(76%)፣አልስማማም ያሉት ደገሞ 12(24%) ናቸው፡፡ በዚህ ጥያቄ ስርም የተወሰነ መሻሻል አሳይቷል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር አምስት በቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና እስማማለሁ ያሉ፣8 (19%)፣አልስማማም ያሉት 34(81%) ነበሩ፡፡በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ወቅት ደግሞ እስማማለሁ ያሉ፣13(31.02%) ሲሆኑ አልስማማም ያሉት፣29(68.45%) ናቸው፡፡እዚህ ላይ በቅድመ ትምህርት ፈተና ወቅት እስማማለሁ ብለው የነበሩ 8‹19) ወደ 13(31.02%) ከፍ ሲል፣አልስማማም ያሉት ደግሞ ከ34 (81%) ወደ 29 (68.45%) ዝቅ ብሏል፡፡ይህም የሚያሳየው የተወሰነ መሻሻል መኖሩን ነው፡፡

ለጥያቄ ስድስት በቅድመ ትመህረት ፈተና እስማማለሁ17(40.5%)ሲሉ፣25(50%) እንደማይስማሙገልጸዋል፡፡በድህረ ትምህርት ደግሞ እስማማለሁ 24(61.89%)፣አልስማማም 18(42.80%) የሚሆኑ ናቸው፡፡በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ከተሰጠው በድህረ ፈተና የተሰጠው ለውጥ ስላሳየ መሻሻል መኖሩን ያሳያል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ሰባት የሰጡት ምላሽ በቅድመ ፈተና እንደሚስማሙ የገለጹ 32(76.23%) ሲሆኑ፣10 (23.84%) እንደማይስማሙ ገልጸዋል፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና 34(80.93%) የሚሆኑ ሲስማሙ፣8 (19 07%) አለመስማማታቸውን ጠቁመዋል፡፡በዘህ መጠይቅ ስር የተሰጠው መልስ በሁለቱም ወቅት የተሰጠው ያን ያህል የጎላ አይደለም፡፡

ለጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና 10(23.8%)እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ፣32(76.2%) አላስማማም ብለው ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና

15(35.71%)አስማማለሁ ሲሉ፣27(64.6%)እንደማይስማሙ ጠቁመዋል፡፡በቅድመ ትምህርት ፈተና ከተሰጠው ምላሽ በድህረ ትምህርት ፈተናው የተሰጠው ምላሽ በልጧል፡፡10(23.8%) ወደ15 (35.71%) ሲያድግ፣ አልስማማም ያሉት ደግሞ 32(76›2%) ወደ 7(64.6%) ቀንሷል፡፡ይህም መሻሻል እንዳለ ያመለክታል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር አስር በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የሰጡት ምላሽ 17(40.47%) እስማማለሁ፣26(61.04%) አልስማማም ብለው መልሰው ነበር፡፡በድህረ ትምህርት ፈተና ወቅት ደግሞ 20(47.61%) እስማማለሁ፣22(52.38%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡በዚህ ስር የተወሰነ መሻሻል ታይቷል፡፡በቅድመ ትምህርት እስመማለሁ17(40.47%) የነበረው፣ በድህረ ትምህርት ፈተና 20(47.61%) ሲቀየር፣ አልስማማም ያሉት ደግሞ በቅድመ ፈተና 26(61.04%) የነበረው ወደ 22(52.38%) ዝቅ ብሏል፡፡ተማሪዎች በብልሃት አልባ አንብቦ መረዳትን ቢመሩም ከምንባቡና ከአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ግንዛቤ እንዳዳበሩ ያመለክታል፡፡

ይህን ከላይ በቁጥርና በበርሰንት የተተነተነ መረጃ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ በገላጭ ስታቲስቲካዊ እና በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ቀጥሎ ተተንተኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.19 የቁጥጥር ቡድን የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስ

| | | አማካይ ውጤት | ብዛት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | ቁጥጥር ቡድን ድህረ ፈተና | 2.82 | 42 | .297 | .046 |
| | ቁጥጥር ቡድን ቅድመ ፈተና | 2.64 | 42 | .284 | .044 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

በሠንጠረዥ 4.19 መመልከት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳትፈተና ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 2.64፣መደበኛ ልይይት 0.284 ሲሆን፣በድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና ደግሞ 2.82 አማካይ ውጤት እና 0.297 መደበኛ ልይይት ነው፡፡የቡድኑ የሁለት ጊዜ አማካይ ልዩነት 0.18 (2.64-2.82)፣0.013 መደበኛ ልይይት ተመዝግቧል፡፡ምንም እንኳን በሁለቱ አማካይ ውጤቶች መካከል ያለው ልዩነት ርቀት ተቀራራቢ ቢመስልም በድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት የተመዘገበው አማካይ

ውጤት 2.82 በቅድመ ተምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 2.64 የሚበለጥ ይመስላል፡፡ ይህንን መረጃ የበለተ ለማረጋገጥ ፣የቡድኑን አማካይ ውጤት በማየት ብቻ በርግጠኝነት መወሰን አዳጋች ስለሚሆን መረጃው በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰላቶ ውጤቱ በሠንጠረዥ፡4.20 የቀረበውንይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.20 የቁጥጥር ቡድን ቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ

| ተጠኝ ቡድን | | ጥንድ ልይይት (Paired Differences) | | | | | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ የስህተት አማካይ | የነፃነት ከፍታ ልዩነት | | | | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| Pair 1 | ድህረ የቁጥጥር ቡድን — ቅድመ-የቁጥጥር ቡድን | .188 | .212 | .033 | .122 | .254 | 5.748 | 41 | .000 |

*ምንጭ፡ከጥናቱ ተሳታፍዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት /ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

በሠንጠረዥ4.20 እንደተመለከተው በባለ ሁለት ጫፍ ጉልህነት ፍተሻ በነፃነት ደረጃ (42) 0.000 ከመቁረጫ የነጥብ ዋጋ (0.05) ያነሰ ነው፡፡ይህ ውጤት የሚያመለክተው የቁጥጥር ቡድኑም በድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ውጤቶች መካከል ልዩነት እንዳመጣ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ፡4.21 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች በድህረ ትምህርት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ

| የፈተና ዓይነት | ተጠኚ ቡድን | ብዛት | አማከይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የስህተት አማከይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 42 | 2.82 | .297 | .046 |
| | የሙከራ ቡድን | 40 | 3.21 | .275 | .044 |

*ምንጭ፡ ከተጠኝዎች ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንጠረዥ4:21 እንደተገለጸው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና በጽሁፍ መጠይቅ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት (3.21) እና መደበኛ ልይይት (.275)፣የቁጥጥር ቡድኑ ካስመዘገበው አማካይ ውጤት (2.82) እና መደበኛ ልይይት (.297) ልዩነት ያለ ይመስላል፡፡በበድኖቹ መካከል ያለው ልዩነት በአማካይ ነጥብ (0.39) 2.82_3.21) መደበኛ ልይይት (0.22) ነው፡፡ይህ በቡድኖቹ ውጤት መካከል የተወሰነ ርቀት እንዳለ ያሳያል፡፡ርቀት አለ ማለት ደግሞ ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ይህንን በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለ የጉልህነት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ መረጃው በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲካዊ ስሌት አማካይ ውጤታቸው ተሰልቶ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ፡4.22 ቀርቧል፡

ሠንጠረዥ፡4.22 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ስታቲስቲክስ

| ተጠኚ ቡድን | የፈተና ዓይነት | በእኩል ልይይት የLevene ፍተሻ | | የእኩል አማካይ ውጤት ቲ-ቴስት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልይይት ዋጋ | ጉልህነት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ | አማካይ ልዩነት | መደበኛ የስህተት ልዩነት | 95%የስህተት ይሆንታ ልዩነት | |
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ሙከራ | ድህረ ፈተና | .55 | .816 | 6.0 | 80 | .000 | .381 | .063 | .507 | .255 |
| ቁጥጥር | | | | 6.0 | 79.096 | .000 | .381 | .063 | .507 | .255 |

*ምንጭ፡ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ከጸሁፍ መጠይቅ የተገኘ (2011 ዓ.ም) በባሶ አጠ/2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በመማር ላይ ካሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ*

ከላይ በሠንጠረዥ፡4.22 መመልከት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት እንብቦ የመረዳት ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ ያስመዘገበው ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ጋር ሲነፀር አማካይ ውጤታቸው የተራራቀ ይመስናል፡፡በ0.816) ጉልህነት ባለ ሁለት ጫፍ ፍተሸ በ (80) የነፃነት ደረጃ (Df) የቲ-ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥብ (0.05) ያንሳል፡፡በዚህ ስታቲስቲካዊ መረጃ መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ውጤት የመጣው ከድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና በኋላ ስለሆነ ፣የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ መሻሻል አሳያቷል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ  በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከማጎልበት እንፃር ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ነው፡፡የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም የመጀመሪያው በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን መፈተሽ ሲሆን፣ሁለተኛው የጽሁፍን አወቃቀር ትምህርት መማር የተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ ማሻሻል አለማሻሻሉን መመርመር ናቸው፡፡

የትናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትነ ዋል፡፡

በመጀመሪያ የተተነተነው ከቅድመና ከድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡የጥናቱ አካላዮች የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖች መሆናቸው ተደጋግሞ መገለጹ ይታወቀል፡፡በሁለቱ ቡድኖች የሚገኘውን መረጃ በንፅፅር በተናጠልና በጥንድ በማወዳደርና ከመረጃዎች የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ ከሁለቱ ቡድኖች የተገኘ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ይብራራል፡፡በሠንጠረዥ 4.3 እንደተመለከተው በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ በንፅፅር ተተንትኖ በቅድመ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤቶች መካከል ያለው ልዩነት እዚህ ግባ የሚባል ስላልሆነ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም የችሎታ መለያየት እንደሌለ አረጋግጧል፡፡በሠንጠረዥ 4.4 እንደተመለከተው የሁለቱ ቡድኖች የጉልህነት ደረጃ በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በእኩል ልይይት ሲታሰብ በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ (0.500) ከጉልህነት የመቁረጫ ነጥብ (0.05) የበለጠ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ አሳይቷል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቀደመ እውቀታቸው ሲፈተሽ የጎላ የእውቀት መለያየት አልነበረም ብሎ ማጠቃለል ያስችላል፡፡

በመቀጠል የተተነተነው የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስ ሲሆን፣ ውጤቱም በሰንጠረዥ4.5 እንደተመለከተው የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 27.80 ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት 21.50 አማካይ ውጤት ይበልጣል፡፡ስለዚህ ልዩነት አለ ማለት ነው፡፡ይህ

ውጤት በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ በነፅነት የጉልህነት ደረጃ (40) የቲ-ዋጋ 0.000 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ በሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት መካከል በስታቲስቲካዊ ስሌት የጎላ ልዩነት መኖሩ ስለተረጋገጠ በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ምንባብን መማር ውጤታማ እንደሆነ አሳይቷል፡፡በተዛማጅ ጽሁፍ ስር 2.1.5 Haydari and Mustaphi (2009) እንዳስረዱት ተማሪዎች ሰለተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀሮች ማወቃቸው ከጽሁፍ ውስጥ መለየት ያለባቸውን ሐሳቦች ለመለየት፣ችግርና መፍትሄ ተዛምዶን መለየት፣ጽሁፍ የተዋቀረበትን አደረጃጀት ለመለየት፣የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን ለመለየት፣የጽሁፍን ሙሉ መልዕክት ለማስታወስ ያስችላቸዋል፡፡በዚህ ሐሳብ መሰረት በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማሻሻል ይችላል ማለት ነው፡፡

ሌላው በትንተናው የታየው የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት በጥንድ ንሙና ስታቲስቲክስና በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት አማካይ ውጤት ካስመዘገበው ውጤት በድህረ ትምህርት ያስመዘገበው በ0.47 በልጦ ቢገኝም ያን ያህል የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡ውጤቱ እንዴውም ከቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤትም በነፃነት ደረጃ (42) የቲ-ዋጋ 0.310 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 በልጦ ስለሚታይ በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል በስታቲስቲክስ መረጃ የጎላ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል፡፡ቡድኑ ምንም እንኳን አንብቦ መረዳትን በተለመደው የመማር ሂደት ቢማርም በብልሃት ከተማረው ቡድን ጋር ሲነጻጸር ያሳየው መሻሻል በጣም ዝቅ ያለ ነው፡፡ በተዛማጅ ጽሁፍ 2.1.6. ተማሪዎች በቀጥታ ስለ ጽሁፍ አወቃቀር የሚያገኙት እውቀት በራሱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ይላል፡፡ስለዚህ የቁጥጥር ቡድኑ ያሳየው የተወሰነ መሻሻል ከዘህ ሐሳብ ጋር ይስማማል፡፡

በመጨረሻም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና የሰጠው መልስ በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ በሰንጠረዥ 4.9 እንደተገለጸው የሙከራ ቡድኑ ያመጣው ውጤት የቁጥጥር ቡድኑ ካመጣው ውጤት የበለጠ ነው፡፡የሙከራ ቡድኑ በጽሁፍ አወቀቀር ብልሃቶች በማወዳደርና ማነጻጸር እና በምክንያትና ውጤት ተደግፌው ሲማሩ የቁጥጥር ደግሞ በብልሃት አልባ /በተለመደው/አንብቦ መረዳትን ከተማሩ በኋላ

የመጣ ውጤት ነው፡፡ይህም በአንብቦ መረዳት ፈተና ላይ መሻሻል ያሳየው የሙከራ ቡድኑ ነው፡፡ይህ ውጤት የመጣው ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ከተማሩ በኋላ ስለሆነ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍን አወቃቀር ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማጎልበት እንደሚችል ነው፡፡ በተዛማጅ ጽሁፍ 2.1.2 የጽሁፍ ውቅር ግንዛቤ ያላቸው አንባቢያን ግንዛቤ ከሌላቸው አንባቢዎች በእንብቦ መረዳትም ይሁን በማስታወስ ችሎታቸው የተሸሉ እንደሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡በሁለቱም በኩል መሻሻል አለ፡፡መሻሻሉ ግን በጣም የተራራቀ ነው፡፡የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 27.80 ሲሆን፣የቁጥጥሩ አማካይ ውጤት 20.90 ነው፡፡በሠንጠረዥ 4.10 እንደተመለከተው በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶም በ4.55 በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ በነጻነት ደረጃ (80) የቲ-ዋጋ 0.000 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 አንሶ ስለተገኘ በስታቲስቲክሳዊ ስሌት መሰረት በናሙናነት በተመረጡት ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ የአነብቦ መረዳት ችሎታ ተስተውሏል፡፡ይህ ደግሞ የጽሁፍ አወቀቀር ብልሃት ትምህርት የተማሩት ስለሆነ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት የጽሁፍ ብልሃትን መማር አንብቦ የመረዳት ክሂልን የማጎልበት ሚና እንዳለው ያሳያል፡፡በተዛማጅ ጽሁፍ 2.2 በአንብቦ መረዳትና በጽሁፍ ውቅር መካከል ጥብቅ ትስስር እንዳለ ጥናቶች የጠቁማሉ፡፡Hass (2006) አራትና አምስት አንቀጽ ያለው ጽሁፍ ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያነት ቢቀርብ የመጀመሪያው አንቀጽ ስለ ችግሩ ምንነት ይጠቅሳል፤ሁለተኛው፣ሶስተኛው እና አራተኛው የችግሩን መፍትሄ ይጠቁማል፡፡ይህ አይነት አደረጃጀት ለአንብቢው ስለሚያነበበው ጽሁፍ ጥቆማን ስለሚሰጥ የሚያነቡትን ጽሁፍ የማደራጃትና የማቀናጀት ችግር ላለባቸው ተማተሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ያስችላቸዋል፡፡በተጨማሪም ተማሪዎች ጽሁፍ በሚጽፉበት ጊዜ ሐሳባቸውን እንዴት ማደራጃት እንዳለባቸው ግንዛቤ ያዳብራሉ ማለት ነው፡፡ስለዝህ የጽህፍ አወቃቀር ብልሃትን ተማሪዎችን ማስተማር የማይናቅ አስተዋጽኦ እንዳለው የመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ከቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የዚህን ጥናት ውጤት በመመለስ እረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው አሳይቷል፡፡ይህም በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማጎልበት እንደሚችልና ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር ለመረዳት እገዛ እናዳለው አሳይቷል፡፡

ሁለተኛው ይህ ጥናት ይዞት የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ በመረጃ መሰብሰቢነት የተጠቀመው የጽሁፍ መጠይቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ከማጎልበት እና ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ከመገንዘብ አንጻር አሻሽሏል አላሻሻለም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በፈተና እንደተገኘው ውጤት ተተነትኖ፣ በፈተና ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህንን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሾችን በቡድናዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ እና በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት የተሰሉ ውጤቶችን እየተመከከትን እናብራራ፡፡

በሠንጠረዥ 4፡13 እንደተመለከተው በቅድመ ትምህርት ፈተና ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት በጣም ተቀራራቢ ነው፡፡የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 2.60 ሲሆን፣የቁጥጥሩ ደግሞ 2.64 ነው፡፡በመካከላቸው ያለው ልዩነት 0.04 ብቻ ነው፡፡ይህው ውጤት በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት በሠንጠረዥ 4፡14 እንደሚታየው በ(0.544) ጉልህነት በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ በ(80) የነጻነት ደረጃ የቲ-ዋጋ 0.631 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 እንደበለጠ አረጋግጧል፡፡ስለዚህ በቅድመ ትምህርት ፈተና በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም የችሎታ መለያየት የለም የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል፡፡ይህንን ውጤት ከድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት ጋር በንፅፅር ሰናየው በድህረ ትምህርት ፈተና የተመዘገበው ውጤት በሠንጠረዥ 4፡21 እንደሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና በጽሁፍ መጠይቅ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 3.21፣የቁጥጥር ቡድኑ ካስመዘገበው አማካይ ውጤት 2.82 ይበልጣል፡፡የጉልህነት ደረጃውም በሠንጠረዥ 4፡22ሰ እንደሚያመለክተው በ0.816 ጉልህነት በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ በ(80) ነጻነት ደረጃ የቲ-ዋጋ 0.000 ከመቁረጫ ነጥብ 0.05 እንደሚያንስ ያሳያል ይህ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ የውጤት ልዩነት መኖሩን አረጋግጧል፡፡በዚህ ግኝት መሰረት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የጽሁፍ አደረጃጀት ብልሃትን ማሻሻል መቻሉን ነው፡፡በተዛማጅ ጽሁፍ 2.1.5 ትምህርታዊ ይዘት ያላቸው ጽሁፎች ከሚቀርቡበት መንገድ አንዱ የጽሁፍ አወቃቀርን በመጠቀም ነው፡፡ተማሪዎች ስለተለያዩ የጽሁፍ አወቃቀር ማወቃቸው ከጽሁፍ ውስጥ መለየት ያለባቸውን ሐሳቦች ለመለየት፣የችግርና መፍትሄን መለየት፣ጽሁፍ የተዋቀረበትን አደረጃጀት መለየት፣የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን ለመገንዘብና ጽሁፉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ለማታወስ ያግዛቸዋል፡፡በዚህ አግባብ ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ ያሉ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ምንነት በመለየት ፣ፍንጭ ሰጭ ቃላትና

ሀረጋትን በመረዳት ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ማስገንዘብ መቻሉን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አንብቦ መረዳት የተገኙት የመረጃ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት የጽሁፍ አወቃቀር ትምህርት መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማጎልበት እንደሚችል፣ጽሁፍ የተደራጀበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት በመገንዘብ የጽሁፍ ችሎታቸውን ማሻሻል እንደሚቻል አሳይቷል ማለት እንችላለን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሐሳብ

## 5.1.ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ማሻሻል አለማሻሻሉን መመርመር፤በጽሁፍ ውስጥ ጽሁፉ የተደራጀበትን የጽሁፍ አጻጻፍ (አወቃቀር) ብልሃት ተገንዝበው በራሳቸው መጻፍ መቻላቸውን መፈተሽ ነው፡፡ጥናቱ በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃትን በሁለት ቡድኖች በሙከራና በቁጥጥር ቡደኖች ላይ በማድረግ መጀመሪያ ለሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ በመስጠት፣እንድሁም የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው የእንብቦ መረዳት ዘዴ፣የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በጽሁፍ ውቅር ብልሃት ከተማሩ በኋላ ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰቶ የተገኘው ውጤት በሚከተለው ሁኔታ ተጠቃሏል፡፡

- በመጀመሪያ የሁለቱ ቡድኖች በቡድናዊ ስታቲስቲክስ እና በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመ ትምህርት ፈተና የተገኘው ውጤት ያመለከተው በቡድኖቹ መካከል ምንም የጎላ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ ከድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በቡድነዊ ስታቲስቲክስ ፣በጥንድ ንሙና ቲ-ቴስት እና በባዕድ ንሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ሲያሳይ፣የታየውም ልዩነት በብልሃት የተማረው የሙከራ ቡድን በተለመደው የማስተማር ስልት ከተማረው የቁጥጥር በድን በልጠ ተገኝቷል፡፡ስለዚህ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ትምህርት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማሻሻል እንደሚችል አረጋግጧል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

በጥናቱ መነሻ ችግር ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ተማሪዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ወደ 2ኛ ደረጃ የመጀመሪ ሳይክል ሲዛወሩ የአንብቦ መረዳት ችግር በስፋት ይታይባቸዋል፡፡ይህንን ችግር ለመፍታት ደግሞ ብዙ ጊዜ እንደመፍትሄ የሚወሰደውና የሚጠናው የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ነው፡፡ይህም ጥናት ተሞከረው ከማስተማሪያ ዘዴ በሆነው በምንባብ ውስጥ የጽሁፍ ውቅር ብልሃትን ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ

መረዳት ማሻሻሉን መፈተሽ ሲሆን፣ፈተሸው ወይም ምርምሩ ከተደረገ በኋላ የተገኘው ውጤት በሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ አደርሷል፡፡

- ተማሪዎች አንድ ጽሁፍ ወይም ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ምንባቡ የተዋቀረበትን የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እና እንዴት እንደተዋቀረ ታሳቢ እያደረጉ ማንበብ እንዳለባቸው ከተገነዘቡ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንደሚያሳድጎ አሳይቷል፡፡ ተዛማጅ ጽሁፍ 2.1.3 ተማሪዎች በማንበብ አውድ ውስጥ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እውቀታቸውን እንዴት እንደሚተገብሩት ካልተማሩ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እውቀት መኖር ብቻውን ለተማሪዎች የማንበብ ውጤት ስኬት ያለው ሚና ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡
- አንድ ጽሁፍ በየትኛው የጽሁፍ ብልሃት እንደተዋቀረ የሚጠቁሙ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ከተገነዘቡ፣እንዲሁም ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋትን ፍች ካወቁ የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እንደማይቸገሩና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ማሻሻል እንደሚቻል አሳይቷል፡፡
- አንድ ጽሁፍ በሚጻፍበት ጊዜ በየትኛው የጽሁፍ አወቃቅር ብልሃት እንደተዋቀረና እንደተደራጀ ከተገነዘቡ ፣በሚያነቡበት ጊዜ የሃሳብ ትስስር እንዴት መፍጠርና ማደራጀት እንዳለባቸው ከተረዱ በሚያነቡበት ጊዜ እንደማይቸገሩ ማሳየት ችሏል፡፡
- ሌላው በሚያነቡበት ውቅት በሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ጠቃሚ የሆኑ ሓሳቦችን ጠቃሚ ካልሆኑ ሐሳቦች ለይተው ማተኮር የሚያስችል የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ማወቃቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ከፍ አድረወጓል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳብ

ተማሪዎች አንብበው መረዳት ካልቻሉ ማንበብ ትርጉም የለውም፡፡አንብቦ መረዳት ማለት የተነበበውን መለየት፣መተርጎምና መጠቀም ነው፡፡የማንበብ የመጨረሻ ግብ አንብቦ መረዳት ነው፡፡ያነበቡትን መረዳት የሚችሉበትን ብልሃት ማወቅ ደግሞ ትላቅ ችሎታ ነው፡፡የተለያዩ የጽሁፍ አይነቶች የተጻፉበትን ስልት ማወቅ ተማሪዎች የሚያነቡት ጽሁፍ ለምን ዓላማ እንደተጻፈ እና እንዴት እንደተጻፈ ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ለምሳሌ አንዳንድ ጽሁፎች የሚፃፉት ለማዝናናት ወይም ማህበራዊ ትምህርት ለመስጠት ሊሆን ይችላል፣ አንዳንዶች ደግሞ ፅንስ ሐሳብ ወይም ይዘት ለማስተማር ሊሆን ይችላል፡፡ስለዚህ ጽሁፍ ለምን ዓላማ እንደተጻፈ እና እንደት እነደተጻፈ መማር ደግሞ የአንብቦ መረዳት አቅማቸውን ያሳድግላቸዋል፡፡የተማሪዎችን የማንበብ አቅም ለማሳደግና የአንብቦ መረዳት

ችሎታቸውን ለማጎልበት ወደፊት ቢተገበሩ ሊጠቅሙ ይችላሉ የተባሉ ስነ ትምህርታዊ የመፍትሄዎችና ተጨማሪ የምርምር አቅጣጭዎች ተጠቁመዋል፡፡

- .በዘህ ጥናት የተፈተሹ የጽሁፍ ውቅር ብልሃቶች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ወደፊት ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉንም የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውስጥ እያካተቱ ቢያስተምሩ፡፡
- የቋንቋ መምህራን በተለያዩ የአፃፃፍ ስልቶች እና ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተፃፉ ጽሁፎችን እየመረጡ ተማሪዎቻቸው እንዲያነቡ ዕድል በመስጠት የማንበብ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ድጋፍ ቢያደርጉ፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች እና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ለማናበብ ክህል መማሪያ ምንባቦችን ስመርጡና የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ሲያዘጋጁ የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶችን ማቅረብ እንደ አንድ የማንበብ ተግባራት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበት የተማሪዎችን እንብቦ የመረዳት ችግር ሊቀንስ ይችላል፤
- የዚህ ጥናት ውጤት በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃቶች ብቻ ማንበብን መማር በአንድ የክፍል ደረጃ በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ብቻ ተተግብሮ የተገኘ ስለሆነ ውስንነት ስለሚኖረው፣ሌሎች ተመራማሪዎች በሌሎች የክፍል ደረጃዎችና በርከት ባሉ የጥናት ተሳታፊዎች ረዘም ላለ ጊዜ ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴ ተከትነው ተጨማሪ ጥነት ቢያደርጉ ብልሃቶቹ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ዙሪያ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በጥልቀት ለማወቅና መፍትሄ ለማስገኘት ቢሞከር፤
- እነዚህ ብልሃቶች የተፈተሸት በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውሰጥ ብቻ በመሆኑ፣ወደፊት እንደ መፃፍ ባሉ ሌሎች የአማርኛ ቋንቋ ክህሎች ጭምር ሚናቸው ቢፈተሽ፤

## ዋቢ መጻህፍት


ሓይማኖት ደመለሽ፡፡ (2004)፡፡በፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች የቃላት እውቀት ችሎታና የአንብቦ መረዳት ውጤት ተዛምዶ፣በባህርዳር ዩንቨርስቲ፡፡ያልታተመ፡፡

መሪነሽ ነጋሽ፡፡(2004)፡፡ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ታምዶ የድግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፡፡በባህርዳር ዩንቨርስቲ፡፡ያልታተመ፡፡

ማስተዋል ሙላቱ፡፡(1989)፡፡የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛ እንብቦ መረዳት ችሎታ አዲስ አበባ በአራት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በ11ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

ሰለሞን ደኑ፡፡(2003)፡፡ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፡፡ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ በአራት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡አዲስ አበባ ዩንአርስቲ፤ለሁለተኛ ድግሪ መሟ ያነት የቀረበ፡፡(ያልታተመ)፡፡

በየነ ገብረህይወት፡፡(1999)፡፡የፍጥነትንባብና አንብቦ የነረዳት ዝምድና፤ጅማ ዩንቨርስቲ፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ መሚያነት የቀረበ፡፡(ያልትተመ)፡፡

ከበደ ሙሉጌታ፡፡(1988)፡፡ በ11ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ትምህርት በተመለከተ በተመረጡ ሁለት የጉራጊ ዞን የመሰናዶ ት/ቤቶች የመጀመሪያ ድግሪማሚያ፡፡ ጅማ ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1986)፡፡ አንብቦ መረዳትና የመጽሐፍ ችሎታ ማዳበር፡፡ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

ዘ-ማይንድ መፅሔት 1ኛ ዓመት፣ቁጥር14፣ታህሣሥ (2002)፡፡አዲስ አበባ፡፡

የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የንባብ ክበብ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ትምህርት ሚኒስተር፡፡(2009)

የሻው ተሰማ፡፡(1996)፡፡ ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ሰብዕ፣በጽሁፍ ተግባቦት ክህል፣ብዕርን የማናገር ሰባኣዊ ብቃት፡፡

ዳኛቸው ወርቁ፡፡(1977)፡፡የጽሁፍ ጥበብ መመሪያ፡፡ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡አዲስ አበባ

ጥሩነሽ ክንፈ፡፡(2005)፡፡በሰሜን ሸዋ ዞን በእንዋሪ ሚሊኒም መሰናዶና አጠ/2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትየአ ማርኛ ቴክስት አወቃቀር እውቀትነ አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ባህርዳር ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

Alderson,J.C. Clapham. C.& wall. D (1995) ***Language test constriction and evaluation***.

Cambridge university press.

Alderson.R.C. (1982) Allocation of attend during reading technical Report N.2321.Cambridge Massachusetts: Bolt Beranck and Newman Inc.

Armbruster.B.B. Anderson.T.K. & Ostrstage.J. (91987) text structure summarization instruction Fac ilitate learning from expository text reading Research quarter. Of 22(331-346). Referred from http//www. Jstor.Org./stable//747972. Accessed :01/08/201109: 55

Armberuster B.B Anderson, T.H, & Oster tag. J. (1989). Teaching text structure to improve Reading & writing. The reading Teacher , 43(2).130 -137 Retrieved from htt//www.Jotor. org /stable/20200307 Accessed :01/08/201109:40

Arkins, T.E. (2013). The effects of explicit teaching of comprehension strategies on reading comprehension in elementary Ached/Colonial dissertation Columbia university.

Baker, W. &Boon kit, K. (2004) learning strategies in reading and writing. EAP contexts Regional language center Journal.35(3) .299-328. 10,117710033 6688205052143.

Chang.c (2002) the reader effects (instruction) awareness of text structure and texteffects well Structural vs.badstructural textson first and second/foreign language reading comprehension and recall what does research teach us Retrieved from ERIC data base, (ED 465180)

Dymock, s. (2007) comprehension strategy instruction teaching narrative text structure . The reading teacher,61 (2),161- 167.Retrieved from http//www.Jstor.org.stable. /20204567. Rccessed.07/11/2014

Haas, C.& Flower, L, (1988) Rhetorical reading strategies and the constriction of meaning. College composition and communication.39(2), (67-183 Retrieved from http//www.Jstor.org. /stable 358026 Accessed: 17/12/2015)

Hess, K.K. (2006). teaching and assessing understanding of text structure across grades national center for the improvement of educational Assessment.

Holsgrus, J.V. (2011) Structure strategy use in children’s comprehension of expository texts unpolished doctorial) Edith Cowan university, faculty of computing health and science.

Mann, W.C. 7 Thompson,S.A. (1979) Rhetorical structure theory Afunctional theory of Text organization, txst,8(3),243_ 281

Meyer, B.J.F. (1991) importance of text structure in every day reading .in A. Ram& K. Hool

maleds. understanding language (pp227 -252) comb rage MIT press.

Meyer, B.J.F. & Ray, M.N. (2011) structure strategy interventions. Increasing reading comprehension of expository Education,A (1) ,127 – 152) Retrieved from www.iejee.c

Pajares, F. (2006).self-efficiency during child hood adolescence, implication for teachers and perfects IN.F. pajares&T. urdm (EDS) self-efficiency beliefs of adolescences (pp339- 367). Geen with CT.Information Age publishing.

## አባሪዎች

### አባሪ ሀ

### ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

### ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ

አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

<u>በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ</u>

ይህ መጠይቅ የቀረበው፣በምንባብ ውሰጥ የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር በሚል ርዕስ የቀረበን ጥናታዊ ጽሁፍ ለማጥናት የሚደረገውን ጥናት ለማገዝ መረጃ ለመሰብሰቢያ የተዘጋጀ መጠይቅ ነው፡፡በመጠይቁ መሰረት የምትሰጡት ምላሽ ለዚህ አገልግሎት የሚውል ስለሆነ፣መጠይቁ ሲሞላ ሚስጥሩ የተጠበቀ መሆን ይኖርበታል፡፡እናንተ የምትሰጡት ትክክለኛ ምላሽ ጥናቱ ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ እገዛ ስለሚኖረው ከዚህ በታች የቀረቡትን መጠይቆች በመሙላት እንድትተባበሩኝ እጠይቃለሁ፡፡ለትብብራችሁ በቅድሚያ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

አሰፋ በቀለ

<u>ማሳሰቢያ</u>

1.መጠይቁ ላይ ስም አይጻፍም፡፡

2.መጠይቁ የሚሞላው በግል ወይም በተናጠል መሆኑን አውቃችሁ የየራሳችሁን ሙሉ፡፡

3.መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

መመሪያ፡-ከዚህ በታች የቀረቡት መጠይቆች በእያንዳንዳቸው ፊት ለፊት አራት አራት አማራጮች ቀረበዋል፤መጠይቆቹን በጥንቃቄ በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች በአንዱ ስር የ‹‹X›› ምልክት በማድረግ ይሙሉ፡፡በአንድ ጥያቄ ፊት አንድ ምልክት ብቻ ነው የምታደርጉት፡፡

አማራጮች፡-4.በጣም እስማማለሁ 3.እስማማለሁ 2.አልስማማም 1.ጭራሽ አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማንኛውንም ጽሁፍ ያለ ምንም ችግር ማንበብ እና የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአግባቡ መረዳት እችላለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያለን ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ለይቸ ለማውጣት አልቸገርም፡፡ | | | | |
| 3 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት የተለያዩየ ንባብ ብልሃቶችን እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 4 | የማነበውን ጽሁፍ ለመረዳት ምንም አይነት የንባብ ብልሃት ተጠቅሜ አላውቅም፡፡ | | | | |
| 5 | አንድን ጽሁፍ ወይም ምንባብ በማነብበት ጊዜ ጽሁፉ በየትኛው የጽሁፍ ውቅር ብልሃት እንደተዋቀረ መለየት እችላለሁ፡፡ | | | | |
| 6 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን ትርጉ /ፍች/ በመረዳት ጽሁፉ የተዋቀረበትን የጽሁፍ ብልሃት ማወቅ እችላለሁ፡፡ | | | | |
| 7 | በማነበው ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት እገዛ እንደሚያደርጉ አውቃለሁ፡፡ | | | | |
| 8 | ከአነበብኩት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ያለምንም ችግር መመለስ እችላለሁ፡፡ | | | | |
| 9 | የማነበው ጽሁፍ በምን አይነት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንደተጻፈ ለመለየት አልቸገርም፡፡ | | | | |
| 10 | አንበቦ መረዳትን ለማፋጠን ከሚያግዙ የጽሁፍ ብልሃቶች አንዱ የጽሁፍ መዋቅር ብልሃትን ማወቅ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ | | | | |

# አባሪ ለ

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የቅድመ ትምህርት ፈተና

የፈተናውመስጫ ጊዜ____2፡40________________

ለፈተና የተሰጠው የጊዜ ርዝማኔ1፡20____________

ተማሪዎች የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ ለሌላ ለምንም ሳይሆን ‹‹የጽሁፍ አወቃቀርን ማስተማር አንባብ የመረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመፈተሽ የሚደረገውን ጥናት የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ብቻ ነው፡፡

ጥያቄዎች የሚቀርቡት ሙሉ በሙሉ ምንባቡን መሰረት አድርገው ሲሆን፣ጥያቄዎቹ ጠቅለል ባለ መልኩ ሁለት ክፍል ሲኖራቸው እነሱም፡- ምርጫ እና ቀጥተኛ መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ለዚህ ለቅድመ ትምህርት ፈተና የሚያስፈልጉ ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል፡፡አንደኛው ምንባብ በምክንያትና ውጤት የተዋቀረ ጽሁፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማወዳደርና ማነጻጸር ውቅር የተዋቀረ ጽሁፍ ነው፡፡በየአንዳንዱ ምንባብ ስር አስር አሰር ጥያቄዎች በጠቅላላው ሃያ ጥያቄዎች ይይዛል፡፡ተማሪዎች ከእናንተ የሚጠበቀው የእያንዳንዱን ትዕዛዝ/መመሪያ/ በጥንቃቄ በማንበብ ለመልስ መስጭያ በተቀመጡት ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ነው የምትሉትን መልስ መመለስ ይሆናል፡፡

## ምንባብ አንድ

ቤተሰብ ሲፈርስ፣ልጆች ከእናት ወይ ከአባት ጋር እንዲሆኑ ወይም እንደቁሳቁስ በቁጥር ተለያይተው ለእናትና አባት እኩል እኩል እንዲደርሱ ሆነው እንደ ቅርጫ ስጋ እንዲከፋፈሏቸው ይፈረድባቸዋል፡፡የየድርሻቸውን የተካፈሉም ሆኑ ሳይካፈሉ በአንዳቸው አላፊነት ብቻ እንዲያድጉ የሚስማሙ እናትና አባት አላማቸው የተመሳሰለ ነው፡፡በጊዚያዊ በመደለያ በማባበል የልጆችን ፍቅር የየራሳቸው የብቻ ድርሻ አድርገው ለመያዝ መታገል፡፡በእናት ስር የሚተዳደሩ ከሆነ ወደ አባት ዘንድ ለጉብኝት ሲሄዱ ከተገቢው በላይ መስተንግዶ ይቆያቸዋል፡፡በአባት ስር የሚተዳደሩ ከሆነ እናት ዘንድ ሲሄዱ እንዲሁ የተለየ መስተንግዶ፡፡አንዴ እናት ዘንድ አንዴ

አባት ዘንድ፣አባት ዘንድ እናት ዘንድ፣እናት ዘንድ አባት ዘንድ፣ልጆች የሚውሉበትን እና የሚያመሹበትን ቦታና ሁኔታ መከታተል ያዳግታል፡፡ የሚየደርጉትንና የተሰማሩበትን ተግባር ለማወቅ ይቅርና፡፡የትነበራችሁ ሲባሉ ‹‹አባጋ››ወይም‹‹እማዬጋ››፤ምን ስታደርጉ ቆያችሁ ሲባሉ፣‹‹ከአባዬ ጋር ስጫዎት››፣‹‹እማዬን ስራ ስረዳ››__የማይሉት የማይፈጥሩት ምክንያት የለም፡፡ለቁጥጥር አመችነታቸው ይዳከማል፤ቁጥጥር ይላላል፡፡ከአጓጉል ጓደኞች ጋር መዋል፤ በአጓጉል ቦታዎች መገኘት ይጀመራል፡፡በሆነ ባልሁነው ምክንያት አንዴ ከአባት ሌላ ጊዜ ከእናት፣ከዘመድ አዝማድ ገንዘብ እየተወሰደ፤ፍላጎት እያደገ ይሄዳል፡፡ገንዘብ እያጠረ፤የህይወት ትርጉሙ እየጠፋ፤መንፈስ እየተረበሸ፤አይሰሩ ስራ እየተሰራ-ሞራላቸው እያላሸቀ፤እንዲያም ብሎ ባስ-ሲል ግዴለሽነትን ፣ሲጠናወት መዛዘንን፣ ሲረጋጋ ወመኔነትን፣ ሲለይለት ወፈፌነት እያስከተለ…የቤተሰብ መፍረስ፣የመንፈስ መረበሽና የሞራል ውድቀት፣ የወመኔነትና የወሮበላነት፣ግፋም ሲል የወንጀለኝነት መንስኤ ነው፡፡

ዳኛቸው ፣1988፤155-156፡፡የተወሰነ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ፡፡

I. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ /አገባባዊ ፍቻቸው የያዘውን ሆሄ/ፊደል በመምረጥ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመሙላት መልሱ፡፡

1.__________መደለያ ፣ ሀ.ማታለያ ለ.መሸንገያ ሐ.ጉቦ መ.‹‹ሀ››እና ‹‹ለ›› መልስ ናቸው

2__________ድርጎ ፣ሀ.ማባባያ ለ.ግብር ሐ. ቦረንትቻ መ. መማጸኛ

3.__________ባስ ሲል ፣ ሀ.ሲሻሻል ለ.ዝቅ ሲል ሐ.ሲከፋ መ.መልስ የለውም

4.__________ መዛዘን ፣ ሀ.መሴሰን ለ.ማላዘን ሐ.መክለፍለፍ መ.መባዘን

II. ከዚህ በታች ለቀረቡ የተለያዩ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልሳቸውን በተሰጠው የመልስ መስጫ ላይ በመጻፍ መልሱ፡፡

1. ለልጆች መበተን ምክንያቱ/ሰበቡ/ ምነድንነው?

______________________________________________

2. ወላጆች ለልጆች ከተበተኑ በኋላ ልዩ መሰተንገዶና እንክብካቤ ማድረጋቸው ለምን ይመስላችኋል ?

______________________________________________________________________

3. ልጆች የት ነበራችሁ ተብለው ሲጠየቁ የሚያቀርቡት ምክንያት ምንድንነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4.የልጆች ከአጓጉል ጓደኛ ጋር መዋል፣በአጓጉል ቦታ መገኘት ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል?

______________________________________________________________________

5. የመጀመሪያው /ምክንያት/ ሰበብ ውጤቱ ምንድንነው?

______________________________________________________________________

6. የልጆች አንዴ እናት ዘንድ፣ አንዴ አባት ዘንድ መሆን ውጤቱ ምንድን ሊሆን ይችላል?______________________________________________________

______________________________________________________________________

## ምንባብ ሁለት

ለአብነት ያህል የሀዲስ አለማየሁንና የበአሉ ግርማን የዘይቤ ምንጮች ብንመለከት ነገሩ ይበልጥ ግለጽ ይሆንልናል፡፡ሁለቱ ደራሲያን በአመዛኙ አነፃፃሪ የተባለውን ዘይቤ የሚመርጡ መሆኑ ከስራዎቻቸው ማወቅ ተችሏል፡፡ሁለቱም አነፃፃሪ ዘይቤን በዋናነት ይጥቀማሉ፡፡ በሁሉም ውስጥ ይህ ዘይቤ ጎልቶ ይታያል፡፡ሁለቱም ዘይቤውን በጎላ ሁኔታ የሚጠቀሙበት ገፀባህርያትን ለመግለፅ ድርጊታቸውን ስሜታቸውንና ያሉበትን ሁኔታ ለማሳየት ነው፡፡የዘይቤ ምንጮቻቸውን ስንመለከት የሀዲስ አለማየሁ በአንደኛ ደረጃ ሰው ሲሆን በሁለትኛ ደረጃ ተፈጥሮ ነው፡፡የበአሉ ግርማ ምርጫ በአንደኛ ደረጃ ተፈጥሮ በሁለተኛ ደረጃ ቁሳቁስ ነው፡፡ይህ የደራሲያኑ ዋነኛ የምናብ ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ መገመት ያስችለናል፡፡

III. ቀጥሎ ለተሰጡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከተሰጡት <u>አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ ነውየምትሉትን በመምረጥ በመለስ መስጫው ላይ በመፃፍመልሱ፡</u>

1________አብነት፣ ሀ.ምሳሌ ለ.መድሃኒት ሐ.ይምሰል መ.ትንግርት

2.________ ጎልቶ፣ሀ.አንሶ ለ.በዝቶ ሐ.ደምቆ መ.አልፎ አልፎ

3._______ ምንጮቻቸው፣ ሀ.መፍለቂያቸው ለ.መነሻቸው ሐ.መጠጫቸው

መ.ሁሉም መልስ ይሆናሉ

4._______ ምናብ፣ ሀ.እይታ ለ.አስተሳሰብ ሐ.አእምሮ መ.ህልም

IV. ከዚህ <u>በታች የቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ ሲሆኑ፣ የያንዳንዱን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ በተሰጡት ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ መልሱ፡፡</u>

1.ሁለቱን ደራሲያን የተወዳደሩት /የተመሳሰሉት/ በምንድንነው?

_____________________________________________

_____ 2.ሁለቱ ደራሲያን በምን በምን የሚነፃፀሩ ይመስልሃል/ሻል?

_____________________________________________

_____________________________________________

3. የሀዲስ አለማየሁ የዘይቤ ምርጫ ምን ይመስላል? አብራሩ?

_____________________________________________

4. የበዓሉ ግርማስ የዘይቤ ምንጮች ምንድን ናቸው?ግለጹ?

_____________________________________________

5.ሁለቱ ደራሲያን ዘይቤውን በአብዛኛው የሚጠቀሙት ምንን ለመግለጽ ነው?

_____________________________________________

_____________________________________________

6.ይህ አንቀጽ የተዋቀረው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ነው?

_____________________________________________

# አባሪ ሐ

## ድህረ ትምህርት ፈተና

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋነቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ድህረ ትምህ ፈተና

ፈተናው የሚሰጥበት ጊዜ ፡-2፡00

ፈተናው የሚወስደው የጊዜ ርዝማኔ__1፡30

## ምንባብ አንድ

## ተስቦና የአንጀት ተስቦ

የአንጀት ተስቦ /ታይፎይድ ፊቨር/ እና ተስቦ /ታይፈስ/ ሰውን የሚያጠቁ በሽታዎች ናቸው፡፡እነዚህ በወረሪሽኝ መልክ የሚከሰቱ በሽታዎች ከሰው ወደ ሰው በፈጥነት ከመዛመታቸውም በላይ በአጭር ጊዜ የአንድን አካባቢ ሕዝብ ሊያጠቁ ይችላሉ፡፡ ተስቦ በቅማል፣በመኘገርና በቁንጫ አማካይነት ወደ ሰው ይተላለፋል፡፡በተለይ የተስቦ ህዋስ ያለባት ቅማል ጤነኛ ሰው ስትነክስና ሰውዬውም ሲያክ ስትደፈጠጥ፣በተፈገፈገው ቆዳው በኩል የቅማልዋ ደም ገብቶ ሰውዬውን ይበክለዋል፡፡የአንጀት ተስቦ ደግሞ በበሽተኛው አይነምድር በተበከለ ምግብና ውሓ አማካይነት ወደ ጤነኛው ሰው አፍ በመግባት ይተላለፋል፡፡

ተስቦ የያዘው ሰው ለአደጋ የሚጋለጠው በወረርሽኙ በተያዘ በአንደኛው ሳምንት ሲሆን፣ የአንጀት ተስቦ ግን በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ነው፡፡ሁለቱም ተስቦዎች በወረርሽኝ መልክ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፉ ናቸው፡፡እድሜና ጾታ የማይለዩት እነዚህ በሽታዎች ትኩሳት፣ራስ ምታት፣ጉንፋን፣ሽፍታ፣ ማስታወክ፣ የአእምሮ መሳት፣ተቅማጥ እና ድካም በበሽተኛው ላይ ያመጣሉ፡፡ሰውነትን ከሚገባው በላይ ይጎዳሉ፤የገድላሉ፡፡ሁለቱንም በሽታዎች በህክምና ለማወቅ የግድ የደም ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በሽተኛውን ማዳኛ ክሎራፌኒኮል የተባለ መድሃኒት ነው፡፡ይሁንና እነዚህ በሽታዎች ሙሉ ለሙሉ የሚጠፉት የአካባቢንና የራስን ንጽህናን በመጠበቅ ነው፡፡ተስቦ ፈጣን ህክምና ካልተደረገለት በበሽታው የተለከፈው ሰው በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ሊሞት ይችላል፡፡የአንጀት ተስቦ ደግሞ አንጀት ሊበሳና ብዙ ደም ሊፈስ ይችላል፡፡ይሁንና ለሞት አደጋ አያጋልጥም፡፡

ደረጀ ገብሬ፣1996፣ <u>ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ</u>

1-5 ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሳቸውን በመምረጥ ለመልስ መስጭያ በተሰጠው ክፍት ቦታ በመሙላት መልሱ፡፡

1________‹‹ ወረርሽኝ›› ለሚለው ቃል በምንባቡ መሰረት ተመሳሳዩ ከሚከተሉትየትኛው ሊሆን ይችላል?

ሀ.በሃይል አስገድዶ የሚይዝ ጠላት ለ.በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ሐ.ሰውነትን የሚያሳክክ በሽታ መ.ሁሉም መልስ መሆን ይችላሉ

2.________‹‹አይነምድር›› ለዚህ ቃል ተመሳሳዩ የትኛው ነው? ሀ.ሰገራ ለ.አር ሐ.ኩስ መ.ሁሉም መልስ ይሆናል፡፡

3.________ በመጀመሪያው አንቀጽ ውስጥ የቀረበውን ሓሳብ ሁለቱን በሽታዎች የገለጸበት መንገድ በየትኛው የአገላለጽ ስልት ነው? ሀ.በማወዳደር ለ.በማነጻጸር ሐ. በማወዳደርና፣ በማነጻጸር መ.ሁሉም

4.__________ በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የቀረበው ሓሳብ በየትኛው የጽሁፍ ትስስር/አወቃቀር/የቀረበ ነው? ሀ.በማወዳደር ለ.በማነጻጸር ሐ.በማወዳደርና ማነጻጸር መ.መልስ የለውም

5.________ሶስተኛውና የመጨረሻው አንቀጽ ሁለቱን በሽታዎች የገለጸበት መንገድ በምን ሁኔታ ነው?

ሀ. በማወዳደርና ማነጻጸር ለ.በማወዳደር ብቻ ሐ.በማነጻጸር ብቻ መ.መልስ አልተሰጠም

I. <u>ከ6-10 የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ ነው የምትሉትን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ መልሱ፡፡</u>

6.ሁለቱ በሽታዎች የተወዳደሩበትን/ የተመሳሰሉበትን /ሁኔታዎች ዘርዝራችሁ ጻፉ?

ሀ.____________________________________________

ለ.____________________________________________

ሐ.____________________________________________

7. ሁለቱ በሽታዎች የተነፃፀሩበትን ሁኔታች ዘርዝሩ?

ሀ.____________________________________________

ለ.____________________________________________

ሐ.____________________________________________

8. የትኛው በሽታ ነው በፍጥነት ህክምና ካላገኘ ለሞት የሚያደርሰው ?

______________________________________________

9. በሽታዎቹን ሙሉ ለሙሉ ለማስወገድ ዋነኛው መንገድ ምንድን ነው?

______________________________________________

10. ምንባቡ /ጽሁፉ/ የተጻፈው ወይም የተዋቀረው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ነው?

---

## ምንባብ ሁለት

ያላገባች ሴት መፀነሷን ካወቀችበት ጊዜ ጀምሮ ጭንቀት ውስጥ ትዘፈቃለች፡፡የጭንቀቷ መንስኤ ማህበረሰቡ በማይደግፈው ህገ-ወጥ እርገረዝና የተነሳ ሊደርስባት የሚችለውን ግላዊና ማህበራዊ ችግር በመፍራት ነው፡፡በተጨማሪም ለህጻኑ ውልደት የገንዘብ ምንጭ አለመኖር ለህጻኑ የሚደረገው እንክብካቤ፣የቤተሰቡ አባላትና የቅርብ ጓደኞች ማርገዟን ሲያውቁ እንዴት እንደሚመለከቷት መፍራት ሌላው የጭንቀቷ መሰረት ናቸው፡፡ጭንቀቷ በጣም ከፍተኛ የሚሆነው ደግሞ የፀነሰችለት ወንድ ሊያገባት የማይችል ወይም የማይፈልጋት መሆኑን በምትረዳበት ጊዜ ቁጣና ፀፀት ብስጭት ያድርባታል፡፡ጽንሱ እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ከቤተሰብ አባላት የቅርብ ዘመዶች፣ጎረቤቶች እና ጓደኞች ለእሷ ያላቸው ጥላቻ ወይም ተስማሚ ያልሆነ አመለካከት ጭንቀቷን ይበልጥ ያባብሰዋል፡፡ባልተወለዱ ህፃናት ላይ የሚወረወረው ተገቢ ያልሆነ አመለካከት ከተወለደም በኋላ መጠነ ሰፊ የሆነና ከፍተኛ ችግር እድገታቸው ላይ ያሳድርባቸዋል፡፡ተገቢ ያልሆነ አመለካከት በሚደረግላቸው እንክብካቤ ላይ አፍራሽ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ፍስሀ፣1990 ፣<u>የልጆች እድገትና መዳበር ስነ-ባህርይ ፣ገፅ 66-67</u>

<u>ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን የያዘውን ፊደል/ሆሄ በመምረጥ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ መልሱ፡፡</u>

1 _____ መፀነስ ፣ ሀ.ማርገዝ ለ. መቋጠር ሐ.ማቁም መ.ማማለል

2. _____ ትዘፈቃለች ፣ ሀ.ውሃ ውስጥ መነከር ለ.ትገባለች ሐ.ትታጠባለች መ.ትጠመቃለች

3.________ ፀፀት ፣ ሀ.ንዴት ለ.ቁጣ ሐ.ቁጭት መ.ብስጭት

4 .____.______አፍራሽ ተጽእኖ ሀ.አወንታዊ ተጽዕኖ ለ.ተስማሚ ግፊት ሐ.አሉታዊ ጫና መ.ሁሉም

5.________________የሚወረወረው፣ ሀ.የሚጣለው ለ.የሚሽቀነጠረው ሐ.የሚወነጨፈው መ.የሚሰጠው

II. <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልሳቸውን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ መልሱ፡፡</u>

6.ያላገባች ሴትን ጭንቀት ውሰጥ የሚከታት የመጀመሪያው መንስኤ ምንድነ ነው?_

________________________________________________

.________________________________________________

7.ይህች ሴት ጭንቀቷ በጣም ከፍተኛ የሚሆነው መቼ ነው?

________________________________________________

8.ከቤተሰብ፣ ከጎረቤትና ከጓደኛ ተፅዕኖ የሚደርስባት መንስኤው ምንድነው?

________________________________________________

9.ህጻናቱ ከተወለዱ በኋላ መጠነ ሰፊ እና ከፍተኛ ችግር እንዲደርስባቸው የሚያደርገው መንስኤ ምንድን ነው?________________________

________________________________________________

10. ጽሁፉ የተዋቀረበት/የተጻፈበት/ የጽሁፍ አወቃቀር ስልት ምንድን ነው?

________________________________________________

## አባሪ ‹‹መ››

## የማስተማሪያ ጽሁፍ

በምንባብ ውስጥ የጽሁፍን አወቃቀር ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን ፋይዳ መመርመር በሚል ርዕስ የቀረበን ጥናት ለማካሄድ መረጃን እንዲያስገኙ ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በምክንያትና ውጤት እና በማወዳደርና ማነፃፀር የተዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሁፎች/ምንባቦች/ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ተዘጋጅቶ ተሰቷል፡፡

እነዚህ ምንባቦች ለሁለቱም ቡድኖች ማለትም ለቁጥጥሩ እና ለሙከራ በድኑ የሚሰጡ ናቸው፡፡ልዩነቱ ትምህረቱ የሚሰጥበት ዘዴ ነው፡፡የሙከራ ቡድኑ አንብቦ መረዳትን በጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት እንዲማሩ ሲደረግ የቁጥጥር ቡድኑ ግን የሚማረው በተለመደው የአንብቦ መረዳት ዘዴ ነው፡፡

የትምህርት ክፍለ ጊዜ 8፡00--10፡00

ትምህርቱ የሚሰጥበት ክፍል ፣የማጠናከሪያ ትምህርት መስጭያ ክፍል

የተሰጠው ጠቅላላ ሰዓት__ 8፡00

## ትምህርት አንድ

የትምህርቱ ርዕስ፡- የምንባቡን ሓሳቦች ተመሳስሎና ልዩነት ትስስር መለየት፣

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የምንባቡ ሓሳቦች ያለቸውን ተመሳስሎና ልዩነት መለየት የሚያሰችሉ ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋትን ትለያላችሁ፣
- የጽሁፍ አወቃቀር ብልሐቶችን የሚጠቁሙ ሓሳበችን በመስጠት የቅድመ እውቀት ጥያቄዎችን ትመል ሳላችሁ፣
- ምንባቡን አንብባችሁ ሀሳቦችን በማወዳደርና በማነፃፀር ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት ትገልፃላችሁ፣
- የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች የተመሳስሎና ልዩነት የሚያመለክቱ ቃላትና ሀረጋትን ለይታችሁ ተወጣላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፣

ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የተሰጠው ሰዓት፡-2፡00

### በብልሃት ማለማመጃ መልመጃዎች

### የማወዳደርና ማነፃፀር የሀሳባ አወቃቀር ምንድንነው?

የማወዳደርና ማነፃፀር የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ፃሓፍት ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ሁነቶችን፣ድርጊቶችን፣ወዘተ ያላቸውን ተመሳስሎ አለያም ልዩነት ወይም ተመሳስሎና ልዩነት በመጥቀስ ዋናው ሓሳብ የሚብራራበት ስልት ነው፡፡በመሆኑም ሀሳቦች ባላቸው አንድነት ወይም ልዩነት እየተወዳደሩ ወይም እየተነፃፀሩ የሚዛመዱበት ስልት ነው፡፡የሚወዳደሩት ወይም የሚነፃጸሩት ጉዳዮች ቁጥራቸውና ዝርዝር ገፅታቸው በበዛ ቁጥር የተዛምዶ ደረጃው ውስብስብነት

ይጨምራል፡፡ዋና ዋና ሀሳቦችን በንፅፅር፣በውድድር ወይም አማራጭ እይታዎች በማቅረብ ይደራጃሉ፡፡

**የማወዳደርና ማነፃፀር የሀሳብ ማዋቀሪያ ቃላትና ሀረጋት እነማናቸው?**

አንድ እንቀፅ ወይም ጽሁፍ በሚነበብበት ጊዜ ሀሳቡ እንዴት እንደተደራጀ ወይም እንደተዋቀረ ለመለየት የሚረዱ የሀሳብ አያያዥ ወይም መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋት የጽሁፍ አወቃቀርን ብልሃት ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋት ይባላሉ፡፡ ማወዳደርና ማነፃፀር የሃሳብ ትስስር ጠቋሚ ቃላት ወይም ሀረጋት ጽሁፍ ውስጥ አንድ ነገር፣ደርጊት ወይም ሁነት ከሌላ ነገር፣ድርጊት ወይም ሁነት ያለውን ተመሳስሎ ወይም ልዩነት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የሚጠቅሙትም በሚወዳደሩ ነገሮች ዙሪያ የሚታዩ ተመሳስሎዎችን ለማመለከት፣በንፅፅር ወይም በልዩነት የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመጠቆም ነው፡፡

**ማነፃፀርን፡-**የሚጠቁሙ፤ከ_____የሚለየው፣በአንፃሩ፣በሌላ በኩል፣ከዚህ በተለየ፣ በተለየ መንገድ፣በምትኩ፣ከዚህ ይልቅ፣ከዚህ በተገላቢጦሽ፣ልዩነታቸው፣የሚለያቸው ወዘተ ናቸው፡፡

**ማወዳደርን፡-**የሚጠቁሙ ደግሞ በተመሳሳይ፣ይጋራሉ፣ይመሳሰላሉ፣የጋራ ባህሪያቸው ፣እንደዚሁም ፣ይህ ብቻ ሳይሆን ፣አንድነታቸው ፣ተመሳስሏቸው ፣ወዘተ የማወዳደርና ማነፃፀር የጽሁፍ አወቃቀር ትስስርን ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ተቀናቃኝ ያለበት አበዳሪና ተቀናቃኝ የሌለበትን ሰው የሚያሳይ ‹‹የሰው ልጅ ባህርይ›› የሚል ምንባብ ቀርቧል፡፡በምንባቡ ፍንጪ ሰጪ /ጠቋሚ/ ቃላትና ሀረጋት እንዴት የሃሳቦች ንፅፅራዊ ትስስር ለማሳየት እንደዋሉ ለማስረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ለቀረቡት ጥያቄዎቹን መመሪያቸውን በመከተል ለመመለስ ሞክሩ፣መልሶቹን ስትሰሩ የመምህራችሁ ድጋፍ አይለያችሁም፡

## የሰው ልጅ ባህርይ

በያዘው ስራ ባላንጣ እንደ ማይነሳበት ርግጡን ያወቀ ሰው ሁሉ ሌላውን ሰው ደሰ የሚያሰኝበት ወይም የሚጠቅምበትን መንገድ አይፈልግም፡፡ሃሳቡም ህልሙም ለጥቅሙ ብቻ ነው፡፡ሚዛን የማያጋድለው በሁለቱም ጫፍ እኩል የሚከብድ ነገር

ሲደረግበት ነው፡፡የሰው ባህሪው ሁለት ነው፡፡አንዱ መላካዊ፣ሁለተኛው ግን እንሰሳዊ ይባላል፡፡ ቀስቃሽ ካላገኘ ግን ሰው መላካዊ ባህሪውን አይከተልም፡፡ ለሰው አውራ ቀስቃሽ ግን ባላጣ ነው፡፡ተፎካካሪ ባላጣ ያለው ሰው ክፉ ስራ መስራት አይችልም፡፡ለባላጋራውም ቢሆን እንዳይሳነው ያውቃልና በደግነት ለማሸነፍ ይጣጣራል፡፡ገንዘብ ያለው ሰው አንድ ብቻ ሲሆን ገንዘቡንም ሲያበድር የፈለገውን ያህል ወለድ አምጡ ቢል ይሆንለታል፡፡የተቸገረውም ሰው አበድረኝ ሊልው ቢመጣ አይራራለትም፡፡ይልቁንም የሰውየውን መጨነቅ አይቶ ከፍ ያለ ወለድ ይፈልጋል፡፡ገንዘብ የሚያበድር ሌላ ባላንጣ ሲነሳበት ግን ተበዳሪዎቹ ወደ ባላንጣው እንዳይሄዱበት ሩህሩህ ነው ለመባል ይጣጣራል፡፡በተቸገሩትም ሰዎች ላይ መጨከኑን ይታየዋል፡፡ባላንጣውም የሚቀበለው ወለድ ስንት እንደሆነ እየጠየቀ ሰው ወደርሱ እንዲመጣለት የሚቀበለውን ወለድ ያሳንሳል፣ዝቅ ደርጋልም፡፡ገንዘብ የሚያበደሩ ባላንጣዎች በበዙ ቁጥር የእያንዳንዱ ባላንጣ ባህሪ እተሻለ ይሄዳል፤ወለዱም ሁሉ በጣም ዝቅ ይላል፡፡

ተስፋዬ፣1986፣ <u>አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር</u>፣ገፅ 53-54

I. ቀጥሎ ለተሰጡ ቃላትና ሀረጋት ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ መልሱ፤

1._________ባላንጣ፣ ሀ.ወዳጅ ለ.ጓደኛ ሐ.ባላንጋራ መ.ቤተዘመድ

2._________የማያጋድለው፣ ሀ.የሚወላውለው ለ.የማይዘነበለው ሐ.የሚያደላው መ.እሚደፋው

3.__________አውራ ቀስቃሽ፣ ሀ.ትልቅ አነሳሽ ለ.ዋና አነቃቂ ሐ.አንገብጋቢ መ.አሳሳቢ አካል

4___________ተፎካካሪ ባላንጣ፣ ሀ.ተቀናቃኝ ለ.ተወዳዳሪ ሐ.ተገዳዳሪ መ.ሁሉም

5.__________ወለድ፣ ሀ.ትርፍ ለ.እዳ ሐ.አራጣ መ.ሁሉም

II. ከዚህ በታች ለቀረቡ የተለያዩ ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ ነው የምትለትን መልስ እያብራራችሁ በመልስ መስጫው ላይ በመፃፍ መልሱ፡፡

1.ይህ ጽሁፍ የተዋቀረው በየትኛው የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ነው?

2. በዚህ ጽሁፍ በንፅፅር የቀረቡት ምንድናቸው?

3.አንድ ገንዘብ አበዳሪ በተበዳሪው ላይ ከፍ ያለ ወለድ የሚጠይቀውና የሚጨክ ነው መቼ ነው?

4.አንድ ገንዘብ አበዳሪ ዝቅ ያለ ወለድስ የሚጠይቀው እና ሩህሩህ ለመምሰል የሚጣጣረው ምን ሲሆን ነው?

5.በዚህ ምንባብ በንፅፅር የቀረቡት ምንና ምን ናቸው?

6.በምንባቡ ውስጥ በማነፃጸሪያነት የቀረቡትን ቃላት እና ሀረጋት የትኞዎቹ ናቸው? ዘርዝሩ?

## ፈተና

እሰቲ ከአንዲት ዘመም ያለች ጎርፍ ከሚያስፈራራት ጎጆ ውስጥ እንግባ፡፡ ወራቱ ሰኔ ነው፡፡ጊዜው መሸትሸት ብሏል፡፡የእንቁራሪቶች ቁርቁርታ፣የነፍሳት ሲርሲርታ ፣የውሾች ጩሄት ይሰማል፡፡ጋሏ ልታልቅ የደረሰች ኩራዝ ጭልጭል ትላለች፡፡አንድ ልጅ ጋቢ መሳይ የተደረተ ጨርቅ ደርቦ ያጠናል-ነገ ፈተና ነው፡፡የኩርዝ ጭስ በአፍንጫው መግባቱ አይሰማውም፣ ብቻ ያጠናል-ያጠናል፡፡ከዛ ውድቂት ላይ ይተኛል፡፡ ግን እንቅልፍ አይወስደውም-‹‹ነግቶልኝ ብቻ፡፡››ያጠናውን ሁሉ ጎልጉሎ ሲያወጣው፣አንደኛ ሲሆን፣ሲሸለም ከዚያ ክፍል ሲያልፍ ሲቀጥል ሲገሰግስ በሐሳቡ ይታየዋል፡፡በማይሸነፍ ሞራል ለሚያምር ዘለቄታዊ ውጤት ምናቡ ጭልጥ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ሌላው ደግሞ በቪላ ቤቱ ውስጥ በሥዕል በተጌጠ መኝታ ክፍል ውስጥ በአረግራጊ አልጋው ላይ በጀርባው ጋደም ብሏል፡፡ደብተሮቹና መጽሀፎቹ ውድ በሆነ ቦርሳ ውስጥ በዚብ እንደ ተዘጉ ከመዲኖው ላይ ተቀምጠው የማንበቢያውን መብራት ይሞቃሉ፡፡እሱ ግን እንደ ኮረዳ ጡት በሾሉት አንፖሎች ላይ አይኑን

ተክሏል፡፡ዝም ብሎ ያስባል፣ያስባል፡፡ ምክንያቱም ነገ ፈተና ነው፡፡ለመሆኑ ምን ሊመልስ ነው? መቼም ስም ብቻ ተጽፎ አይወጣም...ደብተርም ተይዞ አይገባም፡፡

መስፍን፣<u>የቡና ቤት ሥዕሎችና ወጎች</u>፣ገፅ 33-34

I. ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከተሰ አማራጮች በመምረጥ መልሱ፤

1.__________ውድቂት፣ ሀ.ምሽት ለ.ጨለማ ሐ.እኩለ ሌሊት መ.ሲነጋጋ

2.________የተደረተ ጨርቅ፣ ሀ.ደባደቦ ለ.የተለበጠ ብርድ ልብስ ሐ.ኩታ መ .ወፍራም ጨርቅ

3.__________አረግራጊ፣ ሀ.ተውረግራጊ ለ.ተለጣጭ ሐ.ከፍ ዝቅ የሚል መ.ምቹ

4.__________ዓይኑን ተክሏል፣ ሀ.አተኩሮ ይመለከታል ለ.አፍጧል ሐ. ያቁለጨልጫል መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

5.________ዘመም ያለች፣ ሀ.ያዘነ በለች ለ.ያማረች ሐ.ቀጥ ያለች መ.ጉልላቷ ያማረ

II. ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስቸውን በመምረጥ መልሱ፣

6. በዚህ ምንባብ ውስጥ ሁለቱን ተማሪዎች ያወዳደረበት የጽሁፍ አወቃቀር ስልት የትኛው ነው? ሀ.በማወዳደር ለ.በማነፃፀር ሐ.በማወዳደርና ማነጻጸር መ.አይታወቅም

7.ከሚከተሉት ሀረጋት አንዱ በተነፃፃሪ ዘይቤ ቀረቧ ል፡፡ ሀ. የማንበቢያውን መብራት ይሞቃሉ፤ለ.ጎርፍ የሚያስፈራራት ጎጆ፤ ሐ.እንደ ኮረዳ ጡት የሾሉ አንፖሎች፤ መ.ጊዜው መሸትሸት ብሏል፤

III. **በብልሃት ማለማመጃ መልመጃዎች**

IV. <u>ቀጥሎ የተሰጡትን /የቀረቡትን/ ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ፣</u>

8. በምንባቡ መሰረት ሁለቱን ተማሪዎች የሚያመሳስላቸው ወይም የሚወዳድራቸው ምንድንነው?________________________________________________

_9. ሁለቱ ልጆች የተነጻጸሩበትን ሰልት አብራርታችሁ መልሱ?

________________________________________________


10.‹‹የመጀመሪያው ተማሪ የመኖሪያ አካባቢ የት ይመስላችኋል?›› የተረዳችሁበትን መንገድ አስረዱ?

________________________________________________

11.የሁለተኛው ተማሪ መኖሪያስ የት ይመስላችኋል? መገለጫውስ ምንድንነው?

12.በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን ፍንጪ ሰጪ/ ጠቋሚ/ ቃላትና ሀረጋትን ዘርዝራችሁ ፃፉ? ______________________________________________

13. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ በማወዳደርና በማነፃፀር የቀረቡ ሀሳቦች ለይታችሁ ከታች የተሰጠውን የሀሳብ ማዋቀርያ ስዕል ክፍት ቦታዎች አሟሉ?




## ቢሮክራሲ

ቢሮክራሲ ሥራን በተለያየ ስልት ማደናቀፍ ፣በያደናፍቅም መጓተት፣ባያጓትትም መጥፎ የስራ ባህልን ኮትኩቶ አሳድጎ ለመጭው ትውልድ ሆን ብሎ የመቀበልና የማውረስ ሂደት ገኖ የሚታይበት የአሰራር ሁኔታ ነው፡፡ቦሮክራሲ በዓይነቱ ብዙ ነው፡፡ሁሉም የሚጋሩት ነገር ቢኖር የማህበራዊ ተቋማት ተገልጋይ ህብረተሰብ ተገቢ አገልግሎት እንዳያገኙ እንቅፋት በመፍጠር የግል ፍላጎትና ጥቅም ማስከበሪያ መሆናቸው ነው፡፡ከዚህ ቀጥሎ የተለመዱ የቢሮክራሲ ዓይነቶች ከነመለያ ባህሪያቸው በንፅፅር ቀርበዋል፡፡

የመጀወሪያው የቢሮክራሲ ዓይነት ‹‹አላውቅም ማለት የሚቀፈው ነው፡፡››ይኽ ቢሮክራት ብዙውን ጊዜ የትምህርት ደረጃው ዝቅተኛ ነው፡፡ከፍም ያለ **ቢሆንም እንኳን** በወጉ የጎለበተ ወይም የዳበረ አይደለም፡፡በአመዛኙ ሲገመገም ደካማ የትምህርት ችሎታና በቂ ልምድ የሌለው ሆኖ ይገኛል፡፡ነገር ግን የቢሮ አላፊ ሆኖ የሚሾመው በዘመድ ፣በአድሎ እና በሌላም በሌላ **መነሻ ብቻም** አይደለም፡፡

‹‹ይገባኛል››በሚለው ሽኩቻ ላይ በድፍረት የመድረክ ጨዋታ ብዙ ተጫውቶ ነው፡፡ **ስለዚህ** ልክ ነኝ የሚለውን የህይወት መመሪያ እንደትዳሩ ተንከባክቦ ይይዛል፡፡‹‹ልክ አይደለህም የሚለውን ሰው ‹እንዴት› ብሎ ከመጠይቅ **ይልቅ** ተኮሳትሮ ብቻውን መሆን ይመርጣል፡፡››**በተቻለ መጠን** ከሌሎች ራሱን ማራቅ፣ሲቀርቡት መንገድ መዝጋትና ሌላም ዘዴ ሲያጠና መዋሉን የተለየ ሙያ ያደርገዋል፡፡የዚህ ቢሮክራት ዋና ጠባይ ስህተቱን አለማመኑ ነው፡፡ሁል ጊዜ ይከላከላል እንጂ እጁን አይሰጥም፡፡ማዳመጥ አይችልም፡፡ቀላሉ ነገር እንዲገባው አይፈልግም፡፡

ሌላው ቢሮክራት ደግሞ ሲያዩት ለስለሰሳ ነው፡፡በመልክ **ሳይሆን** በጠባይና በአቀራረቡ ጥሩ ሰላምተኛ ነው፡፡ሽቁጥቁጥ ሲል የዋህ ይመስላል፡፡ዓላማው ሮጠህ ቅደም ብቻ ነው፡፡ተሹሞ ገንዘብ፣አሳብቆ ገንዘብ፣አታሎ ገንዘብ ብቻ ላጋልጠው ካላችሁ እናንተንም ሰነዶችንም የማጥፋት ረቂቅ ችሎታ አለው፡፡የሚያቅደው ሁሉ አያታውቅበትም፡፡

የመጀመሪያው መሰተንግዶውና ተግባቢነቱ ሚደነቅ የሚሆነው ድጋሚ እስክትፈልጉት ብቻ ነው፡፡ያኔ ጉቦ ካልሰጣችሁ በመጣችሁበት እግራችሁ ይመልሳችኋል፡፡ የዚህን ቢሮክራት ማንነት ለመቋጨት ለጉቦ ብቻ የተቀጠረ፣ ለጉቦ የሚኖር፣ ባለጉዳይን በገንዘብ ዓይን ብቻ ቅርጸ የሚያይ፣ሁለመናው ገንዘብ አሽታችነቱን የሚናገርበት እስስት መልክ ያለው ቢሮክራት ነው፡፡

‹‹ትንሽ ቢሮክራት ሊባል የሚችለው ደግሞ ሶስተኛው አይነት ቢሮክራስ ነው፡፡ትንሽ ሊባል የሚችነው ግንኃላፊነትን ስለሚፈራና ስለሚሸሽ ነው እንጂ ከሥራ ኅታችነት አነፃር ካየንው ከሌሎች ቢበልጥ እንጂ አያንስም፡፡ይኸኛው ገና ከተቀጠረበት እለት አንስቶ የገዛ ፊርማውን እንኳን ስለማያምን እየደጋገመ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ባለጉዳዮችን **ብቻ ሳይሆን** የገዛ መስርያ ቤቱ አዲስ ተቀጣሪዎች፣ቢሮው ውስጥ ድንገት የሚያገኛቸው ያልተለመዱ እቃዎች-አካባቡውን ሁሉ ተጠራጣሪ ያደርጉታል፡፡የከፋቱ ክፋት ደግሞ ኃላፊነቱ ገንዘን በሚመለከት ቁልፍ ቦታ ላይ ይሆናል፡፡እሱ ካልፈረመ ገንዘብ ወጪ አይደረግም፡፡ታዲያ እዚያ ቦታ ላይ ተቀምጦ አላውቅም ባይ ነው፡፡እሚፈርመው ነገር ሁሉ እዳ ውስጥ የሚያስገባው ይመስለዋል፡፡እሱ የወር ደመወዝ ከተበደረ ዕዳ አይባልም፡፡በኃላፊነቱ ከተሳሳተ ብቻ

ነው ዕዳ ውስጥ የሚገባው፡፡**በመሆኑም** ለራሱ ጥንቃቄ ሲል ለሌሎች ዴንታቢስ ይሆናል፡፡ ሰልጣኑን የሙጥኝ ብሎ ይይዛል፡፡

በአራተኛው አይነት የሚካተቱ በአንድነት ተፎካካሪ ቢሮክራቶች በሚል ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡እነዘህ ደግሞ ከማገልገል **ይልቅ** ለመከላከል የተዘጋጁ ናቸው፡፡ከቀና መልስ **ይላቅ** እኔ አይመለከተኝም የሚሉ ናቸው፡፡በአርሰ በርስ ቂም ወይም እኔ አበልጥ እኔ እበለጥ የሚል ልማድ ስላላቸው አንድ ቦታ ፈርመው ወደሌላ ሊመሩት የሚችሉትን ጉዳይ በተራ እየተያዩ ባለበት ያቆዩታል፡፡

ዋን ጉዳያቸው ገንዘብ ባይሆንም በጉቦ ወይም በሌላ መልኩ ቢያገኙ አይጠሉም፡፡ ትኩረታቸውን ወደ ጉቦ እንዳያደርጉ ኃይለኛ የሆኑ በጣም የሚበልጧቸው የበላዮች አሉባቸው፡፡የጥቅም ጉዳይየ ማይሳካላቸው **በመሆኑም** ባለጉዳይን በማጉላላት ይፅናናሉ፡፡የሚያውቁትን እንደማያውቁ መምሰል፣ቂም ነገር ስታወራቸው አርዕስቱን ወደ ሌላ መለወጥ፣አንተን ጎልተው ለረጅም ጊዜ በስልክ ማውራት፣ያለተራቸው ሌሎች ተስተናጋጆችን ማስገባት፣ወዘተ መለያ ባህሪያቸው ነው፡፡


<u>ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት መልሱ፣</u>

1. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ በንፅፅር የቀረቡት ምን ምን ናቸው የተነጻፀሩትስ በምንድንነው?
2. ከላይ በቀረበው በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ የሐሳብ አደረጃጀት ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋትን ነይታችሁ በማውጣት ፃፉ፡፡
3. በምንባቡ ውስጥ በንፅፅር የቀረቡት ተግባራት ምን ምን ናቸው?
4.በምንባቡ በንፅፅር የቀረቡት ነገሮች ምን የጋራ ባህሪያት አሏቸው? በምንስ ይለያያሉ?
5.ዝቅተኛ የትምህርት ችሎታና ስራ ልምድ ያለው ቢሮክራት ራሱን ለመሸፈን የሚጠቀመው ስልት ምንድንነው?
6.የመጀመሪያው ቢሮክራት ከሁለተኛው ቢሮክራት የሚመሳሰልበት በምንድነው? የሚለያየውስ?
7.ከላይ በቀረበው ምንባብ የቀረቡት ሐሳቦችን ዝምድና በጅምር አወቃቀር ሰርታችሁ አሳዩ?

8.ተጠራጣሪውና በአደገኛነቱ ከሌሎች ቢበልጥ እንጂ አያንስም የተባለው ቢሮክራት የትኛው ነው? መገለጫ ባህሪያቱስ?

9.አራተኞቹን ቢሮክራቶች ከሌሎቹ ቢሮክራቶች የሚለዩበትን በንፅፅር አሳዩ?

10.ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ሐሳቦች ያላቸውን ሐሳብ ትስስር በመለየት ታዛምዷቸውን ቀጥሎ በቀረበው የሐሳብ ማደራጃ ስዕል እየሞላችሁ አሳዩ?




## ትምህርት ሁለት

የትምህርቱ ርዕስ፡-የምንባቡን የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ትስስር መለየት፣

የትምህርቱ ዓላማ፡-

- ምንባቡ በምክንያትና ውጤት ትስስር የተዋቀረ መሆኑን ለመለየት የሚረዱ ብልሃቶች ምን ምን እንደሆኑ የቀደመ እውቀታችሁን ተጠቅማችሁ ትመልሳላችሁ፣
- ምንባቡን አብባችሁ ሀሳቦቹ የተዋቀሩበትን የምክንያትና ውጤት ትስስር ለይታችሁ ታብራራላችሁ፣
- የምንባቡ ዋና ዋና ሀሳቦች ትስስር በምክንያትና ውጤት መሆኑን
- የሚያመለክቱ ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋት ለይታችሁ ታወጣላችሁ፣
- ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች እየመረጣችሁ ታሳያላችሁ፣
- የምንባቡን ሀሳብ የምክንያትና ውጤት ትስስር ለመለየት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በተሰጠው ክፍት ቦታ ምላሻችሁን ትሰጣላችሁ፣

**ብልሃቱን ለማለማመድ የቀረበ ማብራሪያ**

**የምክንያትና ውጤት የሀሳብ አወቃቀር ምንድነው ?**

ምክንያት አንድን ነገር ለምን እንደተከሰተ የሚነግረን ሀሳብ ነው፡፡ውጤት ደግሞ በአንድ ክንውን ምክንያት ምን እንደተከሰተ የሚጠቁም ሀሳብ ነው፡፡ በምክንያትና ውጤት የሀሳብ አወቃቀር ሁነቶች ወይም የተሰበሰቡት ሰበብና ያስከተሉት ውጤት በትስስር በሚቀርብ ሀሳብ የሚደራጅበት የሀሳብ አወቃቀር አይነት ነው፡፡ይህ አወቃቀር ሀሳቦችን ባላቸው ምክንያታዊ ተዛመወዶ የሚያስተሳስር ነው፡፡ የምክንያትና ውጤት ትስስር መስመሮች በጨመረ ቁጥር ተዛምዶ ውስብስብነቱ ከፍ ይላል፡፡አንድ ምክንያት በርካታ ውጤቶች ወይም በርካታ ምክንያቶች አንድ ውጤትን የሚያስገኙበት ሁኔታ ሲፈጠር ተዛምዶውም የተወሳሰበ ይሆናል፡፡

**የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ትስስር ጠቋሚ ቃላት**

የጽሁፍ አወቃቀር ፍንጭ ሰጪ ቃላት ወይም ሀረጋት የሚባሉት አንድ አንቀፅ ወይም ጽሁፍ በሚደራጅበት ጊዜ ሀሳቡ እንዴት እንደተደራጀ የሚያመለክቱ የሀሳብ ማያያዥዎች ወይም መሸጋገሪያ ናቸው፡፡የምክንያትና ውጤት የሀሳብ ትስስር ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋት በአስረጅ ጽሁፍ ውስጥ ሁነቶች፣ድርጊቶች ፣ነገሮች፣ወዘተ የምያመለክቱ ናቸው፡፡የትኛው ነገር ወይም ድርጊት የትኛውን ውጤት እንዳመጣ ወይም የትኛው ውጤት በምን ሰበብ፣ነገር፣ድርጊት ወይም ሁነት እንደተከሰተ የሚያመለከቱ ዋና ፍንጭ ሰጭዎች ናቸው፡፡ቃላትና ሀረጋቱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ምክንያቱም፣ስለ፣በዚህ ስበብ ፣በዚህ የተነሳ ፣በዚህ መሰረት፣ከዚህም በለይ ፣እንደዚያ ከሆነ፣ለዚህ መነሻው፣ይህ ሊሆን ወይም ሊከሰት ወይም ሊመጣ የቻለው፣ውጤቱ፣ወዘተ ናቸው፡፡

- ከዘህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለመመለስ ሞክሩ?

- በምንባቡ ውስጥ የትኞቹ ሀሳቦች በምክንያት ተገልጸዋል?
- የትኞቹ ሀሳቦችስ በውጤትነት ተገልጸዋል?

# የተውኔት አውድ

ፀሐፊ ተውኔት በተለያዩ አጋጣሚዎች እራሱን በብዙ ማህበራዊና ግላዊ ክንዋኔዎች በሚከናወንበት ሊያገኘው ይችላል፡፡እነዘህ ማህበራዊ ወይም ግለሰባዊ ክንዋኔዎች አሳዛኝ ወይም አስደሳች ጎን ኖሯቸው ግን ከእንከን ወይም ከህፀፅ የነፁ ባለመሆናቸው መሻሻል ካለዚያም መታረም እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡አንድ አይነት እርማት ወይንም መስተካከል መፈለጋቸው ቢታውቅም አንኳን ቅሉ ከዋኞቹ ስህተቱን በቅጡ ሳይረዱ እንደቀሩ ይታያል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ታዲያ በፀሃፊ ተውኔቱ ዘንድ የድርሰት ፅንስ እንዲፀነስ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ለምሳሌ የብየዳ ሙያ ሲማር ከርሞ ወደ መንግስት ሥራ ለመሰማራት እየተዘጋጀ  ያለ ሙያተኛ በሀኪም ተመርምሮ የብየዳ ስራውን ለአንዴዬና ለመጨረሻ ጊዜ ካላቆመ የአይን ብርሃኑን እንደሚያጣ ቢነገረው፣አንዲት ልጅአገረድ የሰርጓ ቀን ተሞሽራ በመጠባበቅ ላይ እንዳለች በለዮው ሃሳቡን የቀየረና ጋብቻውንም የሰረዘ ለመሆኑ መልዕክት ቢደርሳት ፣ወይም ባንፃሩ ወንዱ ሙሽራ ሊወስዳት ሲሄድ ተጠልፋ ቢያገኛት፣የሚፈጠረው አስደንጋጭ ሁኔታ በፀሃፊ ተውኔቱ ልቦና ቅንጣት የተውኔት ዘር ለመዝራት ምክንያት ይሁናል፡፡እንዲህ መሰሉ ህፀፅ እንዲታረምም ፀሃፊ-ተውኔቱ ህሊናዊ ከሆነ የድርሰት ሃሳብ በመነሳት አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

<u>የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ</u>፣ፋንታሁን እንግዳ፣2005፣ገፅ130-131

**ብልሃቱን በድጋፍ ማለማመድ**

1. በምንባቡ ውስጥ በምክንያትነት የቀረቡት ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ የሀሳባ ማደራጅያ ጠቋሚ ቃላትና ሀረጋት እየለያችሁ አውጡ?
3. የተጠቀሱት ሀሳቦች ውጤቶች ወይም ምክንያቶች መሆናቸውን ከምንባቡ ውስጥ ለመለየት መነሻ የሆኑት ፍንጪ ሰጭ ቃላትና ሀረጋት የትኞቹ ናቸው?
4. ከላይ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ያሉ ምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን ሀሳቦች እየለያችሁ የራሳችሁን የሀሳብ ማደራጃ ስዕል በመስራት ሰርታች አሳዩ?

## የቋንቋ ለውጥ

በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የአማርኛ ቋንቋ ዝንባሌ ግን፣ የተፈጥሮ ሥርዓታዊ የቋንቋ ሕግ ለውጥ **ሳይሆን**፣ በዘላንነትና በግደለሽነት የመጣ ለውጥ ነው፡፡**ለዚሁም** ዋናው ምክንያት ልዩ ልዩ የባዕድ ቋንቋዎች/ፈረንሳይኛ፣ጣልያንኛ፣ እንግሊዝኛ.../በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የአማርኛ ቋንቋ በማደፍረሳቸው ነው፡፡**በተለይም** ከብዙ ጊዜ ጀምሮ እንግሊዝኛ በአገራችን ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት መስጫ ቋንቋ በመሆኑና አዲሱ ትውልድ እንደ ሁለተኛ ቋንቋው አድርጎ ስለሚጠቀምበት አማርኛችንን አደፍርሶታል፡፡**ከዚህም በላይ** አብዛኛውን ጊዜ በየሲኒማ ቤቱና በቴሌቪዥን ላይ የሚያየው ፊልም፣ በእየለቱ ከልዩ ልዩ ጣቢያ በሬዲዮ የሚሰማው ወሬ፣ ሙዚቃና ዘፈን፣ በየጊዜው የሚያነበው ጋዜጣ፣መጽሐፍ ሁሉ በአብዛኛው በእንግሊዝኛ በመሆኑ በአማርኛ ሀሳቡን በሚገልጽበት ጊዜ ወዶም ሆነ ሳይወድ የእንግሊዝኛ ቃል ጣልቃ እያስገባ ሲነጋገር ይሰማል፡፡**ከዚህም አለፎ ተርፎ** የእንግሊዝኛውን የአነጋገር ፈሊጥ፤መጠጣ ውሰድ ፣ቡና ታዘጋጇለች ፣መድሓኒት ወስዶ፣ሓኪም አየ.../ቃል በቃል በመውረስ አማርኛ በሚናገርበት ጊዜ ይጠቀምበታል፡፡

አሰፋ፣ ‹‹የአማርኛ ቋንቋ አቋም››፣Teaching News,ገፅ-2

V. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መልስ ነው ያላችሁትን በመምረጥ መልሱ፣

1.________ማደፍረስ፣ ሀ.መበጥበጥ ለ.መረበሽ ሐ.ሥርዓት ማሳጣት መ.ሁሉም መልስ ነው፡

2.________ዝንባሌ፣ሀ.ፍላጎት ለ.አመለካከት ሐ.እይታ መ.ሁሉም

3.________እንዝህላል፣ሀ.ቦዘኔ ለ.አስተዋይ ሐ.ግዴለሽ መ.ጠንቃቃ

4.________የአነጋገር ፈሊጥ፣ ሀ.የአገላፅ ለዛ ለ.የአነጋገር ልማድ ሐ.የአነጋገር ዘዬ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

5.________የባዕድ ቋንቋ ፣ ሀ.አገርኛ ቋንቋ ለ.የወገን ቋንቋ ሐ.የራስ ቋንቋ መ. የሌላ ሀገር ቋንቋ

VI. ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፤ ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ጥያቄዎቹን በማብራራት መልስ ስጡ፤

6. ይህ ከላይ የቀረበው አንቀጽ /ጽሁፍ/ ለምክንያትና ውጤት ትንተና ስልት በምሳሌነት ሊቀርብ የቻለው ምን ምን መመዘኛዎችን ማሟላት በመቻሉ ይመስልሃል/ሻል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

7.በመጀመሪያው ዐረፍተነገር ውስጥ ለተከሰተው ውጤት መንሥኤዎቹ ምንድን ናቸው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

8.በዐረፍተ ነገር አንድ ውስጥ ለተከሰተው ወይም ለመጣው ውጤት ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

9 .የአማርኛ ቋንቋን እያደፈረሱ ያሉት ምንድን ናቸው ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

10. አዲሱ ትውልድ ቃል በቃል በመውረስ እንዳለ የሚጠቀመው ምንድንነው?

____________________________________________________________

11. በምንባቡ ውስጥ የትኞቹ ሀሳቦች በውጤትነት ተገልጸዋል ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

12.በምንባቡ መሰረት አንድ ምክንያት ስንት ውጤቶች አሉት?

____________________________________________________________

____________________________________________

## የእናቶች የወሊድ ስርዓት

ማንኛዋም እናት ተፈጥሮ በፈቀደችው የአወላለድ ሥርዓት መውለድ ብትችል ተመራጭና አስፈላጊ ነው፡፡ይህ የተፈጥሮ ሂደት እውን እንዳይሆን በርካታ

**ምክንያቶች** እክል ሲፈጥሩ ይስተዋላል፡፡የእናትዋንም ሆነ የፅንሱን ህይወት ለመታደግ ሲባል በቀዶ ህክምና ዘዴ ለማዋለድ ይሞከራል፡፡ይህ የሚሆነው ደግሞ እናትየዋ ለመቆጣጠር የሚያሥቸግር የደም ግፊት፣ የስኳር፣የሚጥል ወይም የሚያንቀጠቅጥ ህመም ካለ፣የበፊት አወላለዷ ችግር የነበረበት ወይም በቀዶ ህክምና የወለደች ከሆነና ሌሎች በእናትየዋ በኩል የሚታዩ ችግሮች ካሉ ነፍሰጡሮች በቀዶ ህክምና የመውለድ እድላቸው ሰፊ ይሆናል፡፡**ሌላው** ፅንሱ ከእናትየዋ አካል ጋር ያለመመጣጠን ካለ፣ ማለትም ፅንሱ ከሚጠበቀው በላይ ተልቆ የእናትየዋን ማህፀን በማጥበቡ ሳቢያ በትክክለኛው የአወላለድ ሒደት መውለድ ሳትችል ስትቀር ለእናትየዋም ሆነ ለፅንሱ ደህንነት ሲባል የግድ በቀዶ ህክምና እንድትወልድ ትደረጋለች፡

ሶስተኛው እናቶች በቀደ ህክምና እንዲወላዱ የሚዳርጋቸው ደግሞ የመህፀን መሰንጠቅ ነው፡፡ብዙ ግዜ እከሊት በወሊድ ጊዜ መህፀኗ ተሰነጠቀ አልያም ተሸነቆረ ሲባል ይሰማል፡፡ከላይ ቀደም ሲል እናቶች በቀደ ህክምና እንዲወልዱ ያስገድዳሉ ተብለው የተገለጹት ምክንያቶች ለዚህም መፈጠር **እንደ ምክንያት** ይሆናሉ፡፡ስለዚህ የተባለውን ላለመደገም ያህል ተጨማሪ በሚሆኑ ምከንያቶች ላይ እናተኩር፡፡ ለረጅም ጊዜ ያለፋታ ማማጥ፣በመጀመሪያ በቀዶ ህክምና የወለደች እናት ሁለተኛውን አምጣ ለመውለድ ያለ ባለሙያ ሙከራ ስታደርግ፣ብዙ ጊዜ የወለዱ ሴቶች ከሆኑ፣መንታ በሚፀነስበት ጊዜ የፅንሶቹ አቀማመጥ የተዛባ ሲሆን፣በመውደቅ ወይም **በሌላ ምክንያት** ድንገተኛ አደጋ ሲደርስባቸው የመሳሰሉ ሁኔታዎች ሲከሰቱ እናቶች የመህፀን መሰንጠቅ አልያም መሸንቆር ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡የመህፀን መሻንቆርም ሆነ መሰንጠቅ በየትኛውም የወሊድ ጊዜ ሊያጋጥም የሚችል አደጋ ነው፡፡አደጋው እንዳይደርስ መከላከል የሚቻለው ደግሞ እናቶች በየጊዜው የወሊድ ክትትል ማድረግና ሐኪም በሚሰጣቸው ምክር መሰረት ወቅቱን እየጠበቁ ክትትላቸውን መከወን ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

<u>*ዘማይንድ መፅሄት 1ኛ ዓመት፣ቁጥር 14*</u>*፣ታህሣሥ* ፣2002፣ገጽ=24-25

**በብልሃት መስተማሪያ መልመጃዎች**

ከዚህ በታች ለቀረቡ የተለያዩ ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ መልሱ፣

1___________ለመታደግ፣ ሀ.ለማትረፍ ለ.ለማዳን ሐ.ለማስማመት መ.‹‹ሀ››እና ‹‹ለ›› መለስ ናቸው

2.___________ያለ ፋታ፣ ሀ.ያለ ትግስት ለ. ያለ እረፍት ሐ.ያለ ድካም መ.ያለ ልፋት

3.____________ተፈጥሮ በፈቀደችው፣ ሀ.ተፈጥሮ ስትመች ለ.በእግዚአብሔር ፍቃድ ሐ.ተፈጥሮ ባመቻቸችው መ.በዘፈቀደ

4. ___________ነፍሰጡር፣ ሀ.እርጉዝ ለ.እመጫት ሐ.ወረገብ መ.እርጥ

5.___________እውን እንዳይሆን፣ሀ.ግልፅ እንዳይሆን ለ. እንዳይሳካ ሐ.ተግባራዊ እንዲሆ መ.ግልፅ እንዲሆን

VII. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ መልሱ፣

6. በአጠቃላይ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ምክንያቶች የሚያመለክቱት ወይም ውጤታቸው ምን ሊሆን ይችላል? ሀ.ተፈጥሮ በፈቀደችው መንገድ መውለድ ለ. በቀዶ ህክምና መውለድ ሐ. በማማጫ መሳሪያ እየታገዙ መውለድ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

7. በመጀመሪያው አንቀጽ በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ይህ የተፈጥሮ ሂደት እውን እንዳይሆን በርካታ ምክንያቶች እክል ሲፈጥሩ ይስተዋላል የሚለው አገላለጽ የትኛውን የተፈጥሮ ሂደት ማለቱ ነው?

ሀ.ተፈጥሮ በፈቀደችው ስርዓት መውለድን ለ.በቀዶ ህክምና መውለድን ሐ.ያለእረዳት መውለድን መ.በባህላዊ ዘዴ መውለድን

I. ቀጥሎ ለቀረቡ ማብራሪ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ማብራሪያ በመስጠት መልሱ፣

8.ለማህፀን መሰንጠቅ ወይም መሸንቆር የሚዳርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ዘርዝሩ?

________________________________________

________________________________________

9. ሁለተኛው እናቶችን በቀዶ ህክምና እንዲወልዱ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድንነው?__________________________________________________________

______________________________________________________________________

10.ይህ ጽሁፍ ለምክንያትና ውጤት የጽሁፍ አወቃቀር ብልሃት ምሳሌ ሊሆን የቻለው ምን መመዘኛዎችን ማሟላት በመቻሉ ይመስላችኋል?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________

11.ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉ ጠቋሚ/ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀረጋት ዘርዝራችሁ ፃፉ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_______________________

12. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን ሀሳቦች ለይታችሁ ከታች የተሰጠውን የሀሳብ ማዋቀርያ ስዕል ክፍት ቦታዎች አሟሉ?

